# ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ

## አንደኛ መጽሐፍ

በኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን የሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን የትምህርት
ክፍል የተዘጋጀ

አዲስ አበባ፥ 1988 ዓ.ም

መ. የሮማ መንበር . . . 43
ሠ. የኤፌሶን መንበር . . . 43
ረ. የሰርምኔስ መንበር . . . 43
ሰ. የአቴና መንበር . . . 43
ሸ. የቁስጥንጥንያ መንበር . . . 44

ምዕራፍ አንድ

ቅዱሳን ሐዋርያት . . . 45
1. የሐዋርያት አመራረጥ . . . 46
2. የሐዋርያት ሲኖዶስ . . . 47
3. አዕማድ ሐዋርያት . . . 48
4. ቅዱስ ጴጥሮስ – የሐዋርያት አለቃ . . . 48
5. የሐዋርያት ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን . . . 50
6. የሐዋርያት ዝርዝር . . . 51
7. የሐዋርያት ክብር በቤተ ክርስቲያን . . . 57

ምዕራፍ ሁለት

የሐዋርያት ታሪክ፣ ሥራና ገድል . . . 61
1. ቅዱስ ጴጥሮስ . . . 61
የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት የመጀመሪያይቱ . . . 67
የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ሁለተኛይቱ . . . 67
2. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ . . . 68
3. ቅዱስ እንድርያስ . . . 70
4. ቅዱስ ዮሐንስ . . . 71
የቅዱስ ዮሐንስ መጻሕፍት . . . 76
የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል . . . 77
የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት የመጀመሪያይቱ . . . 80
የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት ሁለተኛይቱ . . . 80
የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት ሦስተኛይቱ . . . 81
የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ . . . 81
5. ቅዱስ ፊልጶስ . . . 85
6. ቅዱስ በርተሎሜዎስ . . . 86
7. ቅዱስ ቶማስ . . . 89
8. ቅዱስ ማቴዎስ . . . 93
የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል . . . 97
9. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ . . . 98
የቅዱስ ያዕቆብ መልእክት . . . 100
10. ቅዱስ ታዴዎስ (ይሁዳ) . . . 100
የሐዋርያው የቅዱስ ይሁዳ መልእክት . . . 103
11. ቅዱስ ስምዖን ቀነናዊው . . . 103
12. ቅዱስ ማትያስ . . . 104
13. ቅዱስ ጳውሎስ . . . 106
ሀ. ከልደት – ጥምቀት . . . 106
ለ. ጉዞዎቹ . . . 109
ሐ. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት . . . 111
ወደ ሮሜ ሰዎች . . . 111
ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች . . . 113
የመጀመሪያይቱ . . . 113
ሁለተኛይቱ . . . 114
ወደ ገላትያ ሰዎች . . . 115
ወደ ኤፌሶን ሰዎች . . . 116
ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች . . . 117
ወደ ቈላስይስ ሰዎች . . . 118
ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች . . . 118

| | |
|---|---|
| የመጀመሪያይቱ | 119 |
| ሁለተኛይቱ | 119 |
| ወደ ጢሞቴዎስ | 120 |
| ወደ ቲቶ | 121 |
| ወደ ፊልሞና | 121 |
| ወደ ዕብራውያን | 122 |
| መ. ማጠቃለያ – ስለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ | 123 |
| **ምዕራፍ ሦስት** | |
| ሌሎች በአንደኛው መ/ክ/ዘመን የተነሡ ቅዱሳን | 126 |
| 1. ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ | 126 |
| 1.ሀ. የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል | 127 |
| 1.ለ. የሐዋርያት ሥራ | 129 |
| 2. ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ | 130 |
| . የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል | 133 |
| 3. ቅዱስ ጢሞቴዎስ | 135 |
| 4. ቅዱስ ቲቶ | 138 |
| 5. ቅዱስ በርናባስ | 138 |
| 6. ሊቀ ዲያቆናት ቅዱስ እስጢፋኖስ | 139 |
| 7. ቅዱስ ስምዖን የጌታ ወንድም | 142 |
| 8. ወንጌላዊው ፊልጶስ | 143 |
| 9. ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ | 145 |
| 10. ሌንጊኖስ ሰማዕት | 146 |
| 11. አልዓዛርና እኅቶቹ | 147 |
| 12. ጲላጦስ ሰማዕት | 148 |


# መቅድም

ትምህርተ ሃይማኖት ማለት ነገረ እግዚአብሔር እና ነገረ ቅዱሳን ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ልጆቹም ቅዱሳን እንሆን ዘንድ የቅድስናን ጸጋ ሰጥቶናል። የሃይማኖት ታሪክ ማለትም እግዚአብሔር በየዘመናቱ ከልጆቹ ጋር ያደረገው የፍቅር ግንኙነት ነው። ይህ በቸርነቱና በምሕረቱ የሚያደርገው ግንኙነት ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሚፈጠረው ከሕዝቡ መሐል ሆነው ስለሕዝቡ ከሚጸልዩ፣ ከሚማልዱና ከሚያስቡ ቅዱሳን ጋር በመሆን እግዚአብሔር በምድር የሠራቸውን ድንቅ ሥራዎች በተመለከትን ቁጥር አብረን ቅዱሳን ልጆቹንም እናገኛለን።

ለልዑል እግዚአብሔር ፍቅር መላ ሕይወታቸውን ከሰጡት፣ እስከ መጨረሻው ከእርሱ ጋር ከኖሩት፣ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለምሕረቱ የሚሆን ሰው አጥቶ እንደ ቅፍርናሆም ሕዝቦች እንዳንሆን ካደረጉን የእግዚአብሔር ልጆች መካከል የክርስትና ፋና በዓለም መብራት በጀመረበት የመጀመርያው መ/ክ/ዘመን የተነሡት ቅዱሳን ይገኙበታል።

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው እነዚህን ቅዱሳን፣ ታሪካቸውን፣ ትምህርታቸውን፣ ተጋድሏቸውንና እርአያንታቸውን ከእነርሱ ብዙ ዘመን ዘግይቶ የተወለደው ይህ ትውልድ ያውቅ ዘንድ ነው። ነገር ግን በዚህች ትንሽ ጥያቄ በዚያ ዘመን የተነሡትን ቅዱሳን ታሪክ፣ ገድልና ትምህርት ሁሉንም ለመዘርዘር መሞከር ማለት ዓባይን በጭልፋ እንደሚሉት መሆን ነው።

ይሁን እንጂ ከፈኛው በአጭሩ፣ ከብዙው በጥቂቱ፣ ቀንጭበን በረከታቸውንና ትሩፋታቸውን እንካፈል ዘንድ ለማቅረብ ሞክረናል።

ይህ መጽሐፍ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን ቁም ነገሮች እንዲይዝ የተደረገውም ለዚህ ነው።

1. የሐዋርያት ትምህርት፣ ታሪክና ገድል ለኛ ስለደረሰበት መንገድ – ስለ ትውፊት።
2. የሐዋርያትና በሐዋርያት ዘመን የተነሡ ቅዱሳንን ገድልና ትሩፋት።

3. የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ መጠነኛ ጥናት፤ እንዲሁም

4. የዚህ ክ/ዘመን አጠቃላይ ክርስቲያናዊ ጉዞ ለማሳየት ይቻል ዘንድ ጥረት ተደርጉዋል።

እነዚህን ነገሮች ለማዘጋጀት ጥንታውያን የሀገራችንን መጻሕፍት፤ የጥንታውያን ታሪክ ጸሐፊዎችን መዛግብት (ዮሴፍ ወልደ ኩርዮን፤ አውሳብዮስ፤ ሩፊኖስ፤ ወዘተ.)፤ በዘመናችን በነዚህ ርእሶች ዙርያ የተዘጋጁ መጻሕፍት፤ በቤተክርስቲያናችን ከ1930 – 1985 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት የታተሙ ጋዜጦችና መጽሔቶችን ለማገላበጥ ተሞክሮአል።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ሆኖ ጽሑፍ በአንድ ጊዜ ፍጹም ሊሆን አይችልምና ነገ ከነገ ወዲያ የሚነሡ ሊቃውንት አጉልተው አስፍተው እንደሚያቀርቡት እናምናለን።

ይህ መጽሐፍ ግን:-

- ለምእመናን ስለ ሃይማኖታቸውና የሃይማኖት አባቶቻቸውን የሚያውቁበት፤
- ለሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ስለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ነገረ ቅዱሳንን ለመግርያ መነሻ፤
- በነዚህ ርዕሶች ዙርያ ጥናት ለሚያደርጉ ምሁራን ደግሞ ፍንጭ ይሰጥ ዘንድ በማኅበራችን የትምህርት ክፍል የተበረከተ ነው።

በዚሁ አጋጣሚ ጽሑፉን በማቀናበር፤ መረጃ መጻሕፍትን በማሰባሰብ፤ ረቂቁን በመገልበጥ፤ በኮምፒዩተር በማዘጋጀትና ለኅትመት በማሰናዳት ለተባበሩን ሁሉ ምሥጋናችንን እናቀርባለን። እግዚአብሔር ዋጋቸውን በሰማያት ይክፍላቸው ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን አሜን።

እግዚአብሔር ሥራችንን ይባርክ!

የማኅበረ ቅዱሳን የትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ



# ክፍል አንድ

## ክርስቲያናዊ ትውፊት

### መግቢያ

### ትውፊት ምንድነው?

ትውፊት:- አወፈየ ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ውርስ፤ ቅብብል ማለት ነው። ይኸውም አንድ ትውልድ (ሰው) ከርሱ በፊት ከነበሩት የሚወርሰው፣ የሚያገኘው፣ የሚቀበለው ነገር ነው። ሂደቱም በዚህ የሚያበቃ ሳይሆን እርሱም በተራው ለተተኪው ያስተላልፋል።

‹ዘአወፈየኒ አወፈይኩከ› እንዳለ በሥርዓተ ቅዳሴ።

### ትውፊትና ትውልድ

በዚህ ዓለም ላይ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ አያሌ ትውልድ አልፏል። እነዚህ ትውልድ በዚህ ዓለም የመጀመርያዎቹ ሳይሆኑ ተተኪዎች ናቸውና ከቀደምቶቹ የሚወርሱት፣ የሚቀበሉት የሚረከቡት ብዙ ነገር አላቸው።

ትውልድ ያለትውፊት አይኖርም። ጠቃሚም ይሁን ጉጂ በመስማት፣ በማየት ካለፈው ትውልድ የሚረከበው ነገር አለው። ለምሳሌ ኢትዮጵያውያን፤ የዶሮ ወጥ አሠራር፣ የእንጀራ አመጋገቡ፣ የአበሻ ቀሚስ፣ የፀጉር አሠራር፣ ወዘተ. ያገኘነው ከቀደሙት አበው ያየነውን፣ የተረከብነውን፣ የሰማነውን መሠረት አድርገን ነው። እኛንም ኢትዮጵያውያን የሚያሰኘን የቀደሙትን ወርሰን መገኘታችን ነው።

በክርስትናው ዓለምም፤ ጌታችን ካስተማራቸው፣ ሠርቶ ካሳያቸው፣ ሑሩ ወመሀሩ ብሎ ካዘዛቸው ሐዋርያት፣ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ብዙ ነገር ወርሰዋል። እነዚህ ደቀ መዛሙርቶቻቸውም ሐዋርያውያን አበው ለመባል የበቁት ሐዋርያትን መስለው፣ ሆነውም በመገኘታቸው ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእግሩ ለተተካው ለመንፈስ ቅዱስ ልጁ ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክት:- አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄ

ዱን፤ አሳቤንም፤ እምነቴንም፤ ትግሥቴንም፤ ፍቅሬንም፤ መጽናቴንም፤ ስደቴንም፤ መከራዬንም ተከተልህ። 2ጢሞ.3፥10–11። በማለት እንደመሠከረለት፤ በክርስትናው ጉዞ አባቶቹን የሚተካው ትውልድ ሁለመናቸውን ወርሶ መገኘት አለበት። ያለበለዚያ ትውልድ ነው ተብሎ ሊቆጠር አይችልም። የራሱን አመለካከት፤ መንገድና ፍልስፍና ብቻ በመከተል አዲስ መሠረት እጥላለሁ ባይ ስለሚሆን ከጥንት ሲፈስ የነበረው መንፈሳዊ ጅረት በርሱ ዘመን ይገደብበታል። ክርስትና ደግሞ ምንጩም ወንዙም አንድ ነው።

## ትውፊትና ዕድገት

ብዙ ሰዎች ሁል ጊዜ የቀደሙትን ከተመለከትን ዕድገታችን፤ የትውልዱም የፈጠራ ችሎታ ይቋረጣል ብለው ሥጋታቸውን ይገልጣሉ። ነገር ግን ትውፊት ዕድገትን አይገድብም እንዲያውም ዕድገቱ የተስተካከለ እንዲሆን ያደርገዋል!

ማደግ ማለት የራስን ትቶ የሌላውን ብቻ መቀበል አይደለም። የራስ የሆነውን በአግባቡ መጠቀም ማለት እንጂ ዕድገታችን እንጀራን አጥፍተን ፓስታ ብቻ ለምን አንበላም? የሐበሻ ቀሚሱን አሳድደን ለምን ዕርቃንን የሚያጋልጠውን አንለብስም? የዘመን አቆጣጠራችን ይቅርና የአውሮፓ ቀመር ይተካ። የቅዱስ ያሬድ ዜማ ተጥሎ፤ የነሞዛርት ቅኝት ያምጣልን ዓይነት ከሆነ ጉዞዋችን ወደ ማደግ ሳይሆን አንገትን ቆርጦ ለፀጉር አበጣጠር የመጨነቅ ያህል ነው።

የራሳችን የሆነውን ወደን፤ አክብረን የበለጠ የሚያድግበትን መንገድ መፈለግ ከሆነ ያ ዕድገት ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

የሰጉን ዕንቁላል ስለጠፋ ጉልላት ይቅር አይባልም። ሰጉን እናርባ ይባላል እንጂ! ካህን ስላጠረ ምእመኑ ይቀድስ አይባልም። ልጆቻችንን አስትምረን ካህን እናድርጋቸው ሹመት እናሰጣቸው ይባላል እንጂ!

ዓለምኮ የሚጓዘው በአንድ አቅጣጫ ብቻ አይደለም፤ በተቃራኒውም ሊያመራ ይችላል። የወንጀል አሠራር፤ የውንብድና ኑሮ እየረቀቀ እና በዘመኑ ቴክኖሎጂ እየተደገፈ በመጣ ቁጥር ዕድገት ብለን ከቆጠርነው ተሳስተናል።



በመጀመርያው መ/ክ/ዘ የነበሩ ሐበው ቀደምት አበው የቤተ ክርስቲያንን አሠራር፤ የአምልኮ ሥርዓቱን ልብሰ ተክህኖውን፤ ጽንሐሑን፤ ዕጣኑን፤ መንበሩን ወዘተ. ከኦሪቷ ቤተ መቅደስ ለቤተክርስቲያን እንደሚገባ አድርገው ተረከቡ እንጂ በዘመኑ ሠልጥኖ የነበረውን የግሪካዊ–ሮማ (Greeco-Roman) ፍልስፍና አልጨመሩበትም። ይህም የሆነው ሥልጣኔው፤ ፍልስፍናው፤ ዕውቀቱ ሳይገባቸው ቀርቶ ሳይሆን የዚህ ሥጋዊ ፍልስፍና ውጤቱ እግዚአብሔርን መካድ፤ ሥጋዊ ፍላጐትን ማርካት፤ ምድራዊ ድሎትን ማደላደል መሆኑን ስለተገነዘቡ ነው።

ይሁን እንጂ አባቶቻችን በዚያን ዘመን ክርስትናን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ትውፊት ጋር የማይጋጩ፤ ያላትንም ሀብት የማያጠፉ ጥበባትን ተጠቅመውባቸዋል።

ለምሳሌ፤ሠዓልያን ሥዕለ ቅዱሳንን ሲስሉ ቤተ ክርስቲያን በቃልና በጽሑፍ ያቆየችውን መሠረት አድርገው ገለጡት እንጂ የራሳቸውን አመለካከትና ፍላጐት ተጠቅመው ትውፊቱን በመሻር ልብወለድ ሥዕል አላቀረቡም።

ቋንቋ:- በዚያ ዘመን የዓለም ቋንቋ ተደርጐ ይሠራበት በነበረው የግሪክ ቋንቋ ቤተ ክርስቲያን ተጠቅማበታለች። ነገር ግን ሐዲስ ኪዳንን ወደ ግሪክ ቋንቋ ስትተረጉም፤ በግሪኩም ቋንቋ ስትጠቀም የዕብራውያንን ባህል ለቅቃ ወደ ግሪኩ ባል አልጠቀለለችውም።

ለምሳሌ፤ በዮሐ.10፥1–5 የምናገኘው ዐንቀፀ አባግዕ:-

‹በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ ይከተሉኝማል› በሚለው በጎች እረኛውን የመከተሉ ባሕል የምሥራቃውያን እንጂ የግሪካውያን አይደለም። ነገር ግን የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ነው።

የትውልድ ዕድገት አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ እስካልሆነ ድረስ ትውፊት ከቴክኖሎጂ ጋር አይጋጭም። ቴክኖሎጂ ባስገኘው ቴፕ ቅዳሴያችንን በድምፅ ቀርፀን ለተተኪው ትውልድ እናስቀምጥበታለን እንጂ የቴክኖሎጂ ውጤት ነው፤ የሰው ኃይልና ጊዜ ይቆጥባል ብለን በካህናቱ ምትክ የቅዳሴ ካሴት ቴፕ ውስጥ አስገብተን በሰንበት ጠዋት አናስቀድስም።

ቴክኖሎጂን ተጠቅመን በቀላሉ ጧፍ ለመሥራትና ለአብያተ ክርስቲያናትም በቶሎ ለማዳረስ የሚያስችለንን መንገድ እንቀይሳለን እንጂ ጧፍን በእጅ ባትሪ አንቀይረውም።

የዕድገት ምንነት በክርስቲያናዊ አመለካከት፣ በነዚህ ጥቂት ምሳሌዎች እንኳን በቁንፅሉ ሳይገባን አይቀርም። አለበለዚያ ትውፊታችንን አስጥሎ፣ ታሪክ አልባ፣ አባት አልባ፣ ቅርስ አልባ የሚያደርገንን ውድቀት እንጂ ዕድገት አንለውም።

## ትውፊትና አፈ ታሪክ

በአንዳንድ ምሁራን ዘንድ ትውፊትን ከአፈ ታሪክ ጋር መቀላቀሉ እየተለመደ መጥቷል። ሁለቱ ግን የምሥራቅና ምዕራብ ያህል ይለያያሉ።

አፈ ታሪክ (Legend) የአንድ ሕዝብ የሥነ ጽሑፍ መነሻው የሆነ የኪነ ጥበብ (Art) ዘርፍ ነው። ስለሚያያቸው፣ ስለሚሰማቸውና ስለሚያጋጥሙት ነገሮች ማንነት፣ ታሪክና ሂደት አንድ ሕዝብ አፈታሪክ ይናገረዋል። እውነትም ፈጠራም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የሕዝብ ቅርስ ነውና ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገራል።

የግሪክና የሮማ አማልክት ታሪክ፣ የሞት፣ የትዳር ፍቺ፣ የበቅሎ መካን መሆን፣ የሰማይ መራቅ – ምክንያት የሚገለጥባቸው አያሌ አፈታሪኮች ይገኛሉ።[1]

ትውፊት ግን ከነዚህ ይለያል። ለምሳሌ የእነዚህን አፈታሪኮች ባለቤት የሆነውን ሕዝብ የምንለየው በትውፊት ነው። ምክንያቱም ልኛ ‹አሉ እነ እገሌ› ተብሎ የሚተረክልን ከአያት ከቅድመ አያት የተወረሠውን መሠረት በማድረግ ነውና ራሳቸው አፈታሪኮች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት በትውፊት ነው። ለዛቸው፣ ቃናቸው፣ ሥነ ጽሑፋዊ ውበታቸው ተጠብቆ።

በትውፊት አማካኝነት አፈታሪኮች፣ ተረቶች፣ አባባሎች፣ ሥነ ቃሎች ወደ ተከታዩ ትውልድ ይተላለፋሉ። ክርስቲያናዊው ትውፊት ደግሞ ከነዚህ ሁሉ ይበልጣል። ያለፉትን አበው መንፈሳዊ

---

[1] Oxford English Dictionary



ኑሮ፣ ባሕል፣ ሥርዓት፣ ታሪክ እና ገድል ያቆየናል። እኛም ክርስትናን ተቀባዮች እንጂ ጀማሪዎች አይደለንምና ተቀብለን አባቶቻችንን እንመስልበታለን።

## ክርስቲያናዊ ትውፊት

## በዓለም መድረክ

እስከ 451 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያን መለያየት ድረስ በቤተክርስቲያን የነበረው ክርስቲያናዊ ትውፊት አንድ ወጥ ነበር። ለዚህም ነው እስከዚህ ዘመን የነበሩ አበው ቅዱሳን በመላው ዓለም ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በዓላቸው የሚከበረው:-

ነገር ግን በ5ኛው መ/ክ/ዘ በሮማ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሥልጣን ጥማት የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ስትከፋፈል ከግሪክ ጀምሮ ወደ ምዕራብ የነበሩት ምዕራባውያን ሲባሉ ከዚያ መለስ ያሉት ደግሞ ምሥራቃውያን ተባሉ።

ምሥራቃውያኑ የአባቶቻቸውን ትውፊት በመጠበቃቸው በምዕራባውያኑ ተጠሉ። ምዕራባውያኑ ደግሞ በዘመናቸው ከነበሩት የሮማ ነገሥታት ጋር የመቀራረቡን ዕድል ተጠቅመው ቤተ ክርስቲ ያናቸውን ታላቅ ያደረጉ መስሏቸው በሥጋዊ ድሎትና ፍልስፍና በመምራት ከእውነተኛው ትውፊት ራቁ።

## የምዕራባውያን ትውፊት

እስከ 5ኛው መ/ክ/ዘ ድረስ የነበረው ትውፊታቸው ከምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተመሳሳይ ነበረ ለማለት ይቻላል። በዚህም የተነሣ ከምሥራቃውያኑ ጋር የሚያመሳስሉዋቸው ጥቂት ነገሮች ዛሬም ይገኛሉ። ለምሳሌ

- በዓላተ ቅዱሳን
- የአጽዋማት ቀናና
- የገዳማት ሥርዓት
- ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን (በአንዳንዱ)
- ምልጃ ቅዱሳን፣ ወዘተ.

ከ5ኛው መ/ከ/ዘ በኋላ ግን ለሥልጣን ሲሉ በፈጠሩት እልክ በምሥራቃውያኑ ላይ ጥላቻ ስላደረባቸው ከኦርቶዶክሳዊት መንገድ ራሳቸውን ለዩ። በዚህ የተነሣ ትውፊታቸው የራሱን መንገድ መከተል ስለጀመረ ዛሬ የምዕራባውያን ትውፊት (Western Tradition) በመባል ይጠራል።

## የምሥራቃውያን ትውፊት

የምሥራቅ አበው በአብዛኛው የሐዋርያት ደቀ መዛሙርት ከነበሩት አበው የተማሩ ናቸው። ምክንያቱም:-

1. ከ12 ሐዋርያት አብዛኛዎቹ ያስተማሩት፣ በሰማዕትነትም ያረፉት በዚህ ሥፍራ ነው።
2. ለዕብራውያን ትውፊት የቀረቡ በመሆናቸው (ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከዕብራውያን የወረሰችው ብዙ በጎ ትውፊት አላት።)
3. ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው እና የመጀመሪያዎቹ ጥንታውያን የክርስትና ት/ቤቶችም የተቋቋሙት በዚህ ቦታ በመሆኑ የሐዋርያት ትምህርት፣ ሥርዓትና ትውፊት በሚገባ ተጠብቆ ደርሶዋቸዋል።

በ451 ዓ.ም በደረሰው የክርስቲያኖች መለያየት ከሮማ ቄሳሮች ጋር በገጠሙ የሮማ መለካውያን አበው የተነሣ መከራ፣ ስደት፣ መንገላታት፣ ከመንበራቸው መሰደድ፣ መታሠር ቢያጋጥማቸውም ምሥራቃውያኑ ሕይወታቸውን እንጂ ትውፊታቸውን አላጡም።

በ6ኛው መ/ክ/ዘ በዓረቢያ በረሃ የተጀመረው እስልምና በዘመኑ የነበረውን የክርስቲያኖች መለያየት በመጠቀም በመካከለኛው ምሥራቅ ባለ በሌለ ኃይሉ ሲዘረጋ፣ የምዕራቡ ዓለም ክርስቲያን መሆናቸውን ዘንግተውት በችልታ ሳይረዱዋቸው ቀሩ። ምሥራቃውያኑ ደግሞ የምዕራቡ ዓለም ተጽዕኖ፣ መከራና ስቃይ አድካሚዎቸው በዓረቡ ዓለም ቢወረሩም ብዙ ቅርሶችን እና ታሪካዊ ቦታዎችን ቢያጡም፤ በየበረሃው፣ በየፍርኩታው፣ በየገዳሙ የአበውን ትውፊት ጠብቀው አቆይተውናል።



ምዕራባውያኑ በ16ኛው መ/ክ/ዘ ማርቲን ሉተርና ተከታዮቹ ባስነሡት ተቃውሞ የተነሣ ብዙ የአበው ትውፊቶችን ለሥልጣኔ እያሉ ሲተው ምሥራቃውያኑ ግን ምንም ባይመቻቸው፣ ባይደላቸውና መንገዱ ሁሉ የሰማዕትነት ጉዞ ቢሆንባቸውም ማንነታቸውን ግን አልዘነጉም።

## ትውፊትና ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያናችን ለክርስቲያናዊ ትውፊት ታላቅ ቦታ ትሰጣለች። ጥንታዊት በመሆንዋ ከቀደምት አበው የወረሰችው አያሌ ነገር አላት። እነርሱም ሁለት ዓይነት ናቸው።

1. ቁሳውያን:- መጻሕፍት፣ ንዋየ ቅድሳት፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማት፣ አድባራት፣ ወዘተ የዚህ ክፍል ናቸው።
2. ቃላውያንና ራእያውያን:- ትውልዱ ከአባቶቹ በመስማት በማየት ለኑሮው የሚጠቀምባቸው ነገሮች ናቸው። ለምሳሌ ባሕሉ፣ ንግግሩ እና ሥርዓቱ ከአባቶቹ እያየ እና እየሰማ የሚቀበላቸው ናቸው።

እነዚህ ሁለቱ ሀብቶችዋ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት፣ የቤተክርስቲያን መሆናቸውም የሚረጋገጠው በትውፊት ነው። አዲሱ ትውልድ የኔ ናቸው፣ እውነተኛ ናቸው ብሎ የሚቀበለው አበው ስላስረከቡት በእነርሱ እጅ፣ በሕይወታቸው ስላያቸው እንጅ በላቦራቶር ፈትኖ አይደለም።

ለሚታየው ለሚዳሰሰው ነገር እንኳን ሳይቀር ማረጋገጫው ትውፊት ነው።

ለምሳሌ:- የቤተክርስቲያን መጻሕፍት እስከ 2ኛው መ/ክ/ዘመን ድረስ ተነጣጥለው ይገኙ ነበር።[2] ‹መጽሐፍ ቅዱስ› ተብለውም በአንድ ላይ አልተጠረዙም። ነገር ግን በዚያን ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ተጠቅመውባቸዋል። አበው የወንጌላውያንንና የሌሎችን መጻሕፍት ለይተው በስማቸው ጠርተዋቸዋል። ነገር ግን የጻፉዋቸው ሐዋርያት የኔ ናቸው ያላሉባቸው ብዙዎች ናቸው።

2 Tradition and Orthodoxy p.10

እነዚህ ሁሉ የግን እንደሆኑ የታወቁት ከቀደምት አበው በተገኙ ትውፊታውያን ማስረጃዎች ነው።

በተለይም በ2ኛው መ/ክ/ዘመን ግኖስቲኮች የተባሉ መናፍቃን ፍልስፍናን ከእምነት ሊቀላቅሉ ሲነሱ ቅዱሱን መጻሕፍት ለኑፋቄያቸው አላመች ቢሏቸው የራሳቸውን ድርሰት እያስመሰሉ በመጻፍ በሐዋርያት ስም ለመጠቀም በመሞከራቸው ቅዱሳን አበው ቅዱሳት መጻሕፍትን በቀኖና መወሰን ግድ ሆነባቸው።

እነዚህ መጻሕፍት በቀኖና ሲወሰኑና መጽሐፍ ቅዱስ ተብለው ሲጠሩ በላያቸው ላይ የሐዋርያት ፊርማና ማኅተም አልነበረባቸውም። ለማንነታቸው ማረጋገጫው የቤተ ክርስቲያን አበው ትውፊት ነበር። በዚያን ዘመን የነበሩ አበው የመጻሕፍትን ቀኖና ሲደነግጉ በትውፊት ያገኙአቸውን እንጂ ልብ ወለድ የግኖስቲኮች ድርሰቶችን አልቀላቀሉም።[3]

እንግዲህ ትውፊት ለቤተ ክርስቲያን ጉዞ ከጥንት ጀምሮ የእምነትዋ፣ ሥርዓትዋና ባሕልዋ ማረጋገጫ፣ መገለጫና ማስተላለፊያ መንገድ በመሆን አገልግሎዋል ማለት ነው። አባታችን ቅዱስ ቄርሎስ ‹ሃይማኖት ርትዕት እንተ ሐዋርያት ትውፊት› በማለት እንደ ተናገረው የሐዋርያት ውርስ የሆነች ሃይማኖታችንን የተረከብንበት እና የምናስረክብበት መንገዱ ትውፊት ነው። ያለበለዚያ የክርስትናው ወንዝ መንገድ ላይ ይቆማል።

## ትውፊትና ቅዱሳት መጻሕፍት

ትውፊት ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የሚጋጭ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ። ነገር ግን ደም ከደም ሥር ጋር እንደማይጋጨው ሁሉ እነርሱም አይጋጩም። ምክንያቱም:-

1. ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስን ያገኘንበት መንገድ ነው። አበው መጽሐፍ ቅዱስ ይኼ ነው ብለው ባያስረክቡን ኑሮ ከየት ይመጣ፤ ይህ ትውልድስ በምን ያውቀው ነበር? ለማግኘት የቻልነው አበው ስላቆዩን ቤተ ክርስቲያንም ስላረጋገጠችልን አይደለምን?

3 Ibid p.21



2. ትውፊት የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እንዳይፋለስ ይጠብቃል። አበው መጻሕፍትን ሲያስረክቡን የደራሲውን ገድል፣ የተጻፈበትን ባሕል፣ የመጻሕፍቱን ትርጓሜ ከምንጩ የቀዱትን ጭምር ነው። ይህም ማንም በየትም ዘመን ተነሥቶ የራሱን ሀሣብና ፍልስፍና በመጨመር የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል እንዳያጣምም አድርጎታል።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የምናገኛቸው ትርጓሜያት ጥንት አበው (እነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ቄርሎስ፣ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ...) ወዘተ. ያስተማሩንን እንጂ አዲስ ጥናት አደረግን ብለን በየዘመናቱ በሥጋዊ ምርምር የተራቀቅንበትን አይደለም።

ለምሳሌ በሉቃ.10፥29–37 የምናገኘውን የሩኅሩኅ ሳምራዊን ታሪክ በመጀመሪያው መ/ክ/ዘመን ከሐዋርያውያን አበው መካከል የነበረ አባት የተረጐመውን በ2ኛው መ/ክ/ዘመን የነበረው ሄሬኔዎስም ደግሞታል።[4] ይህ የእነርሱ ትርጓሜ ሳይዛባ፣ ሳይፋለስ በጥበበ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ዛሬም ይገኛል።

ወደ ኢያሪኮ የወረደው ሰው – አዳም፤ ኢየሩሳሌም – ገነት፤ ኢያሪኮ፥ ዓለም፤ ወንበዴዎቹ – አጋንንት፤ ርኅሩኅ ሳምራዊ – ጌታ መሆኑን እነርሱ የተረጐሙት በኛም ዘመን አለ።[5]

- 3 ትውፊት ቅዱሳት መጻሕፍትን ያብራራል።

ቅዱሳት መጻሕፍትን ቤተ ክርስቲያናችን ብቻቸውን አላገኘቻቸውም። አላስረከበችንምም። መጻሕፍት ‹ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እናምን ዘንድ› የሚያስችለንን ያህል ከባሕር በጭልፋ አቀረቡልን እንጂ ትምህርተ ክርስትናን አላጠቃለሉልንም። ስለዚህም በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፈው ግልፅ ያልሆኑ፣ የተጓደሉ ታሪኮች ለማይመስሉ ክፍሎች በትውፊታችን ያገኘናቸው ትምህርቶች ማብራሪያዎቻቸው ናቸው።

ትውፊት ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጠበቅ ከማውረስ በስተቀር የሚያዛባ የሚያፋልስ ምንም መንገድ የለውም። እንዲያውም ዛሬ

4 Origen Hom. Wc 34
5 ትርጓሜ ወንጌል ገ 328–29

ዓለም እርስ በርሱ በእምነት እየተለያየ የመጣው ትውፊቱን ትቶ በፍልስፍናው በመመራቱ ነው።

## ትውፊት በዘመነ ሕገ ልቡና

ትውፊት አበው የጽሑፍን ሕግ ከማግኘታቸው በፊት ሥርዓተ አምልኮዋቸውን ለትውልድ ያወረሱበት ብቸኛው መንገድ ነበር።

የሕግ መጻሕፍት የተጻፉት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት 1400 ዓመት አካባቢ ነው። ከዚህ ዘመን በፊት በምድር ላይ የነበሩ ቅዱሳን አበው እግዚአብሔርን አገልግለው መንገዳቸውን ከእርሱ ጋር አድርገው (ፍጹምና ጻድቅ) ተብለው ክብር በቅተዋል። እነዚህ ቀደምት አበው ከአባቶቻቸው ሥርዓተ አምልኮን የተቀበሉትና እነርሱም በፋንታቸው ለልጆቻቸው ያወረሱት በትውፊት ነው። ምክንያቱም በዚያ ዘመን ስለ ነገረ እግዚአብሔርና ሥርዓተ አምልኮ የተጻፉ መጻሕፍት አልነበሩምና። ለምሳሌም:-

*ሥርዓተ መሥዋዕት*

የመሥዋዕት ሥርዓት የተሠጠው ለሊቀ ነቢያት ሙሴ በ1400 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ነው። ነገር ግን ከዚህ ዘመን 4000 ዓመት አስቀድሞ የነበሩ አቤልና ቃየል መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ማቅረባቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ዘፍ.4፥3–5። በዚያን ዘመን ስለዚህ ሥርዓት ትምህርት የሚሰጡ መጻሕፍት አልነበሩም። እነዚህ ሰዎች ከየት ተማሩት? (ገድለ አዳም) የተሰኘው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ አባታችን አዳም ከገነት በተባረረ ጊዜ በእግረ ገነት መሥዋዕት መሠዋቱን ይነግረናል። የአዳም ልጆችም ይህንን ሥርዓት ከአባታቸው በትውፊት ወርሰው ተጠቅመውበታል።

በዘመነ ኖኅ ደግሞ የዚህን ትውፊት ያለማቋረጥ መቀጠል የሚያመለክት ታሪክ እናገኛለን።

ጻድቁ ኖኅ ከመርከብ በወጣ ጊዜ «ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያውን ሠራ፤ ከንጹሕም እንስሳ ሁሉ ከንጹሐን ወፎችም ሁሉ ወስዶ በመሠዊያውም ላይ መሥዋዕት አቀረበ።» ዘፍ.8፥20 ይላል።



ሀ. መሠዊያውን ሠራ:- አባታችን ኖኅ የምሥዋዑን (መሠዊያን) አሠራር ከየት ተማረው? ከአባቶቹ ከነ አቤል በትውፊት ያገኘው ትምህርት ካልሆነ በቀር! በዚያን ጊዜ በአሪት መጽሐፍት ላይ እንደተዘረዘረው ያለ የመሠዊያን አሠራር የሚገልጥ መጽሐፍ አልነበረም።

ለ. መሥዋዕት:- ከአቤል እስከኖኅ ያለው ዘመን 1400 ዓመት ነው።[6] ነገር ግን ለልዑል እግዚአብሔር መሥዋዕት የማቅረቡ ሥርዓት ሳይቋረጥ ለጻድቁ ኖኅ የደረሰው በትውፊት ነው።

ሐ. ንጹሑን ለእግዚአብሔር ማቅረብ:- አቤል (ንጹሑ እግዚአብሔር ንጹሕ መሥዋዕት ይገባዋል) በማለት ከበጎቹ ንፁሑን እንዳቀረበ ሁሉ ኖኅም ይህንን ደገመው። ይህንንም ትምህርት ከጻድቁ አቤል ያገኘው በትውፊት ነው። ምክንያቱም ንጹሕ የሆነውንና ያልሆነውን እንስሳ የመለየት ሥርዓት ከእርሱ በኋላ 2600 ዓመት ዘግይቶ ለሊቀነቢያት ሙሴ የተሰጠ ነበርና!

የእግዚአብሔር ቤት

አባታችን ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ሸሽቶ ወደ አጎቱ ሀገር ወደ ሶሪያ ሲኮበልል እግዚአብሔር በፍኖተ ሎዛ በራእይ ተገለጠለት። ያዕቆብም ከዕንቅልፉ ተነሥቶ — በእውነት እግዚአ ብሔር በዚህ ሥፍራ ነው እኔ አላወቅሁም ነበር አለ። ፈራ እንዲህም አለ:- ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራል! ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም። ይህም የሰማይ ደጅ ነው። ዘፍ.28፥17። ስለ እግዚአብሔር ቤት በሕግ መጻሕፍት ትምህርት የተሰጠው በዘመነ ሙሴ (በደብተራ ኦሪት) በኋላም በዘመነ ሰሎሞን (ቤተ መቅደስ ሲሠራ) ነው። ነገር ግን አባታችን ያዕቆብ (የእግዚአብሔር ቤት፣ የሰማይ ደጅ) ብሎ እንዴት ለመናገር በቃ!

አባታችን አዳም እንደ መላእክት ሥርዓት በገነት ውስጥ ከእግ ዚአብሔር ጋር የሚገናኝባት በአት ነበረችው። እርሱና እግዚአብሔር

6 በዘፍ.5፥1–31 ያሉትን አበው ዕድሜ ይቁጠሩ።

የሚገናኙባት። ይህቺን ትምህርት ለልጆቹ አውርሶአቸዋል – በትውፊት። ለዚህም ነው ቅዱስ ያዕቆብ ያንን ራእይ ባየ ጊዜ ‹የእግዚአብሔር ቤት› በማለት የተናገረው።

አባታችን ያዕቆብ ግልጾ ከዕንቅልፉ በተነሣ ጊዜ ተንተርሶት የነበረውን ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው፤ በላዩም ዘይትን አፈሰሰበት። ያዕቆብም ያንን ሥፍራ ቤቴል ብሎ ጠራው ዘፍ.28፥18።

ለያዕቆብ አባታችን በቅብዐተ ዘይት (ሜሮን) ማክበርን ማን አስተማረው? ከመጽሐፍት? አልነበረም። በትውፊት ከአባቶቹ ያገኘው እንጂ! ዛሬ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደምናደርገው ድንጋይ አቁሞ በዘይት አክብር – ቤቴል (የእግዚአብሔር ቤት) ብሎ ጠራው። በቤተ ክርስቲያናችንም በኤጲስ ቆጶሱ የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ በቅብዐተ ሜሮን ክብር ቤተ ክርስቲያን (የእግዚአብሔር ቤት) ትታነፃለች። ያ የቅዱስ ያዕቆብ ሥርዓት 4000 ዘመናትን አልፎ ለእኛም በትውፊት መድረሱ አይደንቅም!

አባታችን ያዕቆብ ጉዞውን ወደ ሶርያ ከመቀጠሉ በፊት ‹እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፤ በምሄድባትም በዚህች መንገድ ቢጠብቀኝ፤ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ፤ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ፤ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል። ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል። ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ።› ዘፍ.28፥20–22 በማለት ተስሎ ነበር። ለመሆኑ አባታችን ያዕቆብ ከአሥር አንድ አሥራት በኵራትን የማውጣትን ሥርዓት ከማን ወረሰው? ወደኋላ ተመልሰን ቀደምት አበውን ስንመለከት እንዲህ የሚል ነገር በጻድቁ አቤል ታሪክ ላይ ተጽፎ እናገኛለን። አቤልም ደግሞ ከበጉቹ በኵራትና ከሰቡ አቀረበ። ዘፍ.4፥3። ያዕቆብ የአሥራት በኵራትን ሕግ በመጀመሪያ አቤል ከዚያም በኋላ አያቱ አብብዙኃን አብርሃም መልከጼዴቅን በጉበኘ ጊዜ ከሁሉ አሥራትን ሰጠው። ዘፍ.14፥20 ተብሎ እንደተጻፈ አባቶቹ ያደረጉትን ወርሶ እርሱም ተጠቀመበት። ትውፊት ማለት እንግዲህ ይህ ነው። ከቀደሙ አበው መውረስ።



## ትውፊት በቤተ አይሁድ

ቤተ እሥራኤል የአበው ዘመን ትውፊት ወራሾች ናቸው። በኋላም አሥሩ ነገድና ሁለቱ ነገድ በ922 ዓመት ከጌታችን ልደት በፊት ሲለያዩና አሥሩ ነገድም በልዩ ልዩ ምክንያት ኃይላቸው ተዳክሞ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ክብራቸውን ሲያጡ ቤተ አይሁድ የቤተ እሥራኤል ትውፊት ወራሾች ሆነዋል። ለምሳሌ:-

የቅዱሳት መጻሕፍት ትውፊት

የብሉይ ኪዳን ጸሐፍት እሥራኤላውያን እንደመሆናቸው መጠን ቤተ ክርስቲያንም የተቀበለችው ከእነርሱ ነው። በቤተ አይሁድ የነበሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጠረዙበትና በቃል የተነገሩበት ዘመን የሚለያይበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ

የሙሴ ጸሎት:- ሊቀ ነቢያት ሙሴ ይህንን ያስተማረው 1400 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ሲሆን የተጻፈው ግን ከመዝሙረ ዳዊት ጋር በ1000 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት አካባቢ ነው። (መዝ.89) እስከዚህ ዘመን ድረስ በትውፊት ይቀባበል ነበር።

የጠቢቡ ሰሎሞን ምሳሌዎች:- ጠቢቡ ሰሎሞን የተናገራቸውን ምሳሌዎች የሰበሰቡዋቸው የተለያዩ ሃገሮች ሰዎች ናቸው። ለምሳሌ ከምዕራፍ 25 በኋላ ያሉትን የይሁዳ ንጉሥ የሕዝቅያስ ሰዎች የቀዱዋቸው ናቸው። ምሳሌ 25፥1። እነዚህም በሕዝቡ ዘንድ በትውፊት ሲተላለፉ የቆዩ ናቸው።

ቤተ አይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠብቀው ለቤተ ክርስቲያን አቆይተዋል። እነዚህ መጻሕፍት በአይሁድ የአኗኗር ሁኔታ መለያየት የተነሣ የተለያዩ ነበሩ። አይሁድ በልዩ ልዩ ምርኮ ተወስደው ስለነበር በዝርወት በልዩ ልዩ ሃገሮች ይኖሩ ነበር። ከነዚህ የተረፉትም መከራውን ችለው በሀገረ ፍልስጥኤም ይቀመጡ ነበር። አንዳንድ መጻሕፍት በዝርወት ባሉት እጅ ተገኝተው በሀገራቸው በነበሩት እጅ አይገኙም፤ ሌሎች ደግሞ በሀገሬው እጅ እያሉ በዝርወት በነበሩት እጅ አልነበሩም። ነገር ግን በንጉሥ በጥሊሞስ አሳሳቢነት ብሉይ ኪዳን በ2ኛው መ/ክ/ዘመን ከጌታ ልደት በፊት

2. የባቢሎናውያን – በ5ኛው መ/ክ/ዘመን የተጠረዘ። ሁለቱ ጥራዞች በትርጓሜ ስልት አንድ ሲሆኑ በይዘት ግን የሚለያዩበት ጊዜ አለ።

### ቶሴፍታ

ቶሴፍታ ማለት (ተጨማሪ) ማለት ሲሆን የመምህራን አይሁድን ሐሳብና አመለካከት ያቀፈ ነው።[10]

### ሚድራሺ

ሃይማኖታዊ ጽሑፎች የሚጠኑበት ክፍል ነው። በአይሁድ ትውፊት የታወቁት የዜና መዋዕል መጻሕፍት ምንጮች (2ዜና.13፥22፤ 24፥27) የሚገኙት በዚህ ነው። በዜና መዋዕልና በነገሥት መጻሕፍት ላይ የነገሥታትን ታሪክ ከተናገረ በኋላ:-

- የእሥራኤል ነገሥታት መጽሐፍ (1ዜና.28፥26)
- የይሁዳ ነገሥታት መጽሐፍ (ነገሥ. 15፥23)
- የያሻር መጽሐፍ (2ሳሙ.1፥18)

እነዚህን መጻሕፍት ይጠቅሳል። እንዲያውም የቀረው ነገር በነዚህ እንደተጻፈ ይጠቁመናል። አንዳንዶም ከእነዚህ መጻሕፍት ይወሰዳል። (2ሳሙ.1፥18) ይህም መጽሐፍ ቅድስ በሙሉ ተጽፎ እንዳላለቀ በትውፊት ለእኛ የደረሰ እጅግ ብዙ ነገር እንዳለ ያመለክተናል። እነዚህ መጻሕፍት በሚድራሺ የጥናት ክፍል በአይሁድ የትውፊት ት/ቤት ይጠኑ ነበር።

ሚድራሺ ሁለት ክፍል ነበረው

1. ሃላክሃ:- ተማሪው ለእምነቱ ቀናዒ እንዲሆን የሚማርበት፤ በመከራ፤ በችግርና በማይጠበቅ የዕለት ተዕለት አስቸጋሪ ሕይወት ውስጥ ሕገ ኦሪትን እንዴት መፈጸምና በእምነቱ ጽኑ ለአምላኩም ታማኝ መሆን እንዳለበት ምክር የሚገኝበት ክፍል ነው።

2. ሃጋዳህ:- የሙሴ መጻሕፍት ትረካዊ ምዕራፎችን (ታሪክ ነክ የሆኑትን) የሚያብራራ ሰፊና ጥልቅ የሆነ ስብከታዊ ክፍል ነው። ዋና ዓላማውም የተማሪውን ሕይወት ማነፅ ሲሆን ታሪኮችን፤ ምሳሌዎችን፤ አባባሎችን እና ሥነ ቃላትን ይዞአል።[11]

---

[10] Ibid p.36
[11] Ibid p.37



## የአይሁድ ትውፊት በጌታ ዘንድ

አይሁድ ከአባቶቻቸው የወረሱዋቸው ትውፊቶች ለብሉይ ኪዳን ጉዞዋቸው በእጅጉ ጠቅመዋቸዋል። ትውፊት ባይኖር ኑሮ ቃለ እግዚአብሔርን መማር፤ መተርጎምና ለተተኪው ትውልድ ትምህርታቸውን ማስተላለፍ ባልቻሉም ነበር።

ነገር ግን በኋላ ዘመን ከአባቶቻቸው በተቀበሉዋቸው ላይ የራሳቸውን ሥጋዊ ፍልስፍና እየጨመሩ ስለመጡ ጌታችን ደጋግሞ ወቅሶአቸዋል። ማቴ.15፥3፤ 7፥13። ይህም የአባቶቻቸውን እንዲጠብቁ በሥጋ ጥበብ ተመርተው፤ ከመንፈሳዊ ሕይወት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር የሚቃረኑ ወጉችን መጨመራቸውን እንዲተው እንጂ ትውፊታቸውን እንዲንቁ ማለቱ አይደለም። የአይሁድ የተቀደሰ ትውፊት በሐዋርያትም ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተላልፎአል። ሐዋርያት የአይሁድን ትውፊት ሐዲስ ኪዳንን አግኝተናል ብለው አልናቁትም በሚገባ ተጠቅመውበታል።

## ትውፊት በዘመነ ሐዋርያት

ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማሩትን ትምህርተ ክርስትና ለተተኪዎቻቸው ያስተማሩት በትውፊት ነው። የመጀመርያዋ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ የምትባለው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች እንኳን የተጻፈችው ከጌታችን ዕርገት በኋላ ከ10 ዓመታት በላይ ቆይታ ነው። በዚህ ዘመን ውስጥ ሐዋርያት ወንጌልን የሰበኩት በቃል፤ በተግባር በማሳየትና በሕይወታቸው ነው። ይህ ደግሞ ተተኪው ትውልድ ከአባቱ የሚወርሰው ትውፊት ነው።

ከዚህም በኋላ ቢሆን በመላዋ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ስትስፋፋ በቂ ቅዱሳት መጻሕፍት አልነበሩዋትም። ይህ ማለት ግን በቂ ክርስቲያናዊ ኑሮ አልነበረም ማለት አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከአበው ሐዋርያትና ከደቀ መዛሙርቶቻቸው ያዩትን፤ የሰሙትንና የተማሩትን ትውፊት ተቀብለው እነርሱም በመኖር ለትውልድ አወረሱት እንጂ።

ሐዋርያት በትምህርታቸው የአይሁድን የተቀደሰ ትውፊት ተጠቅመዋል።

ለምሳሌ:- ማቴ.2፥23 – ‹በነቢያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈፀም ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ ገብቶ ኖረ።› በ46ቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ትንቢታት ተጽፈዋል። ነገር ግን በእነዚህ መጻሕፍት ጌታ ‹ናዝራዊ ይባላል› የሚል ትንቢት የለም። ይህ ትንቢት ግን በሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ተጠቅሷል። ከየት መጣ? በቤተ ክርስቲያን ትውፊት እንደምንማረው ይህ ትንቢት በነቢያት ተነገር በምርኮ ጊዜ በጠፉት መጻሕፍት የነበረ ሲሆን መጻሕፍቱ ቢጠፉም በቃል ለሐዋርያት ደርሶአል።

ዕብ.12፥21 – ሙሴም እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጣለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበረ።

በኦሪት መጻሕፍት ውስጥ ሙሴ በደብረ ሲና ‹ፈራ ተንቀጠቀጠ፣ እፈራለሁ አለ› የሚል አልተጻፈም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግን ከአይሁድ ትውፊት ያገኘውን በመልእክቱ አሥፍሮታል።

2ጢሞ.3፥8 ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደ ተቃወሙት...

በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 7፥11 ላይ ሙሴን ለመቃወም የግብፅ ጠንቋዮች በፊቱ እንደተገዳደሩት ይነገረናል። ነገር ግን ‹የግብፅ ጠንቋዮች› ከማለት በቀር ሙሴ በኦሪት መጽሐፉ ስማቸውን አልገለጠውም። ቅዱስ ጳውሎስ ግን በትውፊት ያገኘውን ተጠቅሞ ‹ኢያኔስና ኢያንበሬስ› ብሎ ጠርቷቸዋል። በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት በሉቃ.16፥19 የሚገኘው ባለጠጋ ‹ነዌ› ይባል እንደነበር የታወቀውም በዚሁ ዓይነት መንገድ ነው።

ይሁዳ 8፥11 የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለሙሴ ሥጋ ሲከራከር ጌታ ይገሥፅህ አለው እንጂ የስድብን ቃል ሊናገረው አልደፈረም።

የኦሪት ዘዳግም የመጨረሻ ምዕራፍ ሙሴ በናባው ተራራ እንዳረፈና መቃብሩም እስከዛሬ እንደማይታወቅ ከመንገሩ በቀር ይህን የቅዱስ ሚካኤልንና የዲያብሎስን ክርክር አይገልጥልንም።



ሐዋርያው ይሁዳ ይህን ታሪክ ያገኘው የሙሴን ታሪክ ከሚናገረው (The Assumption of Moses) ትውፊታዊ መጽሐፍ ነው። እሥራኤል ሙሴን በጣም ይፈሩት ነበር። ተአምር ሲያደርግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር፣ ፊቱ እንደ ፀሐይ ሲያበራ ስላዩት አምላክ ነው ብለው ለማመን ደርሰው ነበር። እንዲያውም መከራ ሲገጥማቸው፣ እግዚአብሔር ሲቆጣባቸው፣ ወደ አምላክህ ጸልይልን ነበር የሚሉት። ሊቀ ነቢያት ሙሴ የዋህ ስለነበር ሀገረ ከነዓንን ለማየት ወደናባው ተራራ በወጣ ጊዜ ሁለት መላእክት በአረጋውያን ተመስለው መቃብር ሲቆፍሩ ቢያይ ለማችሁ ብሎ መቆፈሪያውን ተቀበላቸው። እነርሱም በመጨረሻ ‹ሰውየው ቁመቱ በአንተ ልክ ነውና እስቲ ገብተህ ለካልን› አሉት። እርሱም በየዋህነት ጉድጓዱ ውስጥ ገብቶ እንደተኛ እንደ ዕንቅልፍ አሸልቦት በዚያው ዐረፈ። መላእክትም ቀበሩት። እግዚአብሔር የሙሴን መቃብር ከእሥራኤል የሠወረበት ምክንያት ነበረው። ሙሴን በጣም ይወዱትና ያከብሩት ስለነበር ፍቅር ስቧቸው እናመልካለን ብለው በመነገት በመቃብሩ ሥርዓት አምልኮዋቸውን እንደይፈፅሙ ነው።

ነገር ግን ጠላት ዲያብሎስ አርፎ ስለማይቀመጥ ሊያሳያቸው በመነሣቱ ቅዱስ ሚካኤል ተቃወመው። በመጨረሻም ከእራሱ ከዲያብሎስም ሠወረበት።[12]

ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ የጠቀሰው ይህንን ነው። ይህም የሚያሳየን አበው ሐዋርያት ገድላትንና ድርሳናትን አክብረው መቀበላቸውን ሲሆን እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የእነርሱን አርአያ ተከትላ ገድላትንና ድርሳናትን ትቀበላቸዋለች።

ራእ.2፥14 ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ በእሥራኤል ልጆች ዘንድ ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበለዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ካንተ ጋር ስላሉ...።

በኦሪት ዘኁልቁ የምናገኘው የበለዓም ታሪክ እሥራኤልን በለዓም በመመረቁ የተነሣ ከባላቅ ጋር ተጣልተው መለያየታቸውን ነው። ይህን የሐንስ በራእዩ፣ በሌላ ቦታ ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስ

---

12 በተጨማሪ:- ሦስቱ ሐዲሳት የይሁዳ መልእክት ትርጓሜ፣ ዜና አይሁድ፣ ዜና ሕይወቱ ወሞቱ ለሙሴን ተመልከት።

(2ጴጥ.2፥13) እና ይሁዳ (ይሁዳ.11) የጠቀሱትን ታሪክ በኦሪት ዘኁልቁ እናገኘውም። እነዚህ ሐዋርያት ግን ከአይሁድ ትውፊት አግኝተው ጠቅሰውታል።

በለዓም ለመርገም ሲወጣ መልአከ እግዚአብሔር መንገድ ላይ ጠብቆ መርገሙን ወደ በረከት ቀየረበት። ዘኁ.22፥21–35። እሥራኤልንም መረቀ። ባላቅ ይህን ሲሰማ በእጅጉ አዘነ። በለዓም ግን እንዲህ ብሎ መከረው እሥራኤል ሊወሩህ ሲመጡ ለጣዖት መሥዋዕት ሠውተህ አስተምሮ። በፊቱም ቆንጆጅት የሞዓብ ሴቶችን አሠልፍ። የእሥራኤል ጉብዛዝትም ቆንጆጅቱን ባዩ ጊዜ ልባቸው ይቀልጣል። ከኛ ጋር ተኙም ይሏቸዋል። ቆንጆጅቱም ‹አስተድግችሁ መሥዋዕተ ጣዖቱን ብሉልን› ይበሉዋቸው። ያን ጊዜ አምላክ እሥራኤል እግዚአብሔር ቀናተኛ ነውና በመቅሰፍት ይጨርስልሃል። አለው። ባላቅም እንደተባለው አደረገ። በዘኁ.25 የምናየው የ24000 እሥራኤላውያን እልቂት የተከሠተው በዚህ የተነሣ ነው።

እነዚህ ሠለስቱ ሐዋርያት የጠቀሱትን ታሪክ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ነው የምናገኘው።[13]

ከቅዱሳን ሐዋርያት ደቀ መዛሙርቶቻቸው ትምህርተ ወንጌልን በትውፊት ተቀብለዋል።

ብዙ ሰዎች ወንጌልና መልእክታት ከተጻፉ ወዲያ ትውፊት የቀረ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ቅዱሳን ሐዋርያት ወንጌልና መልእክታትን ሲጽፉ ሌሎች ትውፊታዊ መረጃዎችንም ተጠቅመዋል።

1ቆሮ.11፥34 የቀረውን ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሄደ ጊዜ የደነገጋቸው ምንድናቸው? እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ዛሬም የምንቀበላቸው የምሥጢራትን አፈፃፀም፣ የቤተ መቅደስ ሥርዓት፣ የቁርባን (የምሥጢር ቤት) ሥርዓት ሲሆኑ ለሁሉም በግልጥ የማይነገሩ የሥርዓተ ክህነት ትምህርቶች ናቸው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በትውፊቷ ተቀብላ ትጠቀምባቸዋለች። የቆሮንቶስ ሰዎችም እነዚህን

13 ክፍል-ሐ [illegible] ተመልከት



ትምህርቶች (ድንጋጌዎች) ከቅዱስ ጳውሎስ ያገኙዋቸው በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን አይተው፣ ተምረው እና ወርሰው ነው።

ቲቶ.1፥5 ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማው እኔ አንተን እንዳዘዝሁህ...

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቲቶ የሰጠው የማደራጀት ትዕዛዝ አልተገለጠም። ቲቶ የቀርጤስ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ በቅዱስ ጳውሎስ ተሹሞ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ በዚያ ሊሠራው ስለሚገባው ሥራ ‹ሥርዓተ ኖሎትን› ከጻፈለት በኋላ ነበር ይህን ቃል የተናገረው እነዚያ የጳጳሳትን አገልግሎት የሚመለከቱ የቅዱስ ጳውሎስ ትዕዛዛት የሥርዓተ ኖሎት ትምህርቶች አካል ሲሆኑ፤

እነዚህን ቲቶ የተቀበለው ከአባቱ በማየትና በመማር በትውፊት ነው።

2ዮሐ.12 እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ በወረቀትና በቀለም ልጽፈው አልወደድሁም። ዳሩ ግን ደስታችሁ ፍፁም እንዲሆን ወደ እናንተ ልመጣ አፍ ለአፍም ልናገራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

ይህ ቃል የተጻፈው ከኤጅያን ደሴቶች በአንዱ ትኖር ለነበረችው የነገሥታት ልጆች ምግዚት በሮምና ለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነበር። በዚህች ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ምእመናን እርስ በርስ ተለያይተው ስለነበር ቅዱስ ዮሐንስ ፍቅርን ከእርሱ አይተው እና ሰምተው በተግባር ይማሩ ዘንድ ስለወደደ ይህን ጻፈ። ምክንያቱም በትውፊት (ከሕይወት) የሚወረስ ነገር በደም ሥር ሠርፆ ኑሮ ሆኖ ስለማይለቀቅ ቅዱስ ዮሐንስ መርጦታል። የሰሙትን ቢያዩት ደስ ያሰኛልና ‹ደስታችሁ ፍፁም እንዲሆን› አላቸው።

3ዮሐ.13፥14:- ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበረኝ ዳሩ ግን በቀለምና በብዕር ልጽፍልህ አልወድም ነገር ግን ወዲያው ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ አፍ ለአፍም እንነጋገራለን።

ጋይዮስ በስደት ምክንያት የሚንከራተቱትን ክርስቲያኖች እየተቀበለ የሚያስተናግድ የዕንግዳ ፍቅር የነበረው ከታናሿ እስያ ከተሞች ባንዱ ይኖር የነበረ ደግ ሰው ነው። ዮሐንስ ዝናውን ስለሰማ በመልካም ምግባሩ ይበረታ ዘንድ ይህን ጻፈለት። ይህ ደግ ሰው

ከአበው ኑሮ! ሕይወትና ክርስቲያናዊ ሥርዓት አይቶ ሰምቶ ቢማር እጅግ መልካም እንደሚሆንለት ቅዱስ ዮሐንስ ስላወቀ በአካል ሊያገኘው በኑሮው (በትውፊት) ሊያስተምረው ወደደ።

2ተሰ.2፥13:- በቃላችንም ቢሆን ወይንም በመልእክታችን የተቀበላችሁትን ትውፊት (ወግ) ያዙ።

ቅዱሳን ሐዋርያት ትውፊታቸውን በቃልም በመልእክትም አስተላልፈዋል። ሁለቱም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን እኩል ቦታ ሊኖራቸው ስለሚገባ «ያዙ» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችን መክሯቸዋል። ምክንያቱም ትምህርቱ በጽሑፍም መጣ በቃል ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ጥቅም እኩል ነውና!

ሐዋርያት አባቶቻችን በወንጌል ያልተጻፈ! ነገር ግን በትውፊት ተጠብቀው የኖሩ የጌታ ትምህርቶችን በመልእክታቸው ገልጠዋቸዋል። ለምሳሌ:-

1ቆር.9፥14 ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲበሉ ጌታ ደንግጎአል።

1ቆር.7፥10 ቅዱስ ጳውሎስ የባልና ሚስትን ነገር ካስተማረ በኋላ ‹እኔ ግን አላዝም ጌታ እንጂ› በማለት ይደመድማል። የመጀመርያው ጥቅስ በወንጌላውያን አልሠፈረም። በትውፊት የተላለፈ የጌታ ትምህርት ነው። ሁለተኛው ጥቅስ ጌታ የባልና ሚስትን ነገር ባስተማረበት በማቴ.19፥1–12 ላይ የለም። ይህም ጌታ ተናግሮት በወንጌላውያን ሳይጻፍ በቃል የተላለፈ ነው።

የጌታችን ትምህርቶችና ሥራዎች ሁሉ በወንጌል ተጠቃለው አልተጻፉም።

ዮሐ.20፥30 – ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ።

ዮሐ.21፥25 ኢየሱስ ያደረገው ሌላ ብዙ ነገር ደግሞ አለ።

ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸው ይመስለኛል።

እነዚህ የጌታ ተአምራትና ትምህርቶች ዛሬ ቃል በቃል እየተወረሱ አልያም ደግሞ ተአምረ ኢየሱስን በመሰሉ መጻሕፍት



ተጽፈው ይገኛሉ። ለምሳሌ ጌታ ከ12 ዓመቱ – 30 ዓመቱ የት እንደኖረ፤ ምን እንደሠራ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም! ተአምረ ኢየሱስ ግን በሚገባ መዝግቦት ይገኛል። ከዚህም ሌላ ደግሞ ወንጌላውያን በአጭሩ የጻፉትን ትውፊት በሰፊው ያብራራዋል።

ዮሐ.12፥20–22 ጌታን እንዲያሳያቸው ፊልጶስን የጠየቁትና እንድርያስም ወደ መድኃኔዓለም ያቀረባቸው ግሪኮች! ከጌታ ጋር የተነጋገሩት ነገርና ለምንም እንደፈለጉት አልተገለጠም። በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ግን እነዚህ ሰዎች ከዑር (ኤዴሳ) ንጉሥ ከአብጋር ዑካማ ለጌታ የሚቀርብ ደብዳቤ ይዘው መምጣታቸው ይነገራል።[14]

ከዚህም ሌላ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ እስካረገበት ቀን ድረስ ለ40 ቀናት ያህል ለደቀ መዛሙርቱ እየተገለጠ አስተምሯቸው ነበር። ነገር ግን በዚህ ረዥም ጊዜ ያስተማራቸው ትምህርት ሙሉ በሙሉ በአራቱ ወንጌላት በወንጌላውያን አልተገለጠም። በቤተ ክርስቲያን ግን በመጽሐፈ ኪዳን ላይ ተጽፎ ይገኛል።

እንግዲህ በአጠቃላይ አበው ሐዋርያት ትውፊትን ተቀብለው ተጠቅመውበታል። ደቀ መዛሙርቶቻቸውም በፈንታቸው ከእነርሱ ወርሰዋል። ታድያ እነርሱ ያከበሩትን እኛ ልንንቀው አይገባም።

## ትውፊት በቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው

የሐዋርያት ትውፊት ተረካቢ የሆኑት ቀደምት አበውም ስለትውፊት አስተምረዋል። በአባቶቻቸውም ትውፊት ተጠቅመዋል። ጠብቀው ተንከባክበውም ለኛ አድርሰዋል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ተቀብለው ለኛ ያስረከቡንም በትውፊት ነው። እነዚህ አበው ስለ ትውፊት ከገለጡት መካከል ጥቂቱን እንመለከታለን።

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም (380–444) ‹ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን እነማን እንደ ሆኑ ተምረናል።› በማለት ቅዱሳት መጻሕፍት እነማን

14 ሙሉ ታሪኩን በሁለተኛው ክፍል በሐዋርያው ተግባር ታሪክ ላይ ተመልከት።

እንደሆኑ፣ ማን እንደጻፋቸው እና ለምን እንደተጻፉ፣ ለማወቅ የቻልነው በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ተጠብቆ ስላገኘነውና አበው ስላስረከቡን፣ ስለመሠከሩልንም መሆኑን ገልጦአል።

ቅዱስ ፓፒያስ (60–130 ዓ.ም):- የፍርግያ (ሄራፖሊስ) ሊቀጳጳስ የነበረ የሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ሲሆን ቀጥሎ ከሐዋርያውያን አበው ነው። ፓፒያስ ከፖሊካርፐስ ጋር አብሮ ከቅዱስ ዮሐንስ ተምሮአል። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት የሚባለው አውሳብዮስ እንደጻፈው ፓፒያስ ከሐዋርያት ከተማሩ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት ማጥናት ይወድ ነበር።

‹የሐዋርያት ደቀ መዝሙር የነበረ ሰው ወደ እኔ ሲመጣ የምጠይቀው ነገር ቢኖር እንድርያስ፣ ጴጥሮስ፣ ፊልጶስ፣ ቶማስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ወይንም ደግሞ ማቴዎስና ሌሎች ሐዋርያት ምን እንደተናገሩ፣ ምን እንዳስተማሩ ነው። ከተጻፉት ይልቅ ለኔ ሕያው ሆነው ዛሬ በተግባር የማያቸውና የምሰማቸው ትውፊቶች የበለጡ ናቸው።›[15] አባታችን ፓፒያስ የአባቶቹን ኑሮ፣ ሥርዓትና ጉዞ እየተመለከተ የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት ለመረከብና ለማስረከብ ይህን ያህል ይተጋ ነበር። ትውፊት ሕያው የሆነ ክርስትና ነውና፤ በኑሮ፣ በተግባር በሕይወት ተገልጦ የሚታይ። ይህንንም እውነታ የፖሊካርፐስ ደቀ መዝሙር የነበረውና በልጅነቱ ቅዱስ ዮሐንስ ፖሊካርፐስን ሲያስተምር የተከታተለው ሄሬኔዎስ እንዲህ ገልጦት ነበር።

ሄሬኔዎስ (130–200 ዓ.ም):- የልዮንስ ሊቀጳጳስ የነበረው ሄሬኔዎስ ከፖሊካርፐስ ጋር በሰርምኔስ ስላሳለፈው ነገር ሲናገር።

‹በዚህ ዘመን ኑሮዬ ይልቅ እነዚያ ቀናት ወለል ብለው ይታዩኛል። ከልጅነቴ ጀምሮ የተማርኳቸውና በሕይወቴ ሠርፀው ዘወትር የሚኖሩ እነዚያ ነገሮች። አባቴ ቅዱስ ፖሊካርፐስ የት ቦታ ተቀምጦ እንዳስተማረ፣ ዛሬ ድረስ የቦታው ትዝታ ከአእምሮዬ ሥዕሉ አልጠፋም። እንዴት ይወጣና ይገባ እንደነበር፣ የአኗኗሩ ሁኔታ፣ አቀራረቡ፣ ለምእመናን የመከራቸው፣ ያስተማራቸውና

15 Eusebius HE 3:39



የነሠፀባቸው ቃላት፣ ከሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ጋር ምን እንደ ተነጋገሩ ጌታችንን በአካል ካዩት ሐዋርያት የተማራቸው ትምህርቶች። እነርሱ የነገሩትን ሁሉ እንዴት ያስታውሳቸው እንደነበር። ስለጌታችን ከአንደበታቸው የሰማቸው ነገሮች ሁሉ...ምንም እንኳን በዚያ ዕድሜየ ከዐቅሜ በላይ ቢሆንም በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት እንዴት በታላቅ ጉጉት እከታተላቸው እንደነበር:- ዛሬም በአእምሮዬ ይመላለሳሉ። በወረቀት አልጻፍኳቸውም፣ በልቤ ግን ቀርጬ ቸዋለሁ። ሁል ጊዜም በትክክል እመረምራቸዋለሁ።[16] አባታችን ሄሬኔዎስ ከአባቱ ከፖሊካርፐስ፣ እርሱንም ካስተማሩት ሐዋርያት ያገኛቸው በኑሮ፣ በሕይወት የሚገለጡ፣ ግን ያልተጻፉ ትምህርቶች በአእምሮው ተከትበው፣ በልቡ ሠርፀው እንደሚኖሩ፤ የሐዋርያት ትምህርቶች በመሆናቸውም እንደሚመራባቸው ጽፎአል።

ቅዱስ ሲፕሪያን (200–258 ዓ.ም):- በቱኒዚያ የተወለደውና የካርቴጅ ሊቀ ጳጳስ የነበረው ሲፕሪያን ‹እውነተኛው የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜና ዶግማ (ትምህርተ ሃይማኖት) የሚገኘው በእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው። የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ርቱዕ የሆነው የአበው እምነት እንዳይበረዝ የሚጠብቅ አጥር ነውና።[17] በማለት አስተምሮናል። እንደ ሲፕሪያን ትምህርት እውነተኛው እምነትና የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም የሚገኘው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ነው። የቤተ ክርስቲያኗን ትውፊት ንቀው እያቃለሉ ሃይማኖት አለኝ ለማለት አይቻልም።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (330–395 ዓ.ም):- የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ወንድም፣ የኑሲስ ሊቀ ጳጳስና ከቀጰዶቅያ አበው አንዱ የሆነው ጎርጎርዮስ እንዲህ ብሏል ‹ለምናስተምረው ትምህርት እውነተኛነት ማስረጃው ከቅዱሳን ሐዋርያት በደቀ መዛሙርቶቻቸውና አሠረፍኖታቸውን በተከተሉ ቅዱሳን አበው በኩል ያገኘነውና የወረስነው ትውፊት ከኛ ጋር መኖሩ ነው።›[18] በቅዱስ ጎርጎርዮስ ትምህርት መሠረትም አንድ ሰው የአበውን ትውፊት ሳይቀበል ርቱዕ የሆነውን እምነት እከተላለሁ ለማለት ፈፅሞ

16 Eusebius HE s:20:9-7

17 St. Cyprian:Epistle 74:11, Unity of the Church 6

18 St. Gregor of Nyssa, Contra Eunomuim 4PG 45:653

አይችልም። የሚያስተምረው እና የሚያምነው ነገር አባት የማይጠራበት ‹ራስ በቀል› ነውና።

ቅዱስ ባስልዮስ ታላቁ። (330–379 ዓ.ም):- የቂሣርያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው የንርጎርዮስ ዘኑሲሱ ወንድም ባስልዮስ በትምህርቱ ‹የመናፍቃን የክህደት ቀስት ዒላማው ዶግማችንን መበረዝ ነው። ለዚህ ተግባራዊ መሆን ከሚጠቀሙበት መንገድ ደግሞ እውነተኛው እምነታችንን፣ ሐዋርያዊ ትውፊታችንን ማጣጣል እና ማናናቅ አንዱ ነው። መጻሕፍትን ያከበሩ መስለው ትውፊታችንን ይንቁብናል!›[19] በማለት አስቅድሞ እንደተናገረው የዘመናችን መናፍቃንም ለወንጌል የተቆረቆሩ ለእግዚአብሔር ቃል የቀኑ መስለው በመቅረብ እኛ መጽሐፍ ቅዱስን ያገኘንበትን ትውፊት አስጥለው እንደነርሱ ባዶ ሊያስቀሩን ይፈልጋሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (347–407 ዓ.ም) የቁስጥንጥንያ ሊቀጳጳስ የነበረው ዮሐንስ አፈወርቅ ‹ሐዋርያት ሁሉንም ነገር አልጻፉልንም። እንዲያውም የበለጠውን ያስተማሩን በቃልና በማሳየት ነው። ለኛ ከጽሑፎቻቸው ጋር ያወረሱን ትልቅ ሀብት ቢኖር ትውፊታቸው ነው?›[20] እንዳለው ቅዱሳን ሐዋርያት ለትምህርትና ለተግሣጽ ያህል ከጻፉልን ሌላ ለኛ ያወረሱን የቤተ ክርስቲያን ሀብት ትውፊት ነው። በዚህም በጽሑፍ ያልተላለፈው ሕያው ሆኖ ዛሬ ድረስ በተግባር የሚታየው የክርስትና ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን ልጆች ደርሶአል። ሁለቱም የሐዋርያት ትምህርት ነውና አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ መሮጥ አይቻልም።

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ (ከ315–403 ዓ.ም) የሰላሚስ (ቆጵሮስ) ሊቀ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ‹ትውፊታችንን ለክርስትና ጉዞአችን መጠቀማችን የግድ ነው። ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለሁሉም ነገር አልተጻፈምና፤ አባቶቻችን ሐዋርያት ሃይማኖትን ለኛ ያወረሱን በጽሑፎቻቸውና በትውፊታቸው ነው›[21] በማለት ተናግሮ ነበር።

---

19 St. Basil: On the Spirit, ch 10/25

20 St. John Chrysostom, In 2 thess., Hom 4:4,PG 62:486.

21 St. Epiphanius :Adv. Hear 61:6.PG 41:1048 Ancoratus 62.



እንግዲህ በአባቶቻችን ትምህርት እንደተገለጠው ትውፊት የመጽሐፍ ቅዱስ ግብራርያ፣ የሐዋርያት ትምህርት ተጠብቆ ለትውልድ የሚተላለፍበት፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያገኘንበት እና የተረዳንበት የቤተ ክርስቲያን ሀብት እንጂ ‹ዘመናውያኑ› እንደሚሉን ተረት አይደለም።

## ትውፊትን መጠበቅ

ባለንበት ዘመን ብዙ ሰዎች አንድ ጥያቄ ሲጠይቁ ተደጋግሞ ይሰማል። «የእምነት ድርጅቶች ለምን በዙ?» ለዚህ ጥያቄ ግን መልሱ አንድ ብቻ ነው። «ሐዋርያዊ ትውፊት በመጣሱ» የሚለው ነው አባቶቻችን ማናቸውንም ነገር የሚፈጽሙት አባቶቻቸውን ተመልክተው፣ ከእነርሱ ተረድተው ከሥርዓታቸውና ከሃይማኖታቸው፣ ከትምህርታቸውና ከመንገዳቸው ሳይወጡ ነው። በዚህም የተነሣ አባቶቻቸውን መስለው አባቶቻቸውን ሆነው ይገኙ ነበር። ይህ ትውልድ ግን በተለይም ሠለጠንኩ ያለው ክፍል እንደ 2ኛው መ/ክ/ዘ መናፍቃን (እንደ ግኖስቲኮች) እምነትን ከፍልስፍና ስለሚተላለው የገዛ ዘመኑን ምቾት ለማሟላት ሲል በፈቃደ እግዚአብሔር ከመመራት ይልቅ ፈቃደ እግዚአብሔርን እንደ ሥጋው ምኞት ለመምራት ይፈልጋል። የሐዋርያትን ትውፊት እየናቀ ‹ራስ በቀል› ትውልድ እየሆነ እርሱ ለክርስትና የመጀመርያ የሆነ ይመስል አባቶቹን እያቃለለ፣ እየረሳም ተጉዞአል።

የዚህ የአበው ትውፊት እየተረሳ እና እየተናቀ መምጣት ደግሞ በመንፈሳዊ ኑር ዙርያ ታጥር የነበረውንና የክህደት ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገባ የብረት ግንብ ሆኖበት የኖረውን አጥር አፈረሰው። የዲያብሎስ መርዝ እንደልቡ በክርስቲያኖች ኑር ውስጥ እንዲነዛም አደረገው። በመጨረሻም መንፈሳዊ ኑርን አስለቅቆ ሥጋዊ ምኞትን፣ ዓለማዊ ቅንጦትን፣ የኃጢአት ነቀርሳን ተከለበት።

የአንደኛና የሁለተኛው ዓለም ሕዝቦች ለስሙ የያዙትን ክርስትና ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከሥልጣን፣ ከቅንጦትና ምቾት ወዘተ. ጋር አያይዘው የምድራዊ ኑርአቸው፣ የኃጢአታቸው ሽፋን ሊያደርጉት ሲሹ።

የ3ኛው ዓለም ሕዝቦች ደግሞ ለእነርሱ ክርስትና ተብሎ የተሰበከላቸው (በተለይ የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች) ከቅኝ ግዛትና ከብዝበዛ ጋር አብሮ በመሆኑ ነፃነታቸውን ካገኙ ወዲህ[22] ለክርስትና እምነት ያላቸው አመለካከት ለቅኝ ገዥዎቻቸው ካላቸው አመለካከት ጋር ተጣምሮአል። ያንኑ ለእነርሱ የተሰበከውን የስም ክርስትና የባዕዳን ጫና አድርገው ስለሚያዩት የኔነት ስሜት አይሰማቸውም።[23]

እንግዲህ ዓለም በዚህ መልክ መንገደ እግዚአብሔርን እየለቀቀ በገዛ ምኞቱ ሲጓዝ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ግን አስቀድሞ ከአበው፣ በኋላም ከሐዋርያትና አሠረፍናታቸውን ተከትለው ከተነሡ ቅዱሳን ያገኘችውን ርቱዕ የሆነ እምነት ሳትከልስ፣ ሳትበርዝ፣ ሳትጥል እና ሳትነጥል ይዛ መገኘትዋ ምን ያህል ሐዋርያዊት፣ ርትዕት፣ ቅድስትና ንጽሕት እንደሆነች ይገልጥልናል።

ከዚህች ቅድስት እናት፣ ዓለም ለተራበ ሕይወቱ ምግበ ነፍስ ይጠብቃል። ለቆት፣ ከዶትና ረስቶት ወደመጣው ማንነቱ እንድ ትመልሰው ይሻል። በዚህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ተጠብቆ መገኘቱ፣ ብሎም ለትውልዱ መገለጡ፣ በየጊዜውም ትምህርቱ መስጠቱ አስፈላጊ ነው። ለዚህም:-

በአበው በኩል:-

ትውልዱ ተራቀቅኩ እያለ በሄደ ቁጥር፣ የመናፍቃንና የከሃድያን ዓይነትና መጠንም እየጨመረ ይሄዳል። በዚህ ጊዜ ደግሞ እነዚህ የኑፋቄ ትምህርቶች በክርስቲያኑ ሕዝብ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ኑሮ ውስጥ ዘልቀው በመግባት አከራካሪ ጥያቄዎችን ያስነሣሉ፣ ሕዝቡን በሥርዓትና በእምነት ለመለያየትም ይጥራሉ። ሕዝቡም የራሱን መንገድ መርጦ በመከተል በሚዋዥቀው ዓለም ውስጥ ሰምጦ እንዳይጠፋ ቅዱሳን አበው ከዚህ በፊት በታሪክ እንደምናውቀውና በዓይንም እንዳየነው:-

22 ከ1960ዎቹ ወዲህ።

23 ቀሲስ ክርስቶስ፤ [illegible] ነገረ መለኮት:-...[illegible] ከዚህ በኋላ ነው።



1. አከራካሪ በሆኑ ነገሮች ላይ መወሰን ያስፈልጋል:-

ለምሳሌ በሀገራችን በኢትዮጵያ ከ13ኛው መ/ክ/ዘመን ጀምሮ በሰንበት በዓል አከባበር ላይ ክርክር ተነሥቶ ነበር። ቀዳሚትን ማክበር ይገባናል ወይስ ዕለተ እሑድን (ሰንበተ ክርስቲያንን) ብቻ? በሚለው ነጥብ ዙርያ። ይህ ጉዳይ ለ100 ዓመት ያህል ሲያከራክር ቆይቶ በ14ኛው መ/ክ/ዘመን አፄ ዘርዐ ያዕቆብ በጠሩትና በደብረ ምጥማቅ በተደረገው ጉባዔ ከእስክንድርያ የመጡት ሁለቱ ሊቃነ ጳጳሳት አባ ገብርኤልና አባ ሚካኤል፣ እነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና ሌሎች ሊቃውንት ተሰብስበው ‹ሁለቱም ሰንበቶች እንዲከበሩ› በማለት የነበረውን ትውፊት አፅንተው ወስነዋል። ይህም ሕዝበ ክርስቲያኑ አንድ ወጥ ሥርዓት እንዲከተል አድርጐታል።

ዛሬም የሕዝቡን የልብ ትርታ በማድመጥ ከመሠረቱ ርቆ ከመሄዱ በፊት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የከዚህ በፊቱን ሥራቸውን ቢቀጥሉበት መልካም ነው።

2. ቅዱሳት መጻሕፍትን ማዘጋጀት

ቅዱሳን አበው በየዘመናቱ ለትውልዱ ሃይማኖቱን የሚያፀናበት፣ በሥርዓት የሚጓዝበት፣ ዘመኑን የሚዋጅበት የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍትን ደርሰው አልፈዋል። ዛሬም አሉ። ይህ መጻሕፍትን ለትውልዱ የመጻፍ ትውፊት አስቀድሞ ከነቢያት በኋላም ከሐዋርያት ቀጥሎም ከቅዱሳን አበው የመጣ ነው። ለምሳሌ ከላይ በ14ኛው መ/ክ/ዘ ደቂቀ እስጢፋ የተባሉ መናፍቃን ሥዕልን፣ መስቀልን፣ ክብረ ቅዱሳንን፣ ቤተ ክርስቲያን መሳለምን... ተቃውመው በተነሡ ጊዜ በደብረ ብርሃኑ ጉባዔ ተወግዘው ሲለዩ የተለያዩ የእምነት ማፅኛ ቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፈው ነበር።

አፄ ዘርዐያዕቆብ:- ንግሥናን ከሊቅነት አስተባብረው የያዙት አፄ ዘርዐያዕቆብ የሚከተሉትን መጻሕፍት ጽፈው ነበር።

- ጦማረ ትስብእት
- መጽሐፈ ብርሃን
- መጽሐፈ ባሕርይ
- መጽሐፈ ምዕላድ

- መጽሐፈ ክህደተ ሰይጣን
- ተዐቅቦ ምሥጢር
- እግዚአብሔር ነግሠ

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በዚያው ዘመን

- መጽሐፈ አርጋኖን
- ሕይወተ ማርያም
- ሰዓታት
- መጽሐፈ ምሥጢር
- ውዳሴ መስቀል
- ተአምኖ ቅዱሳን
- ክብረ ቅዱሳን፣ ወዘተ. መጽሐፍትን ጽፈዋል።

ዛሬም አበው ጳጳሳት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እና ከሲኖዶስ ስብሰባ መጠናቀቅ በኋላ ለሕዝቡ ጥያቄ መልስ የሚሆን እምነት እንዲፀና፣ ሥርዓት እንዲረጋ የሚያደርግ አንድ መጽሐፍ ቢያወጡ፣ ከዚህም በተጨማሪ በቃል ያለ ይረሳል ነውና ትውልዱ መዓዛ ቅዱሳን እንዳይርቀውና ቀላዋጭ እንዳይሆን የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ታትመው ለምእመናን ቢዳረሱ መልካም ነው።

3. የአብነት ት/ቤቶችን መጠበቅ:- በተለይ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአበው ትውፊት ተጠብቆ ለዘመናችን እንዲደርስ ታላቅ አስተዋፅኦ ያደረጉት የአብነት ት/ቤቶች ናቸው። ትምህርትን፣ ሥርዓትን፣ ሥነ ምግባርን፣ ክርስቲያናዊ ኑሮን፣ ታሪክን፣ ወዘተ ለተከታዩ ትውልድ ያስተምራሉ ያወርሳሉ። ዛሬ ግን ሁለት ችግሮች አፍጠው ይታዩባቸዋል።

ሀ. የት/ቤቶቹ መዘንጋት። የአብነት ት/ቤቶች በአቋም ደረጃ ጥንት እንደነበሩት ናቸው። የቤቱ አሠራር፣ የተማሪዎች የኑሮ ሁኔታ፣ የመምህራን ኑሮ እና ደመወዝ አልተሻሻለም። ዘመኑ ሲገፋ እርሱ ግን ባለበት ይሄዳል። በዚህም የተነሣ የ20ኛው መ/ክ/ዘመንን ወጣት ገና በሩቁ ያስደነግጠዋል።



ለ. የተማሪዎች ሁኔታ። ዛሬ በሀገራችን እቡን ዘበሰማያት የማይደግም ትውልድ እየመጣ ነው! ይህ ደግሞ ከየመዋዕለ ሕፃናቱ የሚመጣው ትውልድ ነው (Kindergartenaized Generation) ይህ ትውልድ የዘመኑን ጥበብና ፍልስፍና ብቻ ስለሚግር ከሥነ ምግባርና መንፈሳዊ በረከት ውጭ እየሆነ ነው። ዛሬ በአብነት ት/ቤቶች የምናገኛቸው አብዛኞዎቹ የገጠር ወጣቶች ናቸው ማለት ይቻላል። እነዚህ ደግሞ አንድ ቀን ከተማን በቀመስዋት ጊዜ በዚያው ቀልጠው ሊቀሩ ይችላሉ።

በመሆኑም የት/ቤቶቻችን አቋም ዘመናዊ፣ በምግባር፣ በሃይማኖት፣ በሥርዓት ትውፊታዊ (ጥንታዊ) ሊሆኑ ይገባል። የከተማ አብያተ ክርስቲያናት በአጥቢያቸው ት/ቤት ከፍተው እቡነ ዘበሰማያት የሚደግም ትውልድ ማፍራት አለባቸው።

ሐ. የንዋየ ቅድሳትና ቅርሶች መጠበቅ:- አባቶቻችን መንፈሳዊ በረከት ያገኙባቸው፣ ከኃጢአትና ከዲያብሎስ ጋር የተጋደሉባቸው፣ የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊነት፣ ታሪካዊነትና ሐዋርያዊነት የሚመሠክሩ፣ ትውልዱን በማንነቱ የሚያኮሩ እያሌ ንዋየ ቅድሳትና ቅርሶች አሉን። አበው እነዚህን መንፈሳውያን ሀብቶች ለኛ ያስረከቡን ከጠላት ታግለው በየዋሻው ሠውረው ነው። ጥቅማቸውን ቢያውቁ። ዛሬ ግን በዘራፍያን እየተመዘበሩ ታሪክ አልባ እየሆን ነውና የቤተ ክርስቲያን ልጆች መጠንቀቅ አለብን።

- ጥበቃው መጠንከር
- ተመዝግበው መያዝ
- ታሪካቸው መጠናትና መመዝገብ
- አቀማመጣቸው ከመፍረስ፣ ከመበጣጠስ፣ ከመጐሳቆል የሚያድን መሆን
- የፈረሱት መጠገን፣ ያሉት መጠበቅ አለባቸው።

## በምእመናን በኩል

የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት ለመጠበቅ የአበው ጥረት ብቻ አይበቃም። ምእመናንም ድርሻ አላቸው።

- የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎችን በማክበር
- የአበውን አሠረፍናት ተከትሎ በእምነት በኑሮ እና በሥርዓት፣ እነርሱን ሆኖ በመገኘት፤
- ቅዱሳት መጻሕፍትን በመግዛት፣ በመሰብሰብ እና በመጠረዝ ለትውልድ በማቆየት
- ንዋየ ቅድሳትን ለመጠበቅ በሰሙኑ ጉባዔያት በኩል አስተዋፅዖ በማድረግ
- በእምነት፣ በሥርዓት፣ አለያም ደግሞ በማኅበራዊ ኑሮ ረገድ ለሚነሡ ጥያቄዎች፤ የዘመኑ ፍልስፍና፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በምእመናን ኑሮ ለሚፈጥሩዋቸው እንዲሁም ችግሮች የራስን አመለካከት ይዞ ከመንዝ ይልቅ ለአበው አቅርቦ መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ፣
- ትውፊታችንን ለልጆቻችን ማስተማር።

እንዲህ ካደረግን በእውነት የሐዋርያትን ትውፊት ይዘን፣ የቅዱሳንን ሕይወት ወርሰን፣ አንድ ጊዜ ፈፅሞ ለቅዱሳን በተሰጠች ሃይማኖት መኖር እንችላለን። ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።



# ክፍል ሁለት

## የመጀመሪያው መቶ ክ/ዘመን ቅዱሳንና ተጋድሏቸው

### መግቢያ

የመጀመሪያው መቶ ክ/ዘመን በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ልዩ የሆነ ሥፍራ ያለው ዘመን ነው። ምክንያቱም

1. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው፣ ወንጌለ መንግሥቱን ያስተማረው፣ ለቤዛ ዓለም ሲል በመልዕልተ መስቀል የተሰቀለው፣ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ክብርት ትንሣኤውን የገለጠው፣ በዐርባኛውም ቀን ወደ ሰማየ ሰማያት ያረገው በዚሁ ዘመን ነው።

2. ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው የሆኑት ቅዱሳን ሐዋርያት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለታላቁ የወንጌል ተልዕኮ የተመረጡት፤ በመላዋ ዓለም ዞረው ወንጌልን የሰበኩት፤ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሲሉ ደማቸውን አፍስሰው ያረፉት በዚህ ጊዜ ነው።

3. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም ተዋጅታ፣ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ጸንታ ለዓለም የተሰበከችበት የሐዲስ ኪዳን መባቻ ነው።

4. ጌታችንን በገንዘባቸውና በጉልበታቸው ያገለገሉ ምእመናን (እነ ዮሴፍ ዘአረማትያስና ኒቆዲሞስ)፤ በተአምራቱ ያመኑ (እነ ጲላጦስና ሌንጊኖስ) የተገኙበት ዘመን ነው።

5. የመጀመሪያዎቹ ሰማዕታት ቅዱስ እስጢፋኖስ (ሊቀ ዲያቆናት) እና ቅዱስ ያዕቆብ ሐዋርያው ክርስትናን በደማቸው ያጸኑበት ዘመን ነው።

6. ለክርስትና መሰበክ ማዕከላት የነበሩት የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያውያን መናብርት የተገኙበት ዘመን ነው።[1]

### ሀ. የኢየሩሳሌም መንበር

ክርስትና መጀመሪያ የተሰበከው በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ስለነበር የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ከተማዋን በማዕከልነት ይጠቀሙባት ነበር። የኢየሩሳሌሙ መንበር የመጀመርያ ፓትርያርክ

[1] The See of St. Mark and the School of Alexandria, p.10-13

ቅዱስ ያዕቆብ (የጌታችን ወንድም – እኅት ለእግዚእን) ሲሆን በ62 ዓ.ም በሰማዕትነት ሲያርፍ ወንድሙ ስምዖን በመንበሩ ተተካ። እርሱም በ106 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ከተማ በሰማዕትነት ዐርፎአል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ በተናገረው ትንቢት መሠረት (ማቴ.23፥37–38) በ70 ዓ.ም ሮማዊው ንጉሥ ጥጦስ 80000 ሠራዊት አስከትቶ ከተማዋን በመውረር ከተማዋን ሙሉ በሙሉ በዚያን ጊዜ በሮማውያን አገዛዝ ላይ ዐምፀው የነበሩትን አይሁድ ግማሾቹን ሲፈጃቸው የተሩትን ደግሞ በባርነት ሸጣቸው። ከተማዋንም አፈረሳት። በዚህም የተነሣ የኢየሩሳሌሙ መንበር ተዘቀዘ።[2]

## ለ. የአንጾኪያ መንበር

አንጾኪያ ለሮማ አስተዳደር ሦስተኛ ከተማ የነበረች የሶርያ ከተማ ናት። በዚህች ቦታ ቀድመው ወንጌልን የሰበኩት ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ ሲሆኑ ተተኪውም ቅዱስ ጴጥሮስ ተካፍሉበታል።

በከተማዋ አይሁድም አሕዛብም ነበሩባት። የጌታ ደቀ መዛሙርት ‹ክርስቲያን› የሚለውን ስም ያገኙት በዚህች ከተማ ነው። ለመጀመሪያዋ የሐዋርያት ሲኖዶስ (50፣ 51 ዓ.ም) ምክንያት የሆነው ጥያቄም የተነሣው ከአንጾኪያ ክርስቲያኖች ነው።

በሐዋርያት እግር ተተክቶ መንበሩን የተረከበው አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ነበር። ዛሬ የሶርያ ክርስቲያኖች መንበር ናት።

## ሐ. የእስክንድርያ መንበር

የእስክንድርያ ከተማ በግብፅ ሰሜናዊ ጫፍ በዓባይ ወንዝ ዳር የምትገኝ ወደብ ናት። ከተማዋ ስሟን ያገኘችው ከታላቁ የግሪኮች ንጉሥ ከእስክንድር ነው። መንበሩን የመሠረተው ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ በ60 ዓ.ም አካባቢ ሲሆን በ68 ዓ.ም በሰማዕትነት ሲያርፍ ቅዱስ አንያናስ በመንበሩ ተተክቶአል። ዛሬ የግብፅ ቤተክርስቲያን ዋና ማዕከል ናት።

---

2 የኢየሩሳሌምን ከተማ አመሠራረት ታሪክ ቤሉምር መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁ.2 ላይ ተመልከት።



## መ. የሮማ መንበር

የሮማ መንግሥት ዋና ከተማ ሮማ ነበረች። በከተማዋ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን የሰበከው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ መሆኑ ይነገራል። የመጀመሪያዎቹን የሮም ጳጳሳት ቅዱስ ሊኖስንና ቅዱስ አኔቅሊጦስን የሾማቸውም እርሱ ነው። የሮም ሰዎች ግን ለታሪክ ሽሚያ በቅድሚያ የሰበከው ቅዱስ ጴጥሮስ ነው ይላሉ።

## ሠ. የኤፌሶን መንበር

በጥንቱ የታናሹ እስያ በዛሬው የቱርክ ግዛት የምትገኝ ከተማ ናት–ኤፌሶን። አስቀድሞ በዚህች ከተማ ወንጌልን የሰበከው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊም መንበሩን በኤፌሶን አድርጐ ለብዙ ዓመታት አስተምሮባታል። በመጨረሻም በሮማውያን ተይዞ ወደ ፍጥሞ ደሴት የተጋዘው በዚህች ከተማ ሲያስተምር ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስን ለዚህች ከተማ ሊቀ ጳጳስ አድርጐ ሾሞት ነበር። በግፍ እስከተገደለበት እስከ 97 ዓ.ም ድረስ የኤፌሶን ሊቀጳጳስ በመሆን ቅዱስ ዮሐንስን ረድቶአል።

የኤፌሶን መንበር ቅዱስ ዮሐንስ ከዚህ ዓለም ከተለየ (ከ99 ዓ.ም) በኋላ ቀዘቀዘች። ዛሬ ኢያዞሉክ ተብላ የጥንት ታሪኳ ጠፍቶ ቱርክ ውስጥ የምትገኝ ከተማ ሆናለች።

## ረ. የሰርምኔስ መንበር

በቅድሚያ በዚህች ከተማ በማስተማር መንበሩን የመሠረተው ነባቤ መለኮት ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ሲሆን እርሱ እየተዘዋወረ ለማስተማር እንዲያመቸው ደቀ መዝሙሩ ፖሊካርፐስን ሊቀጳጳስ አድርጐ በመንበሩ ሾሞት ነበር። ፖሊካርፐስም በሰማዕትነት እስካረፈበት እስከ 155 ዓ.ም ድረስ ሲያገለግል ቆይቷል። ከዚያ በኋላ ግን ማዕከልነቷ እየቀዘቀዘ መጣ። ዛሬ ከተማዋ ኢዝሚር ተብላ ቱርክ ውስጥ ትገኛለች።

## ሰ. የአቴና መንበር

በመጀመሪያ ለአቴናውያን ወንጌልን የሰበከው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ነው። እርሱም ለአቴና መንበር ቅዱስ ዲዮናስዮስን ሊቀጳጳስ

አድርጉ ሾመው። በመጀመሪያው መ/ክ/ዘ የአቴና መንበር ወደ ሮም መጠቃለል በመጀመሩ እየተዘተዘ መጣ።

### ሸ. የቁስጥንጥንያ መንበር

የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ የተሰበከችው በሐዋርያው በቅዱስ እንድርያስ ነበር። ከተማዋ የምሥራቁ ሮም ግዛት (የባዛንቲየም) መናገሻ ነበረች። ይህች መንበር እነ ዮሐንስ አፈወርቅን የመሰሉ ታላላቅ የተዋሕዶ ሊቃውንት ያፈራች ናት። ነገር ግን ቁስጥንጥንያውያን በ451 ዓ.ም በኬልቄዶን የተፈጠረውን የክህደት ትምህርት በመቀበላቸው ርትዕት ከሆነችው ሃይማኖት ፈቀቅ አሉ። ይባስ ብሉ በ1445 ዓ.ም በአቶማን ቱርክ ወረራ አካባቢው ሲያዝ የቁስጥንጥንያ መንበርነት ተደመደመ። አስደናቂው የቅድስት ሶፍያ ቤተ ክርስቲያንም መስጊድ ሆነ። ስሟም ተቀይሮ ኢስታንቡል ተባለ።

የመጀመሪያው መ/ክ/ዘ በአጠቃላይ ዛሬ ሁላችንም በታሪክ የምናነሣው፣ በኑሮ የምንገልጠው፣ የክርስትና ሕይወት ለዓለም የተበሠረበት ነበር።

ብዙ የታሪክ ምሁራን የሚዘነጉት ነገር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲነሣ ታላቁን ቦታ የሚይዘው የቅዱሳን ልጆቿ ገድል መሆኑን ነው። የቤተ ክርስቲያን ጉዞ ማለት የቅዱሳን ተጋድሎ ነው። ያለ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን፣ ያለ ቅዱሳንም ቤተ ክርስቲያን አይኖሩም። ቤተ ክርስቲያን በዓላውያን ነገሥታት፣ በአረማውያን መኳንንት ስትገፋ፣ በመናፍቃን ጌራ ስትፈተን ብትኖርና ብትመነምን እንኳ ሳትበጠስ ለዚህ ትውልድ እንድትደርስ ያደረጋት የቅዱሳን ልጆቿ ሰማዕትነት ነው።

ስለዚህም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስናነሣ ከአድራጊዎቹ፣ ከባለሟሎቹ እና ከታሪኩ ባለቤቶች አንዣር ጭምር እንጂ ከድርጊቱ ጋር ብቻ መሆን የለብንም።

በዚህ በመጀመሪያው መ/ክ/ዘመንም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ አያሌ ቅዱሳንን አፍርታለች። አሠረ ፍኖታቸውን እንድንከተል፣ ውለታቸውንም እንዳንዘነጋ፣ ብበረከታቸውም እንድንጠቀም ከቅዱሳን ሐዋርያት ታሪክ ገድልና በረከት በመጀመር ጥቂቶቹን እነሆ።



ምዕራፍ አንድ

## ቅዱሳን ሐዋርያት

መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዘመኑ በማየ ዮርዳኖስ በዕደ ዮሐንስ ተጠምቆ 40 ቀንና ሌሊት በገዳመ ቆሮንቶስ ከጾመ ከጸለየ በኋላ የማስተማር ሥራውን ሲጀምር አስቀድሞ ያደረገው ነገር ቢኖር ቃሉን ተምረው፣ ሰምተው፣ ተአምራቱን አይተው፣ ዳሰው፣ በዓለም ዞረው ወንጌልን የሚሰብኩ ደቀ መዛሙርቱን መምረጥ ነበር። እነዚህ ደቀ መዛሙርቱም ሐዋርያት ተብለው ይጠራሉ።

ሐዋርያ የሚለው ቃል ሖረ–ሄደ ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም የተላከ ሂያጅ፣ ልዑክ ማለት ነው። ወንጌለ መንግሥትን፣ ድኅነተ ዓለምን ለመላው ዓለም ሊያውጁ፣ ሊያበሥሩ ተልከዋልና። ቅዱስ ማርቆስ በወንጌሉ እንደገለጠው (ማር.3፥13) አስተድሞ ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ከጠራቸው በኋላ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የገለጠውን ድንቅ ሥራ፣ አምላክ ሰው ሆኖ ያደረገውን ተአምራት፣ ለዓለም ድኅነት የተደረገውን ሁሉ ሊመሠክሩ ተመርጠዋል።

ከዚያ በፊት በሌዋውያን ዘር ይወርድ የነበረውን የብሉይ ኪዳን ሥልጣነ ክህነት በሐዲስ በመተካት ለእነርሱ ሰጣቸው። ዮሐ.20፥22። እነርሱም ጌታችን እንዳስተማራቸውና ቃል ኪዳንም እንደገባላቸው። ማቴ.28፥20። ለተከታዮቻቸው ይኸንን ሥልጣን በአንብሮተ ዕድና በንፍሐት በመሾም አስተላለፉ። የሐዋ.9፥12።

በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተዋጀችውን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በስብከታቸው፣ በሰጣቸውም ሥልጣን፣ ባደላቸውም ጸጋ ጠብቀው አቆዩዋት።

የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በበዓለ ኀምሳ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት በ3000 ምእመናን በሀገረ ኢየሩሳሌም በ34 ዓ.ም

ተመሠረተች። ከዚያም ዓለምን ዕጣ በዕጣ ተካፍለው ተዘዋውረው አስተማሩ። ወንጌልን ሰብከው ቤተ ክርስቲያንን አነፁ። አምልኮ ጣዖትን አጠፉ። ርኩሳን አጋንንትን አሳደዱ። በመስቀል ዕርፍ አርሰው፤ ንጹሕ ዘር ወንጌልን ዘርተው፤ በደማቸው አተሙ።

ላስተማሩት ሕዝብ ለእምነቱ ማጽኛ የሚሆኑ መልእክታትን ጻፉ። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ሠሩ። ከጌታ የተማሩትን፤ ያዩትን እና የሰሙትን ለተከታዮቻቸው በቃልም፤ በኑሮም በመጻሕፍትም አውርሰው በተጋድሎ ዐረፉ።

## የሐዋርያት አመራረጥ

ጌታችን ሐዋርያትን ከድኆችም ከሀብታሞችም መርጦአል። እነ ቅዱስ ጴጥሮስን የመሰሉ ድኻ ዓሣ አጥማጆችን ሲጠራ እነቅዱስ ማቴዎስን የመሰሉ በቀረጥ ብር የከበሩትንም አልተዋቸውም። ሁሉም በእግዚአብሔር ዘንድ እኩል ናቸውና። ሁሉም ደግሞ ያላቸውን ትተው ተከትለውታል። ማቴ.4፥20፤ 9፥9።

ከተማሩትም ከማይማሩትም ወገን መርጦአል። ዮሐንስና ያዕቆብን ጌታ የጠራቸው ከአባታቸው ጋር ዓሣ ሲያጠምዱ ነው። ሌላ ትምህርት አልነበራቸውም። ነገር ግን አልናቃቸውም። ምሁረ ኦሪት የነበረውንም ናትናኤልን ጠርቶታል አልተወውም።

የቀናተኞች አይሁድ ወገን በመሆኑ በዚያን ዘመን ሮማውያንን ለማስወጣት ውስጥ ውስጡን በምድረ ፍልስጥኤም ይካሄድ የነበረው በመፅ ተካፋይ የነበረውን ስምዖንን ከዚያ ግርግር አውጥቶ የሰላምና የፀጥታ ወደብ ወደ ሆነው ወደ እርሱ ወስዶታል።

ቤተ እሥራኤል ስትመሠረት 12ቱ አበው እየተባሉ በሚጠሩት ከያዕቆብ አብራክ በተከፈሉ የአሥራ ሁለቱ ነገድ አባቶች ነበር። አሁንም የእሥራኤል ዘነፍስ ማኅበር ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት በ12ቱ ሐዋርያት ትሆን ዘንድ እምላክ ፈቀደ።



1. ቅዱስ ጴጥሮስ – ከቤተ ስምዖን (በእናቱ ወገን) እናቱ ትወደው ስለነበር በነገድዋ ስም ጠራችው።
2. ቅዱስ እንድርያስ–ከቤተ ሮቤል (በአባቱ ወገን) አባቱ ይወደው ነበርና ከነገዱ በተወረሰ ስም ጠራው።
3. ቅዱስ ያዕቆብ – ከነገደ ሌዊ (በአባቱ)
4. ቅዱስ ዮሐንስ – ከነገደ ይሁዳ (በእናቱ)
5. ቅዱስ ፊልጶስ – ከነገደ ዛብሎን
6. ቅዱስ በርተሎሜዎስ – ከነገደ ንፍታሌም።
7. ቅዱስ ማቴዎስ – ከነገደ ይሳኮር
8. ቅዱስ ቶማስ – ከነገደ አሴር
9. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ – ከነገደ ጋድ
10. ቅዱስ ታዴዎስ – ከነገደ ዮሴፍ
11. ቅዱስ ስምዖን ቀነናዊ – ከቤተ ብንያም
12. ያስቆሮቱ ይሁዳ – ከቤተ ዳን[3]

## የሐዋርያት ሲኖዶስ

ሲኖዶስ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም ስለ ነገረ ቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰቡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉባኤ ማለት ነው።

የመጀመሪያዋ የሐዋርያት ሲኖዶስ የተደረገችው በ50 ዓ.ም አካባቢ በኢየሩሳሌም ከተማ ሲሆን ለጉባኤው መደረግ ምክንያት የሆነውም በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከይሁዲነት በተመለሱትና ከአረማዊነት በተመለሱት መካከል የተነሣውን ክርክር ለመፍታት ነበር።[4]

---

[3] ገድለ ሐዋርያት ገጽ 49–50

[4] አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ይህችኛይቱን እንደ ሦስተኛ ጉባኤ በመቁጠር የመጀመሪያው በ34 ዓ.ም በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ የሚተካውን ሐዋርያ መርጦ ለመሾም የተደረገው ጉባኤ (የሐዋ.1፥15–26) ሁለተኛው ደግሞ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ያሉ ክርስቲያኖችን ያገለግሉ ዘንድ ሰባቱን ዲያቆናት ለመምረጥና ለመሾም የተሰበሰበው ጉባኤ ነው ይላሉ። የሐዋ.6፥1–6። ትንሣኤ መጽሔት፤ ቁ.17/71፤ ገጽ 18። በሌላት አብያተ ክርስቲያናት መጻሕፍትና ብዙ አበው ግርግርስ በጻፉት የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ላይ ግን የመጀመሪያዋ ሲኖዶስ ተብላ የተመዘገበችው በሐዋ.15 ላይ የተደረገችው ናት።

ቅዱሳን ሐዋርያት በተሰበሰቡ ጊዜ ሁሉ ስለ ነገረ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ካህናት አገልግሎት፣ ስለ ምእመናን ድርሻ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውሳኔዎችን አስቀምጠዋል። እነዚህ ‹እነርሱና መንፈስ ቅዱስ› በአንድ ላይ ሆነው የወሰኑዋቸው ውሳኔያት በሲኖዶስ፣ በአብጥሊስ፣ በግፅው፣ በዲድስቅልያ ወዘተ. መጻሕፍቶቻቸውና በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ለኛ ደርሰውናል።

ዛሬም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዓመት ሁለት ጊዜ የሊቃነ ጳጳሳት ጉባዔ (ሲኖዶስ) የሚደረገው በዚሁ መሠረት ነው።

## አዕማድ ሐዋርያት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች በላከው መልእክቱ (2፥9) ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ እና ያዕቆብን ‹አዕማድ ሐዋርያት› በማለት ጠርቷቸዋል። ይህ ስም ሊሰጣቸው የቻለበት ዐቢይ ምክንያት የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን በዋናነት ያስተባብሩ ስለነበር ነው።

ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ሦስቱ ሐዋርያት ‹የምሥጢረ ሐዋርያት› እየተባሉም ይጠራሉ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

- በደብረ ታቦር ምሥጢረ መለኮቱን ሲገልጥ
- በኢያኢሮስ ቤት ልጁን ሲፈውስ
- በጌቴሴማኒ ሲጸልይ ከሌሎች ለይቶ ይዟቸው ሄዶ ነበርና።

## ቅዱስ ጴጥሮስ – የሐዋርያት አለቃ

ጌታችን በቂሣርያ ከተማ ለሐዋርያት ያቀረበውን ጥያቄ በመመለሱ ቅዱስ ጴጥሮስን ‹የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋ እና ደም ይህን አልገለጠልህም። አንተ ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ (ዐለት–በላቲን) ነህ። በዚህች ዐለትም ላይ ቤት ክርስቲያኔን እሠራለሁ። የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ። በምድር የምታሥረው በሰማያት የታሠረ ይሆናል። በምድር የምትፈታው በሰማያት የተፈታ ይሆናል።» ማቴ.16፥17–19 የሚለውን ቃል ተናግሮታል።



ቅዱስ ጴጥሮስ ይህንን ለመባል የበቃው የክርስትና እምነት መሠረት የሆነውን ምሥጢረ ሥጋዌን – ምሥጢረ ተዋሕዶን በመመስከሩ ነው። አይሁድ የዮሴፍ ልጅ ነው፤ ሌሎቹ ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው፤ ሲሉ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ቁልጭ አድርጎ በመመስከሩ ምስክርነቱም የእምነት መሠረት ነውና ‹ዐለት› ተባለ። የክርስትና እምነት መነሻው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያድነን ሊዋጀንም መጣ ብሎ ማመን ነው።

ጌታችን ቅዱስ ጴጥሮስን ‹ዐለትነህ› ያለው ስለ እምነቱ ነው። ሰዎችን ታናሽ ወይም ታላቅ፣ ብፁዕ ወይንም ሌላ የሚያደርጋቸው እምነታቸው ነውና! ለዚህ ነው ጌታችን በመዋዕለ ትምህርቱ ብዙ ጊዜ ‹እምነትህ(ሽ) ታላቅ ነው› ይል የነበረው።

‹የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ› ለሐዋርያት የተሰጠውን ሥልጣነ ክህነት የሚያሳይ ነው።

በምድር ያሠሩት:- ከምእመናን ልቡና እያወጡ ያሠሩት ጠላት ዲያብሎስ፣ ርትዕት የሆነችውን ሃይማኖት ሊያጣምም ሲሞክር በስንዴው አዝመራ እንክርዳድን ሲዘራ ተገኝቶ አውግዘው የለዩት መናፍቅ በሰማያትም የታሠረ፣ የተለየ፣ የተወገዘ ይሆናል። እንኳንስ በሐዲስ ኪዳን ጥንት በሕገ ልቡና ዘመን አብርሃም የባረከውን ይስሐቅ፤ ይስሐቅ የባረከውን ያዕቆብ እግዚአብሔርም በሰማያት በረከት ሲባርካቸው የለዩዋቸውን እስማኤልንና ዔሳውን ደግሞ ከበረከቱ ለይቷቸዋል።

በምድር የፈታኸው:- ዓለም በበደል በኃጢአት የታሠረ ነውና የኃጢአትን ገመድ በወንጌል ሰይፋቸው በጣጥሰው በፊት ቢፈቱለት በንስሐ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ከበደል እሥራት ቢፈቱት በሰማያት ፍርድ፣ በሰማያት መዝገብ የተፈታ ነፃም የወጣ ይሆናል።

ይህ ሥልጣነ ክህነት ለቅዱስ ጴጥሮስ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ሐዋርያትን ሁሉ ወክሎ የተቀበለው ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ በወንጌል ብርሃን የኃጢአትን ጨለማ እንዲገልጡ፣ የታሠሩትን እንዲፈቱ ጌታችን ሐዋርያትን ሁሉ ወደ ዓለም ባልላከም ነበር። መላክ የሚገባው ቅዱስ ጴጥሮስ ብቻ ነበርና።

ይህንንም ሲያረጋግጥልን ጌታችን ለሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ሀብት ባደለበት፣ ሥልጣነ ክህነትን (አስቀድሞ የነገራቸውን፣ ያበሠራቸውን፣ ቃል ኪዳንም የገባላቸውን) ሲሰጣቸው ‹እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውንም ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል። የያዛችሁባቸውም ተይዞባቸዋል።› በማለት ቀድሞ በቃልና የተመሠለ ሥልጣናቸውን አብራርቶ ተረጉሞ ነገሮቸዋል። ዮሐ.20፥22–23።

ይህም ሥልጣን በአንብሮተ ዕድ ለቤተ ክርስቲያን ካህናት ተላልፎአል ይተላለፋልም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንኳን ከተጠመቀ በኋላ ይህንን ሀብት በአንብሮተ ዕድ አግኝቶታል። የሐዋ.9፥12። እርሱም በፊንታው እነ ቅዱስ ጢሞቴዎስንና ቲቶን በዚሁ ሥልጣን ሾሟቸዋል። የመንፈስ ቅዱስ ልጁን ጢሞቴዎስንም ‹በማንም ላይ ፈጥነህ እጅህን አትጫን› በማለት ያዘዘው ይህንን ሥልጣነ ክህነት ለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ለተመረጡ፣ ራሳቸውንም ወደው ፈቅደው ለለዩ፣ ለምእመናን አባት፣ መሪ መሆን ለሚችሉ ብቻ መስጠት ስላለበት ነው።

ከሁሉም በላይ ደግሞ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያርግበት ሰዓት ‹እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ› ማቴ.28፥20 በማለት የተናገረው ሐዋርያት ሳይሞቱ በዚህች ምድር የሚኖሩ ሆነው ሳይሆን በእነርሱ እግር ተተክተው ቤተክርስቲያንን ለሚያገለግሉ ካህናት ጭምር ይህንን የሐዋርያት ሥልጣን ማደሉን ሲናገር ነው።

## የሐዋርያት ትምህርት – ለቤተ ክርስቲያን

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተሰበከችው በሐዋርያት በመሆኑ ትምህርተ ሐዋርያት ከክርስቶስ የተገኘ የቤተ ክርስቲያን እምነት መነሻ ነው። የሐዋርያት ትምህርት በዓይን ያዩት፣ በጆሮ የሰሙት፣ በእጅ የዳሰሱት በኋላም በመንፈስ ቅዱስ የተረዱት ነውና እውነተኛነቱ የተረጋገጠ ነው።

በመድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ‹ሂዱና አስተምሩ› ተብለው የታዘዙ ናቸውና መልእክተኛነታቸው የታመነ ነው። የእነዚህን ሐዋርያት ትምህርት ቤተ ክርስቲያን 1.በትውፊት 2. በመጻሕፍት አግኝታዋለች።



### 1. በትውፊት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ ‹ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን፣ የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ› ፊልጵ 4፥9። በማለት እንደተናገረው ሐዋርያት ያስተማሩት በመጻሕፍት ብቻ ሳይሆን ከኑሮአቸው፣ ከተግባራቸው፣ ከገድላቸው እና ከትሩፋታቸው ጭምር በመሆኑ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያዊው ትውፊት ትጠቀምበታለች።

### 2. በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

የሐዋርያትን እውነተኛ ትምህርት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጠብቃ በመያዝ ለዓለም አበርክታዋለች። ሐዋርያት ወንጌልንና መልእክታትን የጻፉት ያስረከቡትም ለቤተ ክርስቲያን ነው። የሚገኘውም በቤተ ክርስቲያን ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤትም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት።

ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የትምህርቷ፣ የሥርዓቷና የሕግ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ የሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው።

## የሐዋርያት ዝርዝር

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሐዋርያት ዝርዝር በአራት ቦታዎች ተጽፎ ይገኛል። እነዚህ ዝርዝሮች በማቴዎስ፣ በማርቆስና በሉቃስ ወንጌሎች ሲገኙ በዮሐንስ ወንጌል ግን ዝርዝሩ አልሠፈረም። የመጨረሻው ዝርዝር የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ ላይ ነው።

| ማቴዎስ 10፥1–4፤ | ማርቆስ 3፥16–19፤ | ሉቃስ 6፥13–16፤ | የሐዋ.ሥራ 1፥13–14 |
|---|---|---|---|
| ጴጥሮስ | ጴጥሮስ | ጴጥሮስ | ጴጥሮስ |
| እንድርያስ | ያዕቆብ ወ/ዘብዴዎስ | እንድርያስ | ዮሐንስ |
| ያዕቆብ ወ/ዘብዴ | ዮሐንስ | ያዕቆብ ወ/ዘብዴ | ያዕቆብ ወ/ዘብዴዎስ |
| ዮሐንስ | እንድርያስ | ዮሐንስ | እንድርያስ |
| ፊልጶስ | ፊልጶስ | ፊልጶስ | ፊልጶስ |
| በርተሎሜዎስ | በርተሎሜዎስ | በርተሎሜዎስ | ቶማስ |
| ቶማስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | በርተሎሜዎስ |
| ማቴዎስ | ቶማስ | ቶማስ | ማቴዎስ |
| ያዕቆብ ወ/እልፍ. | ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ | ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ | ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ |
| ታዴዎስ | ታዴዎስ | ስምዖን ቀነናዊው | ስምዖን ቀነናዊው |
| ስምዖን ቀነናዊው | ስምዖን ቀነናዊው | የያዕቆብ ይሁዳ | የያዕቆብ ይሁዳ |
| ያስቆርቱ ይሁዳ | ያስቆርቱ ይሁዳ | ያስቆርቱ ይሁዳ | – |

ይህ የሐዋርያት ዝርዝር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ሳይሆን በቤተክርስቲያን አዋልድ መጻሕፍትም በልዩ ልዩ ቦታ ይገኛል። ለምሳሌ ያህልም የገድለ ሐዋርያትንና የቅዳሴ ማርያምን አቅርበናል።

| ገድለ ሐዋርያት[5] | ቅዳሴ ማርያም[6] |
|---|---|
| ጴጥሮስ | ጴጥሮስ |
| እንድርያስ | ያዕቆብ |
| ያዕቆብ ወ/ዘብዴዎስ | ዮሐንስ |
| ዮሐንስ | እንድርያስ |
| ፊልጶስ | ፊልጶስ |
| በርተሎሜዎስ | በርተሎሜዎስ |
| ማቴዎስ | ቶማስ |
| ቶማስ | ማቴዎስ |
| ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ | ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ |
| ታዴዎስ | ታዴዎስ |
| ስምዖን ቀነናዊው | ስምዖን |
| ያስቆሮቱ ይሁዳ | ማትያስ |

ከ12 ሐዋርያት መካከል ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ያዕቆብ፣ እንድርያስ፣ ቶማስ፣ ማቴዎስ፣ ስምዖን ቀነናዊ፣ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ፣ በርተሎሜዎስና ፊልጶስ በአራቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ዝርዝሮችና በሁለቱ አዋልድ መጻሕፍት ላይ ስማቸው ሳይለወጥ የሚገኝ ሲሆን ያስቆሮቱ ይሁዳ ደግሞ ታንቆ በመሞቱ የተነሣ በሐዋርያት ሥራ ላይ ስሙ ባይጠቀስም በሦስቱ ወንጌላውያን መጻሕፍትና በገድለ ሐዋርያት ላይ ተጽፎአል።

[5] ዝኒ ከማሁ

[6] ቅዳሴ ማርያም በተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት በ1984 የታተመ



ሐዋርያው ማትያስ የተተካው በዚሁ ሐዋርያ ምትክ ነው። በቅዳሴ ማርያም ላይም አባሕርያቆስ ስሙን ጠቅሶት ይገኛል።

ታዴዎስ ከአራቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ዝርዝሮች በሁለቱ እና በሁለቱ አዋልድ መጻሕፍት ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ የያዕቆብ ይሁዳ (ከአስቆሮቱ ይሁዳ ለመለየት) ደግሞ በቀሩት ሁለቱ ማለትም በሉቃስ ወንጌልና በሐዋርያት ሥራ ላይ ተመዝግቦአል።

ማቴዎስና ማርቆስ እንዲሁም ገድለ ሐዋርያትና ቅዳሴ ማርያም ታዴዎስ በሚለው ስሙ ሲጠሩት፤ ወንጌላዊው ሉቃስ ግን በሁለቱም መጻሕፍቱ (በወንጌሉና በየሐዋርያት ሥራ) ‹የያዕቆብ ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ› ፤ በማለት ይጠቅሰዋል።

በእሥራኤላውያን ዘንድ ከአንድ በላይ ስም የተለመደ ነው። ምክንያቱም ከብዙ ሕዝብ ጋር በመኖራቸውና የብዙ ቋንቋ ማለትም የግሪክ፣ የዕብራይስጥ፣ የአራማይክ፣ የሮማይስጥ፣ ወዘተ. ተናጋሪዎች በመሆናቸው በልዩ ልዩ ቋንቋ ብዙ ስሞች አሏቸው።

ለምሳሌ

- ጴጥሮስ (ላቲን)፣ ስምዖን (ዕብራይስጥ)፣ ኬፋ (አራማይክ)
- ቶማስ (ዕብራ)፣ ዲዲሞስ (በግሪክ መንታ ማለት ነው።)
- ማቴዎስ–ሌዊ
- ማርቆስ (ሮማይስጥ)፣ ዮሐንስ (ዕብራ)
- ሳውል (ዕብራ)፣ ጳውሎስ (ግሪክ)

በልዩ ልዩ ስም ተጠርተዋል። በዚህም መሠረት ታዴዎስም ‹ልብድዮስ–የያዕቆብ ይሁዳ› ተብሎ በሦስት ስም ተጠርቷል።

ናትናኤል

በዮሐ.1፥44–52 ላይ እንደምናገኘው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊልጶስን በጠራው ጊዜ ፊልጶስም ናትናኤልን ጠርቶት ነበር። ጌታም ለናትናኤል የሕይወቱን ነገር በነገረው ጊዜ ናትናኤል ተደነቀ። በዚህም ሰዓት ጌታችን ‹ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ› በማለት አስከትሎት ነበር። ነገር ግን የናትናኤል ስም

በሐዋርያት ዝርዝር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ሆነ በአዋልድ መጻሕፍት አልተጠቀሰም። ታድያ ናትናኤል የትደረሰ?

የምዕራቡ ዓለም ሊቃውንት ናትናኤል ማለት በርተሎሜዎስ ነው በማለት ያስተምራሉ።[7] የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳት መጻሕፍት ግን በርተሎሜዎስ የሌላ ሐዋርያ ስም ሲሆን ናትናኤል የስምዖን ቀነናዊው ሌላ ስሙ ነው።[8] በማለት ይገልጣሉ።

ናትናኤል ምሁረ ኦሪት እንደነበር አውግስጢኖስ ጽፎአል። ስምዖን ቀነናዊው ለመባል የበቃውም በወቅቱ በምድረ ይሁዳ ይካሄድ የነበረው የከነዓናውያን ንቅናቄ አባል የነበረ በመሆኑ ነው። ለዚህ ያበቃው ለኦሪትና ለሀገሩ የነበረው ቅናት ሳይሆን አይቀርም። በመሆኑም የናትናኤልና የስምዖን ጠባይ በዚህ ይመሳሰላል። ስለዚህም ናትናኤል ስምዖን ነው ለማለት ያስኬዳል።

## ያዕቆቦች

በሐዋርያት ዝርዝር ውስጥ ሁለት ያዕቆቦች ተጠቅሰዋል።

1. ያዕቆብ ታላቁ፣ ወልደ ነጎድጓድ፣ ወልደ ዘብዴዎስ በሄሮድስ አግሪጳ ተይዞ በ44 ዓ.ም በኢየሩሳሌም በሰማዕትነት ያረፈው።

2. ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ

የመጀመሪያው ያዕቆብ በስሙም በግብሩም በሊቃውንቱ ዘንድ አከራካሪ አልሆነም ነገር ግን ሁለተኛውን ያዕቆብ ብዙዎች ከያዕቆብ የጌታ ወንድም የተለየ አድርገው ይጽፉታል። (ገላ.1፥19)

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የጌታ ወንድሞች በመባል ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ስምዖን ተጠርተዋል። ማር.6፥13። ስለነዚህ የጌታ ወንድሞች ከጥንት ጀምሮ በሊቃውንቱ ዘንድ ሁለት ዓይነት አመለካከት አለ።

1. ዮሴፍ ከሟች ሚስቱ የወለዳቸውና ከጌታ ጋር አብረው ያደጉ ናቸው። ይህን መልስ የሰጠው አባታችን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ነው። ኤጲፋንዮስ በ382 ዓ.ም ተነሥቶ እመቤታችን ከጌታ ሌላ ልጆች

---

7 Dictionary of Saints p. 58-59, Oxford Christian Dictionary p. 136

8 ገድለ ሐዋርያት ገጽ 49–50፤ ለንክሳር ሐምሌ 10፤ ትንሣኤ 138/82 ገጽ 19–20። ትንሣኤ 70/75 ገጽ 13። (St.Jerome, PL 23; 763; 26; 63)



መልዳለች የሚለውንና ዛሬ ድረስ መናፍቃን የሚነዙትን የክህደት ትምህርት ማስተማር ለጀመረው ሄሊቪዲየስ ለተባለው ላቲናዊ መናፍቅ በሰጠው መልስ ላይ የጌታ ወንድሞች የተባሉት ዮሴፍ ከሟች ሚስቱ የወለዳቸው እንደሆኑ አስተምሮ ነበር።

ይህ ትምህርት የተሰጠው ቃል በቃል ሲነገር የመጣውን ትውፊት መሠረት በማድረግ ሲሆን በግብፅ፣ በሶርያ፣ በግሪክ እና ኢትዮጵያ አበው በመጻሕፍትም ተጠቅሶ ይገኛል። አውሳብዮስ ዘቂሣርያ፣ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቄርሎስ ዘእስክንድርያም ይህን ትምህርት አስተምረዋል።

2. የአክስቱ ልጆች ናቸው።

ይህንን ትምህርት ለሄሊቪዲየስ በሰጠው መልስ ላይ ያሠፈረው አባ ጀሮም ነው። አባ ጀሮም ለዚህ ትምህርቱ መሠረት ያደረገው መጽሐፍ ቅዱስን ሲሆን አቀራረቡም እንደሚከተለው ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመከራው ሰዓት የተከተሉትን አንስት ወንጌላውያን በየክፍላቸው ጽፈዋቸዋል።

- ማቴዎስ – ኢየሱስንም እያገለገሉ ከገሊላ የተከተሉት ብዙ ሴቶች በሩቅ ሆነው ሲመለከቱ በዚያ ነበሩ። ከእነርሱም መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም የዘብዴዎስም የልጆቹ እናት ነበሩ። ማቴ.27፥55–56።
- ማርቆስ – ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብም እናት ማርያም፣ ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቶ ገዙ። ማር.16፥1–2።
- ሉቃስ – ይህንም ለሐዋርያት የነገሩዋቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና የያዕቆብም እናት ማርያም... ሉቃ.24፥10
- ዮሐንስ – ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ፣ የእናቱም እኅት የቀለዮጳም ሚስት ማርያም፣ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር። ዮሐ.19፥25።

ከላይ በአራቱም ወንጌላውያን እንዳየነው በጌታችን መከራ መስቀል ጊዜ ከእመቤታችን ሌላ ሁለት ማርያሞች ነበሩ።

1. መግደላዊት ማርያም (አራቱም ወንጌላውያን በዚሁ ስም ጠርተዋታል።)

2. ማቴዎስ – የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም

- ማርቆስ – የያዕቆብ እናት ማርያም
- ዮሐንስ – የእናቱ እኅት የቀለዮጳ ሚስት ማርያም በማለት የጠሯት ሁለተኛዋ ናት።

በዚህም መሠረት የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም የተባለችው ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ የእናቱ እኅት ያላት የቀለዮጳሚስት ማርያም ናት።

በመሆኑም ያዕቆብ ለጌታ የአክስቱ ልጅ ነው። አባቱ ቀለዮጳ (እልፍዮስ ሲሆን) እናቱ ማርያም ትባላለች። ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍት ቀለዮጳ የዮሴፍ ወንድም ሲሆን ማርያም ደግሞ የእመቤታችን እኅት መሆንዋን ጽፈዋል።[9] ከአዋልድ መጻሕፍት አንዱ የሆነው ትርጓሜ ወንጌል የእመቤታችን እናት ሐና ካረፈች በኋላ ኢያቄም ሌላ ሚስት አግብቶ የቀለዮጳ ሚስት የሆነችውን ማርያምን እንደወለደ ይዘግባል።[10]

ቅዱስ ያዕቆብ የጌታ ወንድም ለመባል የበቃው፣ አባቱ ቀለዮጳ የዮሴፍ ወንድም በመሆኑ እናቱም የእመቤታችን እኅት ስለሆነች በዝምድናው ቅርበት ሲሆን፤ በሌላ በኩልም ከጌታችን ጋር በዮሴፍ ቤት በአንድነት በማደጋቸው ነው።

ቀለዮጳ የግሪክ ስም ሲሆን እልፍዮስ ደግሞ ዕብራዊ ስሙ ነው። ሁለት ስም ለእሥራኤል ልማዳቸው ነው። እንግዲህ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉት ያዕቆቦች ሁለት እንጂ ሦስት አይደሉም። እነርሱም:-

1. ያዕቆብ ወልደ ቀለዮጳ፣ ወልደ እልፍዮስ፣ የጌታ ወንድም፣ ታናሹ ያዕቆብ (ከያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ በዕድሜ ስለሚያንስ)

2. ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ፣ የዮሐንስ ወንድም፣ ታላቁ ያዕቆብ።

---

9 Hegesib 29 Eusebius Hist Eccl. 1.III. C. 11; Ibid III.C.32

10 ትርጓሜ ወንጌል ገጽ 103፤ በአይሁድ ዘንድ በአንድ ቤተሰብ በአንድ ዓይነት ስም የሚጠሩ ሰዎች መኖር ልማዳቸው ነው። ለምሳሌ መጥምቁ ዮሐንስን በአባቱ ስም ዘካርያስ ሊሉት ፈልገው ነበር።



## የሐዋርያት ክብር በቤተ ክርስቲያን

ቅዱሳን ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን ቀዳማውያን አበው፣ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተሠዉ፤ ሕይወታቸውን ለቤተ ክርስቲያን የሰጡ፣ በመሆናቸው በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ልዩ ክብር አላቸው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም በልዩ ልዩ መንገድ ታከብራቸዋለች።

ሀ. ትምህርታቸውን ሳታዛባ በመጠበቅ:- ብዙዎች በልዩ ልዩ ዘመን ከእውነተኛው ትምህርተ ሐዋርያት አፈንግጠዋል። በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በሲሞን መሠርይ መሥራችነት[11] ከተነሡት ግኖስቲኮች ጀምሮ በኋላ ዘመን እስከፈለቁት አርዮሳውያን፣ መቅዶንዮሳውያን፣ ሰባልዮሳውያን፣ ንስጥርሳውያን፣ መሐመዳውያንና ሉተራውያን ድረስ ሐዋርያዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያቆየችላቸውን ትምህርተ ሐዋርያት፣ ትውፊተ ሐዋርያትን ትተው በገዛ ፍልስፍናቸውና ምኞታቸው ፈታድ ሲመሩ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ግን የሐዋርያትን ትምህርትና ትውፊት ጠብቃ እስከዛሬ ኑራለች።

ለ. ገድላቸውን በመመስከር:- አበው ሐዋርያት የክርስትና ኑሮ ፋና ወጊዎች በመሆናቸው ከክህድያን፣ ከመናፍቃን፣ ከአረማውያን፣ ከትዕቢተኛ መኳንንትና መሳፍንት፣ ከዚህ ዓለም የዲያብሎስ አሽከላ ጋር ተጋድለው በደማቸው ቀለም በአጥንታቸው ብዕር ነው – ክርስትናን የጻፉት። ጽፈውም ብቻ ሳይሆን ኑረው ቀም ሰው አሳይተውናል። ‹እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም› እንዳለ ልበ አምላክ ዳዊት።

በሹክሹክታ የተማሩትን በጩኸት፣ በጨለማ የተማሩትን በብርሃን፣ በቤት የተማሩትን በሰገነት ገልጠውታል። በዚህ ጊዜም ጨለማ የሰፈነበት ዓለም የወንጌልን ብርሃን መቀበል ተስኖት ፍዳ መከራ አብዝቶባቸዋል። ይህ ያደረጉት ተጋድሎ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ በገድላቸው፣ ወዘተ ይገኛል። ጽፎ መረከብ ማስተማርም ብቻ ሳይሆን በእግራቸው የተተኩ አበውም መንገዳቸውን ተከትለውታል።

---

11 Oxford Christian Dictionary p. 1258

ዛሬም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን ተጋድሎ ለትውልድ ሁሉ ትመሰክረዋለች። ልጆቿ አሠረ ፍኖታቸውን እንዲከተሉ ታስተምራቸዋለች። ልጆቿም «የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ። ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእሥራትና በወኅኒ ተፈተኑ። በመጋዝ ተሰነጠቁ። በሠይፍ ተገድለው ሞቱ። ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ። ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ።» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ ዕብራ.11፥38።

ስለ ወንጌል ክብር፣ ስለ ርትዕት ሃይማኖት የተሠዉ፤ የቤተ ክርስቲያን መዓዛ የሆኑ ሐዋርያትን ገድል በተግባር ያውሉታል።

ሐ. በዓላቸውን በማክበር:- ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ሐዋርያት የሰማዕትነታቸውን (ከቅዱስ ዮሐንስ በቀር፤ እርሱ ግን ሳይሞት ወደ ብሔረሕያዋን ስለተወሰደ የተወለደበት ይከበራል። ዮሐ.21፥22።) በዓል ታከብራለች። የጻድቅ ሞቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበረ ነውና።

ይህ የሐዋርያት በዓል ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ጀምሮ ይከበር ነበር። የሰርምኔሱ ሊቀ ጳጳስ ፖሊካርፐስ ሐዋርያት በሰማዕትነት ያረፉበት በዓል በጥንታውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ይከበር እንደነበረ በ2ኛው መ/ክ/ዘመን ላይ ጽፎ ነበር።[12] ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሐዋርያት በዓል በድምቀት በቤተ ክርስቲያን ይከበራል። በቤተ ክርስቲያናችን የበዓላት ቀኖና መሠረት የቅዱሳን ሐዋርያት በዓል የሚከበርበት ዕለት እንደሚከተለው ነው።

| | |
|---|---|
| 1. ዮሐንስ ወንጌላዊ | መስከረም 4 (ልደቱ) |
| 2. ሐዋርያው ማቴዎስ | ጥቅምት 12 |
| 3. ሐዋርያው ፊልጶስ | ኅዳር 18 |
| 4. ሐዋርያው እንድርያስ | ታኅሣስ 4 |
| 5. ሐዋርያው ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ | የካቲት 10 |
| 6. ሐዋርያው ማትያስ | መጋቢት 8 |
| 7. ሐዋርያው ያዕቆብ ወ/ዘብዴዎስ | ሚያዝያ 17 |
| 8. ሐዋርያው በርተሎሜዎስ | መስከረም 1 |
| 9. ሐዋርያው ስምዖን ቀነናዊ/ናትናኤል | ግንቦት 15 |
| 10. ሐዋርያው ቶማስ | ግንቦት 26 |
| 11. ሐዋርያው ታዴዎስ | ሐምሌ 2 |
| 12. ሐዋርያው ጴጥሮስ | ሐምሌ 5 |
| 13. ሐዋርያው ጳውሎስ | ሐምሌ 5 |

[12] Dictionary of Saints,p.8



መ. በስማቸው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በመሰየም።

አስቀድሞ እግዚአብሔር በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል «ሰንበቴን ስለሚጠብቁ፣ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ፣ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላል:- በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ» ኢሳ.56፥4 ብሎ ለቅዱሳን ልጆቹ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ታቦት ተቀርጾላቸው፣ በስማቸው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶላቸው ይከበራሉ።

ሠ. በስማቸው በመጠራት:- ቅዱሳን ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን መሠረት የክርስትና ፈር ቀዳጅ ናቸውና ዘወትር ሊታሰቡ ይገባል። በመሆኑም በክርስቲያኖች ዘንድ ክርስትና ከተነሣበት ዕለት ጀምሮ በስማቸው መጠራት ባህላችን ነው።

1. ሥዕላቸውን በማክበር

ከጥንቱ የካታኮምብ (ግበበምድር) ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ የቅዱሳን ሐዋርያት ሥዕል ለሥርዓተ አምልኮ (ለጸሎት፣ ለምልጃና ለምስጋና) መጠቀም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው። ከዚያም በኋላ እስከ ዛሬ ድረስ የሐዋርያት ሥዕል በየአጥቢያ ቤተክርስቲያኑ

ይገኛል። ምእመናንም አስቀድመው የልብሳቸውን ዘርፍ እየነኩ በጥላቸው ላይ እየተኙ ይፈወሱ እንደነበሩት ሁሉ የሐዋ.5፥15፤ 19፥11 ዛሬም ሥዕላቸውን እየዳሰሱ ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስ ያገኙበታል።

ሰ. በአማላጅነታቸው በመታመን

የቅዱሳን አማላጅነት በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርትና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተለያዩ ቦታዎች ተገልጦ ይገኛል። በዚህም መሠረት የቅዱሳን ሐዋርያት አማላጅነትም ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ጀምሮ የታወቀ የታመነም ነው። በሮማ መንግሥት ጨካኝነት የተነሣ በግበበምድር ለመኖር የተገደዱት ጥንታውያን ክርስቲያኖች፤ በግበበ ምድሩ ግድግዳ ላይ በጻፉት ጸሎታቸው፤

«ጳውሎስና ጴጥሮስ ሆይ ድል እናገኝ ዘንድ ጸልዩልን» ብለው የተናገሩት ተገኝቷል።[13]

13 Dictionary of Saints p. 8



ምዕራፍ ሁለት

# የሐዋርያት ታሪክ ሥራና ገድል

የቅዱሳን ሐዋርያት ታሪክ ገድልና ሥራ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በሙሉ አልሰፈረም። አርባዕቱ ወንጌላት ሐዋርያት እንዴት እንደተጠሩና እስከ ዕርገት ድረስ የነበራቸውን ሁኔታ ሲጽፉ፤ ወንጌላዊው ሉቃስ ደግሞ የሐዋርያትን (በተለይ አስቀድሞ በኢየሩሳሌም የነበሩትን በኋላም የቅዱስ ጳውሎስን ጉዞ በመከተል) ታሪክ እስከ 60ዎቹ መጀመሪያ ያለውን ጽፏል።

ከዚህ በመለስ ያለውን የሐዋርያት ታሪክ ለማወቅ ግን ዋናው ምንጩ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ መጻሕፍት ናቸው። የሐዋርያት ደቀ መዛሙርት እነ ፓፒያስ፣ ፖሊካርፐስ፣ አግናጥዮስ፣ ቀሌምንጦስ ዘሮም ወዘተ. የአባቶቻቸውን ታሪክ ጽፈው አቆይተውልናል። በኋላ ጊዜም በ2ኛውና በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሱት የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍት እነአውሳብዮስ፣ ሩፊኖስ፣ ጀሮም፣ ወዘተ. በትውፊት የተቀበሉትን መዝግበው አልፈዋል።

ቅዱሳን ሐዋርያት ገድላቸው የተጻፈላቸው፤ በዓላቸው የተከበረላቸው የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ናቸው። እኛም በአጭሩ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

## 1. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ

በገሊላ ባሕር ዳር በምትገኘው በቤተሳይዳ ተወለደ። የአባቱ ስም ዮና ይባላል። ከአምስት ዓመቱ ጀምሮ ያደገው በቅፍርናሆም ከተማ ሲሆን በጉልማሳነቱ ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር በገሊላ ባሕር ዓሳ ማሥገር ጀመረ። ለደቀመዝሙርነት ሲመረጥ ዕድሜው 55 ዓመት

እንደነበረ ይነገራል።[14] ወደ ጌታችን ያመጣውም ወንድሙ እንድርያስ ነው።

ቅዱስ ጴጥሮስ በርናባስ እና ወንጌላዊው ማርቆስ ቤተ ዘመድ ናቸው። የማርቆስ አባት አርሶጦቡሎስ እና በርናባስ በእናት የሚገናኙ ወንድማማች ናቸው። ቅዱስ ጴጥሮስ ያገባው የበርናባስና የአርስጦቡሎስን እኅት ስለነበር በጋብቻ ይዛመዳሉ።[15]

ቅዱስ ጴጥሮስ ለሐዋርያነት ሲጠራ መተዳደሪያው የነበረውን መረቡንና ታንኳውን እንዲሁም አባቱን እርግፍ አድርጎ ትቶ ጌታውን የተከተለ ሐዋርያ ነው።

የመጀመሪያ ስሙ ስምዖን ሲሆን ይህንንም እናቱ በነገዱ ስም እንዳወጣችለት ይነገራል። በቂሳርያ ከተማ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹ማን ትሉኛላችሁ?› ብሎ በጠየቀ ጊዜ ‹አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ› ብሎ ለአይሁድ ሊታወቅ የተሰወረውን ምሥጢረ ተዋሕዶ ገልጦ በመመስከሩ ጌታችን ‹አንተ ጴጥሮስ ነህ› ብሎታል ይህም በላቲን ቋንቋ ዐለት ማለት ነው። በአራማይክ ደግሞ ኬፋ ይባላል።

ቅዱስ ጴጥሮስ ከአዕማድ ወይንም የምሥጢር ሐዋርያት ከእነ ዮሐንስን እና ያዕቆብ ጋር የሚቆጠር ነው። ከሐዋርያት ሁሉ ቀደም ቀደም የማለት ባሕርይ ነበረው። ጌታ በጥብርያዶስ ባሕር ላይ ሌሊት በእግሩ ሲመጣ ቢመለከት ወደ አንተ እመጣ ዘንድ እዘዘኝ በማለት ካስፈቀደ በኋላ ወደ ጌታ ለመምጣት መንገድ ጀምሮ በመሐል ቤት ጥርጣሬ ገባውና መስጠም ስለጀመረ ጌታችን ‹ያመንክ እንጂ ያላመንክ አትሁን› ብሎ ገስፆ ከመስጠም አድኖታል። ማቴ.14፥22–33።

በቅፍርናሆም ጉባኤ ጌታችን ምሥጢረ ቁርባንን ሲያስተምር፣ አይሁድ ስላልገባቸው ወደ ኋላ አፈገፈጉ። ከደቀ መዛሙርቱም «ብዙዎቹ ወደ ኋላ ተመለሱ» በዚህን ጊዜ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁ?» ብሎ ሐዋርያትን ጠየቃቸው። በዚህ ሰዓት «ጌታ ሆይ ወደማን እንሄዳለን?

14 ዜና ሐዋርያት ገፅ 3–15
15 መጽሐተ እሚን ገፅ 35



አንተ የዘላለም የሕይወት ቃል አለህ። እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ እናምናለን» በማለት ሐዋርያትን ወክሎ የመለሰ እርሱ ነው። ዮሐ.6፥66–68።

ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን ይወድ ነበር። ፍቅሩ ግን ቅንዓት የተቀላቀለበት በመሆኑ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የሞቱን ነገር ቀድሞ ሲነግራቸው አይሁንብህ በማለት ተከራክሯል። ማቴ.16፥23 በኋላም «ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም» ብሎ በራሱ ቅንዓት ተማምኖ ተናግር ነበር። ጌታችን «ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» እያለው እንኳን «ከአንተ ጋር መሞት እንኳን የሚያስፈልገኝ ቢሆን ከቶ አልክድህም» በማለት የተናገረ ሰው ነው። ማቴ.26፥34።

ቅዱስ ጴጥሮስ አስቀድሞ የተናገረውን ቃል ለመጠበቅ ሞክሮ ነበር። ጌታ ዛሬ ‹የሰው ልጅ አሳልፎ ይሰጣል› ብሎ አስተምሮአቸው ነበርና መከላከያ ይሆነኛል ብሎ ሠይፍ ደብቆ ይዞ ነበር። የሮም ጭፍሮችም ጌታን ለመያዝ ሲጠጉ የሊቀ ካህናቱን ባርያ (ማልኩስን) በሠይፍ ጆሮውን ቆረጠው። ዮሐ.18፥10 ጌታችን ግን ሞቱ በፍቃዱ ለድኅነተ ዓለም ነውና ‹ሠይፍህን ወደ ሰገባው› መልስ ሲል ገሠፀው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታ በሐናና በቀያፋ፣ በሮማ መኳንንትና ወታደሮች መከራን ሲቀበል በሩቅ ይከተለው ነበር። ጌታን ወደ ሊቀ ካህናት ቀያፋ ግቢ ባስገቡትም ጊዜ ተከትሎ ገባ። ነገር ግን አይሁድ ከሮም ወታደሮች ጋር አብረው በጌታ ላይ ያደርሱት የነበረው መከራ ለሰው ልጅ ኀሊና የሚከብድ በመሆኑ እውነተኛ ፍርድ መጥፋቱን የተመለከተው ጴጥሮስ እሳት ወደሚሞቁት ተጠጋ። በዚያም እያለ የገባውን ቃል አጥፎ ሦስት ጊዜ ጌታን ‹አላውቅም› ብሎ ካደ። ያን ጊዜም ዶሮ ጮኸ።

ቅዱስ ጴጥሮስ የሚታወቅበት ሌላው ትልቁ ነገር ንስሐው ነው። ጌታው የነገረው መድረሱን፣ ቃል የገባለትን አምላኩን መበደሉን እንዳወቀ ከግቢው ወጥቶ አለቀሰ።

ጴጥሮስ በዕድሜው ታላቅነት በሐዋርያት ዘንድ እንደ አባት ይታይ ስለነበር ጌታ በተለያቸው ጊዜ ሐዋርያቱን ሊመግብ ወደሚያውቀው ሙያ ዓሳ ወደ ማሥገሩ ተሠማራ። ጌታም አስቀድሞ

የመረጠው እርሱ ነውና ቢክዳው እንኳን በንስሐ በመመለሱ ንስሐውን መቀበሉን፤ ዛሬም እንደሚወደው ይገልጽለትም ዘንድ በጥብርያያዶስ ባሕር ተገለጠለት።

ሦስት ጊዜ ክዶት ነበርና ቀኖና ሰጠው። አሁን ቅዱስ ጴጥሮስ በራስ መተማመኑ እንዳላዋጣው ዐውቆአል «ትወደኛለህን?» ተብሎ ሲጠየቅ ‹አንተ ታውቃለህ› ነበረ መልሱ። የራሱ ዕውቀት የት እንዳደረሰው ያውቃልና ጌታችንም ኅዳጌ በቀል (በቀልን የሚተው) ነውና ዛሬም እንደሚወደው፣ በንስሐ ተመልሶአልና ዛሬም ለእርሱ የሰጠውን ክብር እንደማያጉድልበት ሲነግረው ‹ግልገሎቼን አሠማራ፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ፣ በጐቼን አሠማራ› በማለት አደራውን አስረከበው። ዮሐ.21፥15–17። ከዚያም በሞቱ እንደምን አድርጐ እግዚአብሔርን እንደሚያከብረው ነግሮት ወደ ሰማያት ዐረገ።

ቅዱስ ጴጥሮስ በአራቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ በተቀመጡት የሐዋርያት ዝርዝር ቀዳሚውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል ይህም:-

1. በሽምግልና አባትነቱ
2. ጌታ በቂሳርያ በሰጠው ቃል ኪዳን
3. የሐዋርያት አፈ ጉባዔ ሆኖ ይናገር ስለነበር
4. በጥብርያዶስ ባሕር በተሰጠው ቃል መሠረት ነው።

በዚህም የተነግ በይሁዳ ምትክ ሌላ ሐዋርያ እንዲመረጥ ሐሳብ ያቀረበ እርሱ ነበር። የሐዋ.1፥16–23። በበዓለ ሃምሳም ለደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ በወረደላቸው ጊዜ ለተሰበሰቡት አይሁድ አፈ ጉባዔ ሆኖ ወንጌልን የሰበከ 3000 ምእመናንንም አሳምኖ የመጀመሪያዋን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም የመሠረተ እርሱ ነው። የሐዋ.2፥14–37።

አስቀድሞ ፈሪ የነበረውና በሊቀ ካህናት ቀያፋ ግቢ ጌታውን የካደው ቅዱስ ጴጥሮስ፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ካገኘ በኋላ ግን በአይሁድ ሸንጐ ድውይ ፈወስክ ተብሎ በተከሰሰ ጊዜ በድፍረት ስለ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ መሰከረ። የሐዋ.4፥1–22። ቆርኔሌዎስን በማጥመቅ ወንጌልን ለአሕዛብ አስቀድሞ የሰበከ ሐዋርያ ነው። የሐዋ.10፥1–11።



ይህ ሐዋርያ ልዑል እግዚአብሔር ባደለው ጸጋ ጥላው እንኳን ድውያንን ይፈውስ ነበር። የሐዋ.5፥15። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ በ50 ዓ.ም አካባቢ በኢየሩሳሌም በተደረገው የሐዋርያት ሲኖዶስ ከአንጾኪያ ክርስቲያኖች ለቀረበው ጥያቄ የመጀመሪያውን መልስ የሰጠው እርሱ ነበር።

ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ መልክና ቁመና ጥንታውያን መዛግብት እንደሚከተለው ያቀርቡታል። «ራቱ ሰፋ ያለ ሲሆን ሪዛምና መካከለኛ ቁመት የነበረው ራሰ በራ ሰው ነው። በማናቸውም ነገር ፈጣንና ቀልጣፋ ነበር።»

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ መሠረት ቅዱስ ጴጥሮስ በፍልስጥኤም፣ በሶርያ፣ በጳንጦን፣ በገላትያ፣ በቀጰዶቅያ፣ በቢታንያ እና በሮሜ ሰብኳል። በሰማዕትነት ያለፈው በሮሜ ከተማ ሲሆን በዚያች ቦታም ለ25 ዓመታት አስተምሯል በማለት የሮማ ሰዎች ይናገራሉ።[16] እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በቅድሚያ ሮሜ የገባው ቅዱስ ጳውሎስ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ የቅዱስ ጴጥሮስን ስም አላነሣውም።

ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህች ከተማ መልእክት እንዲጽፍ ያደረጉት በኔሮን አዋጅ ተሰደው በ52 ዓ.ም ቆሮንቶስ የገቡት አቂላስና ሚስቱ ጵርስቅላ ናቸው። ስለሮም ክርስቲያኖች ቅዱስ ጳውሎስ የሰማው ከእነርሱ ነው። በዚያን ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ በሮም ቢኖር አቂላስና ጵርስቅላ ለቅዱስ ጳውሎስ በነገሩት ነበር።

ቅዱስ ጳውሎስ በአንድ ቦታ ብቻ ስለማያስተምር ለዚያች ሀገር ጳጳሳትን ከሾመላት በኋላ ወደ ስብከቱ ሲሄድ ነበር ቅዱስ ጴጥሮስ ሮም የደረሰው። በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊታዊ ታሪክ መሠረት ግን ቅዱስ ጴጥሮስ ሲጠራ የ55 ዓመት ሰው ሲሆን ከጌታ ጋር ሦስት ዓመት ከሦስት ወር፤ ዞሮ በማስተማር ደግሞ ለ27 ዓመታት ከቆየ በኋላ በሮሜ በማስተማርና በእሥር የቆየው ለአንድ ዓመት ያህል ብቻ ነው። ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ታሪክ አንፃር ስንመለከተው ትክክለኛው ይህ ነው።

16 ይህን መጀመሪያ የገለጠው ቲ.ጀሮም ነው Oxford Christian Dictionary,p. 1050

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሮሜ አንድ ዓመት ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ካስተማረ በኋላ የሮሜ ክርስቲያኖች እየበዙ ከመምጣታቸውም በላይ የክርስትናው ጉዞ እስከ ሮማ ባለሥልጣናት ደረሰ። የኔሮን የቅርብ ባለሥልጣናት የሆኑት የአልቢናስና የአግሪጳ ሚስቶች ወደ ክርስትናው ገቡ። በዚህ ጊዜ ኔሮን ንጉሠ ሮማ በቅንዓት ተነሣባቸው።

ኔሮን በሮም የነገሠው በ54 ዓ.ም ነው። በመንግሥቱ መጀመሪያ ደግ ሰው ነበረ። ነገር ግን በነገሠ በዓመቱ የጨካኝነት ፀባዩ ብቅ ማለት ጀመረ እና የአባቱን ልጅ አስገደለ። በ59 ዓ.ም ደግሞ እናቱን በመርዝ ገደለ። በ63 ዓ.ም እያስተማረ ያሳደገውን መምህሩን፤

በ62 ዓ.ም የልጅነት ሚስቱን አግታቪያን አስገደለ። ከእርስዋ በኋላ ያገባትን ሚስቱንም ፓፒያን በርግጫ ብሎ ገደላት።[17]

ኔሮን በ64 ዓ.ም እርሱ ከከተማው ወጣ ብሎ በሚገኘው ቤተ መንግሥቱ ተቀምጦ የሮማን ከተማ እሳት ለቀቀባት። የሮማ ሕዝብ በደረሰው አደጋ እጅጉን ተቆጣ። ኔሮንም በክርስቲያኖች አመካኘ። በዚህም የተነሣ በሮማ ከተማ ሁለት ዓይነት ወሬ መናፈስ ጀመረ።

የሮማ አማልክት በክርስቲያኖች ሃይማኖት ስለተቆጡ በከተማዋ እሳት አዘነቡባት የሚለው የመጀመሪያው ሲሆን ክርስቲያኖች ሆን ብለው ከተማዋን አቃጥለዋታል የሚለው ደግሞ ሁለተኛው ወሬ ነበር።

የከተማው መጋየት ያበሳጨው የሮማ ሕዝብ፤ ክርስቲያን የሆነውን ሁሉ እያወጣ መግደሉን ተያያዘው። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ሰዓት በእሥር ነበርና ተሠይፎ ዐረፈ። ይህን የሰሙት የአግቢኖስና የአግሪጳ ሚስቶች (የኔሮን ባለሟሎች ነበሩ) ‹ባይሆን አንተ ትረፍልን› ብለው በከተማዋ ግንብ በገመድ አሥረው በቅርጫት በማውረድ ቅፅረ ሮማን ለቅቆ እንዲወጣ አደረጉት።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በአፒየም ጎዳና ጉዞውን ቀጠለ። ሮማን ለቀቀ። እያዘገመ በሸመገለ ጉልበቱ ሲጓዝ አንድ ቀይ ጉልማሳ ወደ እርሱ ሲመጣ አየ። እየቀረበ ሲመጣ ጌታችን መሆኑን ተረዳ።

17 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤የኢትዮጵያ ታሪክ፤ 2ኛ መጽሐፍ፤ ገጽ 174



ወዲያው በፊቱ ተደፋና ‹ጌታዬ ወዴት እየተጓዝክ ነው?› አለና ጠየቀው። ‹ዳግም በሮም ልሰቀል› አለው።

በዚህ ሰዓት ቅዱስ ጴጥሮስ አዘነና እንደገና ወደ ሮማ ተመለሰ። የኔሮን ወታደሮች እየፈለጉት ነበር። ‹እነሆኝ ስቀሉኝ» አለ ቅዱስ ጴጥሮስ። ያን ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስን ይዘው አሠሩት። ከጥቂት ቀናት በኋላም ሮማውያን የመስቀያውን እንጨት አቀረቡለት። ያን ጊዜ ‹እኔ እንደ ጌታዬ ልሰቀል አይገባኝም› በማለት ቁልቁል እንዲሰቅሉት ለመነ። ያለውንም አደረጉለት። ሐምሌ 5 ቀን 67 ዓ.ም በሰማዕትነት ዐረፈ።[18]

ንጉሥ ኔሮን ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ጳውሎስን ከሠዋ በኋላ አልቆናውም። ግፈኛነቱና ሞልቃቃነቱ እየባሰ በመምጣቱ የሮም ሕዝብ ዐመፀበት። በዚህም የተነሣ ሸሽቶ ከተማዋን ለቅቆ ጠፋ። በመጨረሻም መሸሸ ሲሰለቸው የገዛ አሽከሩን ‹እባክህ በሠይፍህ ግደለኝ› በማለት ለምኖ በአሽከሩ ሠይፍ በ68 ዓ.ም ሞተ። ኔሮን ሲሞት ‹ዓለም ዛሬ እንዴት ያለውን አርቲስት አጣች› አለ ይባላል።[19]

አባታችን ቅዱስ ጴጥሮስ የጻፋቸው መልእክታት በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ናቸው። እነዚህም:-

**የመጀመሪያዋ መልእክቱ:-** በሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ ላይ በ35 ዓ.ም አካባቢ በደረሰው መከራ ተሠቀው ለተሰደዱት የአይሁድ ክርስቲያኖች አባት እንደመሆኑ መጠን (ገላ.፪፥8) በእምነታቸው ይጸኑ ዘንድ በ60 ዓ.ም ይህችን መልእክት ጻፈላቸው።

**ሁለተኛዋ መልእክቱ:-** በኔሮን አዋጅ ተይዞ ታሥሮ እያለ (በ67 ዓ.ም አካባቢ) በመከራው ተጨምረው መናፍቃን የክህደት ትምህርት እያስተማሩ ምእመናንን አውከዋቸው ነበርና በታናሽ እስያ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች:-

1. ለዚህ ዓለም ሠራዔ መጋቤ የለውም
2. ትንግኤ ሙታን የለም

18 HE.3.1.2

19 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ 2ኛ መጽሐፍ፤ ገጽ 177

3. ኅልፈተ ሰማይ ወምድር የለም

4. አንድ ጊዜ ካመኑ ምግባር አይጠቅምም። በማለት መናፍቃን ላነሡዋቸው አጠራጣሪ ጥያቄዎች በመልክቱ መልሱን ሰጥቷቸዋል።[20]

## 2. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ (ወልደ ዘብዴዎስ)

ቅዱስ ያዕቆብ የቅዱስ ዮሐንስ (ነባቤ መለኮት) ታላቅ ወንድም ነው። የመጀመሪያ ሥራው ከአባቱ ጋር ዓሣ ማጥመድ ነበር። በገሊላ ባሕር አጠገብ ከአባታቸው ጋር ዓሣ ሲያጠምዱ ከእነ ቅዱስ ጴጥሮስ ቀጥለው ተጠሩ። ወዲያውም አባታቸውንም መረባቸውንም ትተው ጌታን ተከተሉት። እርሱና ወንድሙ ዮሐንስ ፍላጐታቸውና ሥራቸው ታላቅ እና ኃይል የተሞላው ስለነበር (ሉቃ.9፥49፤54፤ ማር.10፥37) ቦኤኔርጌስ (የነጐድጓድ ልጆች) ተብለዋል።

ቅዱስ ያዕቆብ ከአዕማድ (የም/ሥጢር) ሐዋርያት አንዱ በመሆኑ በደብረ ታቦር፣ ጌታችን ወለተ ኢያኢሮስን ሲፈውስና በጌቴሴማኒ ተገኝቷል።

ቅዱስ ያዕቆብ በሐዋርያት ዝርዝር ውስጥ፣ በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል በሦስተኛ ደረጃ፣ በቅዱስ ማርቆስ በሁለተኛ፣ በሉቃስ በሦስተኛ፣ በሐዋርያት ሥራም በሦስተኛ ቦታ ተጽፎአል። ከጌታ ወንድም ያዕቆብ ለመለየትም ታላቁ ያዕቆብ፣ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ እየተባለ ይጠራል።

ቅዱስ ያዕቆብ የኖረው ያረፈውም በኢየሩሳሌም ከተማ ነው። ከ17ኛው መ/ክ/ዘ ወዲህ ግን በሰማዕትነት ከማለፉ በፊት በስፔን እንዳሰበከ የሚናገሩ አንዳንድ መዛግብት ተገኝተዋል።

በዚህችው ሀገር 7 (ሰባት) ልዑካንን ሾሞ ሲመለስ በኢየሩሳሌም ከተማ በሰማዕትነት እንዳለፈ የስፔን ሊቃውንት ይናገራሉ። እንዲያውም በመካከለኛው ዘመን ዐፅሙን ከኢየሩሳሌም አፍልሰው በስፔን ሳንቲያጐ ያሳረፉት መሆናቸውን ያረፈበትን ቦታ እያሳዩ ይመሠክራሉ።[21]

---

20 ኅሩይ ወ/ሥላሴ ግን መልእክቲቱን በ60/66/ የተጻፈች ናት ይላሉ። ዜና ሐዋርያት ገጽ 73።
21 T.D. Kendrick, St. James.in Spain (1960)



## ቅዱስ ያዕቆብና ሁለቱ ጠንቋዮች

ፊሊጦስ የተባለው ጠንቋይ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት ማመኑን ለጓደኛው ለሄርሞጌኒስ ነገረው። ሄርሞጌኒስም የራሱን ታላቅነት ለማሳየት ሲል ፊሊጦስን እጅ እግሩን በአስማት አሣሠረው። ፊሊጦስም የደረሰበትን ሁሉ ዘርዝር ለያዕቆብ ላከበት። ይህን የሰማው ሄርሞጌኒስ ቅዱስ ያዕቆብን አሥረው እንዲያመጡለት በአስማት አጋንንትን ላካቸው። የተላኩት አጋንንት ግን በቅዱስ ያዕቆብ ላይ ኃይል ስላልነበራቸው የተላኩበትን መፈጸም አልቻሉም። ማር.16፥17። እንዲያውም ቅዱስ ያዕቆብ መልሶ ሄርሞጌኒስን እንዲያመጡት አዘዛቸው። እነርሱም እጅ እግሩን ጠፍረው ይዘውት መጡ። ያን ጊዜ ቅዱስ ያዕቆብ ፊሊጦስን ፈታው። ፊሊጦስ ክርስቲያን ሆኗልና ለሄርሞጌኒስ ምሕረት ለመነለት። ቅዱስ ያዕቆብም «እኛ ክፋን በክፉ ስለማንቃወም በሰይጣናት እየተሠቃየህ እንዳትኖር ከክርስቶስ ምሕረትን ለምንንልኻል» በማለት ሄርሞጌኒስን ከታሠረበት እንዲፈታ አደረገ።

አስማተኛው ሄርሞጌኒስ የክርስቲያኖችን ኃይል፣ ርኅራኄና ቸርነት ዓይቶ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት አመነ። ወደ ቤቱም ተመልሶ የጥንቆላ መጻሕፍቱንና ዕቃዎቹን ሁሉ ሰብስቦ በማምጣት በቅዱስ ያዕቆብ እግር ሥር በእሳት አቃጠላቸው።[22]

## የቅዱስ ያዕቆብ ሰማዕትነት

አበው እንደሚያስትምሩን ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በዕድሜ ገፍቶ ስለነበር እንደሌሎች ሐዋርያት ብዙ አልተዘዋወረም። መቀመጫውም በኢየሩሳሌም ከተማ ነበረ።

አንድ አይሁዳዊ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት ስለተናደደ በነገር ከስሶ ለአይሁድ ሸንጐ አቀረበው። ቅዱስ ያዕቆብ ግን ያለፍርሃት እና ያለ ሃፍረት ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሸንጐው ፊት መሠከረ።

በዚህ የተበሳጨው ንጉሥ ሄሮድስ አግሪጳ በ44 ዓ.ም ያዕቆብን በሠይፍ አስገደለው። የሐዋ.12፥2። ቅዱስ ያዕቆብን የከሰሰው

---

22 ገድለ ሐዋርያት። ትንሣኤ ቁ.67/75 ገጽ 11 እና 17።

አይሁዳዊ ግን ለሃይማኖቱ ያለውን ፍቅርና ቆራጥነት በማየቱ ቅዱስ ያዕቆብን በመክሰሱ ተፀፀተ። «እኔ እንደ ቅዱስ ያዕቆብ ክርስቲያን ነኝ። የእርሱን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምናለሁ።» እያለ በየ አደባባዩ እየዞረ መመስከር ጀመረ። በዚህም ምክንያት እርሱም ተሠይፎ በሰማዕትነት ዐረፈ።[23]

ቅዱስ ያዕቆብ ከሐዋርያት መካከል ሰማዕትነቱ በሐዲስ ኪዳን የተጻፈለት ብቸኛ ሐዋርያ ነው። ከሐዋርያት መካከልም መጀመሪያ የሰማዕትነትን አክሊል የተቀዳጀ እርሱ ነው።

## 3. ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ

ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ በመጀመሪያ የተጠራ ሐዋርያ ነው። (ዮሐ.1፥35–45) የቅዱስ ጴጥሮስ ወንድም ሲሆን ትውልዱም በቤተ ሳይዳ ነው። በመጀመሪያ የዮሐንስ መጥምቁ ደቀ መዝሙር ነበረ። ነገር ግን ዮሐንስ «የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሠርይ የእግዚአብሔር በግ» ብሎ ስለጌታችን ሲመሰክር በሰማ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን ተከተለ። ስሙ 12 ጊዜ በወንጌል፣ አንድ ጊዜ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ተገልጦአል። ቅዱስ እንድርያስ በሐዋርያት ዝርዝር ውስጥ በማርቆስና በሐዋርያት ሥራ አራተኛ፣ በማቴዎስና በሉቃስ ወንጌል ደግሞ ሁለተኛ ሆኖ ተቀምጦአል።

ፕሮቶክሌቶስ:- የተጠራ ማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በዚህ ስም ይጠሩት ነበር። አስቀድሞ ለሐዋርያነት ስለተጠራ ሳይሆን አይቀርም።

አስተባባሪ:- ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታ ስለነበረው በሐዋርያት ዘንድ እንደ አስተባባሪ ይቆጠር ነበር።

የቤተሰብ ሐዋርያ:- የጌታችንን ማደርያ ካየ በኋላ ተመልሶ ለወንድሙ ለቅዱስ ጴጥሮስ በመንገሩ እና የምሥራቹን ለቤተሰቡ በማብሠሩ ‹የቤተሰብ ሐዋርያ› ይባላል።

የወጣቶች ሐዋርያ:- በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ከጠዋት እስከ ማታ ሲማር ለቆየው ሕዝብ የሚሆን ምግብ ጌታ ሲጠይቅ እና ፊልጶስ ሐዋርያው ለዚያ ሁሉ የሚበቃ እንጀራ እንደሌለ በመለሰ

23 Eusebius HE



ጊዜ፣ ቅዱስ እንድርያስ ግን አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘውን ጉብዝ (ወጣት) ወደ ጌታ አቅርቦ አስባርኮታል። ዮሐ.6፥6–7። በዚህም ‹የወጣቶች ሐዋርያ› እየተባለ ይጠራል።

የአሕዛብ ወዳጅ ሐዋርያ:- ጌታችንን ለማየት የፈለጉትን ከአሕዛብ ወገን የነበሩትን ግሪኮች ተቀብሎ ከጌታ ጋር አገናኝቷልና። ዮሐ.12፥20–22።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ እንደገለጠው[24] ቅዱስ እንድርያስ ጥንት ስኩቴስ ዛሬ ሩስያ በተባለው ቦታ ወንጌልን ሰብኳል። ይህ ሀገር በጥንቱ ዓለም አጠራር በርባርስ ይባል ነበር። ከጥቁር ባሕር በስተሰሜን በዳኒዩብና ታናዮስ ወንዞች መካከል ይገኛል። ከዚህ በኋላም በቢታንያ፣ በገላትያና ሩማንያ አስተምሯል። የቁስጥንጥንያ የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ መሆኑም ይነገራል።[25]

በመጨረሻ ግሪክ ውስጥ ሲያስተምር በአካያይ አውራጃ ጳጥራስ በተባለች ቦታ በ60 ዓ.ም[26] ታኅሣስ 4 ቀን በሰማዕትነት ዐርፏል። የሀገሩ ሰዎች በጌታ ዓይነት መስቀል ሊሰቅሉት ሲመጡ ‹ጌታዬ በተሰቀለበት ዓይነት መስቀል አትስቀሉኝ› ብሎ የእንግሊዝኛውን ፊደል ኤክስን (x) የመሰለ ቅርጽ ባለው መስቀል ተሰቅሎ ሞተ።

በ357 ዓ.ም ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የሐዋርያው እንድርያስን ዐፅም ከጳጥራስ ወደ ቁስጥንጥንያ አስመጣው። በ8ኛው መ/ክ/ዘ ደግሞ ሬጉሉስ የተባለ መነኩሴ የቀኝ እጁን ጣቶች ወደ ስኮትላንድ ወሰዳቸው። ስኮትላንዶች ጠባቂያችን (patron) ነው ብለው የሚያከብሩት ለዚህ ነው።[27]

## 4. ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ብዙ ስሞች ያሉት ሐዋርያ ነው።

1. ጌታ ይወደው የነበረ (ፍቁረ እግዚእ) በሕይወቱ እና በኑሮው ጌታን ለመምሰል ይጥር ስለነበር ጌታ ይወደው ነበር። በቤተ

24 HE. III.I
25 St. Mark and the School of Alexandria p.14, Dictionary of Saints,p.45
26 Oxford Dictionary of the Christian Church,p.40
27 W.F Skene Celtic Scotland I (1876) pp. 296-99

ክርስቲያን ትውፊት እንደሚነገረውም አንድ ቀን ጌታችን መታጠቂያውን ፈትቶ ባስቀመጠበት ወቅት አንሥቶ በመታጠቁ ፍትወት ሥጋዊ ወደማዊ ጠፍቶለት ኑሮው እንደመላእክት ሆኖለታል።[28]

2. ወልደ ዘብዴዎስ:- የታላቁ ያዕቆብ ታናሽ ወንድም ስለሆነና አባቱ ዘብዴዎስ ስለሚባል ‹ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ› ተብሎ ይጠራል።

3. ወልደ ነጐድጓድ:- ለጌታችን ባለው ኃያል ቅንዓትና ከወንድሙ ጋር ሆነው ባሳዩት የኃይል ሥራ ጌታችን ወልደ ነጐድጓድ (ቦኤኔርጌስ) ብሏቸዋል። ማር.3፥17፤ ሉቃ.9፥49–54። በተጨማሪም ደግሞ የትምህርቱ ጥልቀት፣ ኃይልና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በመግለጡ፣ ‹ወልደ ነጐድጓድ› ተብሎአል።

4. ነባቤ መለኮት:- (ታኦሎጎስ) – ነገረ መለኮትን ከሌሎች በበለጠ አምልቶ አስፍቶ፣ አልቆ አጥልቆ በማስተማሩ ነባቤ መለኮት ተሰኝቷል።

5. አቡቀለምሲስ:- ቃሉ የግሪክ ሲሆን ‹ባለራእይ› ማለት ነው። ኃላፊያትንና መጻዕያትን በራእዩ ስለገለጠ ‹ዮሐንስ አቡቀለምሲስ› ተብሎአል።

6. ቁጹረ ገጽ:- (ፊቱ በሐዘን የተቋጠረ):- በዕለተ ዓርብ በእግረ መስቀሉ ተገኝቶ የጌታችንን መከራ መስቀል በማየቱ ከዚያች ዕለት ጀምሮ ፊቱ በሐዘን ተቋጥሮ ይኖር ስለነበር ይህ ስም ተሰጥቶታል።

የቅዱስ ዮሐንስ ሀገሩ በገሊላ አውራጃ ነው። ከወንድሙ ከቅዱስ ያዕቆብና ከአባቱ ከዘብዴዎስ ጋር ዓሣ እያጠመደ ይኖር ነበር። የቤተ ክርስቲያን ትውፊት እናቱ ማርያም እንደምትባል እና[29] ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት አንዷ እንደ ነበረች ይገልጣል። ማቴ.27፥56።

ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን በመከራው ሰዓት ሳይሸሽ እስከ እግረ መስቀል የተከተለ ሐዋርያ ነው። እንዲያውም በዚያች በዕለተ ዓርብ

28 ትንግሌ፣ ጥቅምት 971/78 ገጽ 9

29 ትንግሌ ቁ.97/78 ገጽ 8



ያየው የጌታ መከራ ትዝ እያለው ተረፈ ዕድሜውን የፈጸመው በዕንባ ነው። የተጠራው ገና በወጣትነት ዕድሜው ሲሆን በዚህ ምድር ላይ የኖረው ለ99 ዓመታት ያህል ነው።

## ቅዱስ ዮሐንስና እመቤታችን

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን እስከ እግረ መስቀሉ በመከተሉ ክርስቲያኖችን ወክሎ የእመቤታችንን እናትነት ከጌታ ተቀብሎአል። ዮሐ.19፥25–27። እመቤታችን ከዮሐንስ ጋር 16 ዓመት ተቀምጣ በ49 ዓ.ም ዐርፋለች። ከዚያም በኋላ በሦስተኛው ቀን እንደ ልጇ ተነሥታ ዐርጋለች። ቅዱስ ዮሐንስ ርቆ ያልሄደው እርሷን የመጠበቅ አደራ ስለነበረበት ነው።

## ቅዱስ ዮሐንስና የጌታ ሥዕል

ለጌታ ሥዕል ምንጭ ከሆኑት አንዱ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው። ጌታ በተሰቀለበት ዘመን የሮማ ንጉሥ የነበረው ጢባርዮስ ቄሣር (14–37 ዓ.ም) ልጁ በሽተኛ ስለነበረ፤ የጌታን የማዳን ሥራ እየሰማ እነ ጲላጦስ የጸፉለትንም ደብዳቤ እየተመለከተ[30] ‹ከዚያ ደግ ሰው መቃብር ልጄን ወስዶ ማን ባዳነልኝ› እያለ ይመኝ ነበር። በመጨረሻም ልጁን ወስደው በጌታ መቃብር ላይ ሲያኖሩት ከሕመሙ ስለተፈወሰለት፣ ለጌታ ያለውን ፍቅር ለመግለጥ የጌታን ሥዕል የሚሥልለት ሰው ሲያፈላልግ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ተገኘና ልክ በዕለተ ዓርብ እንዳየው አድርጎ ሥሎ ሰጠው።[31]

ዮሐንስ ወንጌላዊ እመቤታችን ካረፈች በኋላ ወደ ታናሿ እስያ ሄዶ አስተምሯል። ዋና መንበሩን በኤፌሶን አድርጎ በተለይ በዚያ ዘመን ከአውሮፓ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በሚወስደው መንገድ ዳር በተቆረቆሩት ከተሞች እየተዘዋወረ አብያተ ክርስቲያናትን በማስተከል ጳጳሳትን በመሾም የወንጌልን ብርሃን አብርቶላቸዋል።

በመጨረሻም በጭካኔው በሚታወቀው በንጉሥ ድምጥያኖስ ዘመን (81–96 ዓ.ም) ወንጌል በማስተማሩ የተነሣ በጣዖት አምላኪዎች ተከሶ ለፍርድ ከቀረበ በኋላ በፍል ውኃ ተሰቃይቶ

30 የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በኢትዮጵያ ገጽ፣ 115-116

31 ዝኒ ከማሁ ገጽ 115

በፍጥም ደሴት ግዞት ተፈረደበት። ራእዩን ያየውና የጻፈውም በዚያ ቦታ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ድምጥያኖስ በ96 ዓ.ም ሲገደል ከግዞቱ ተመልሶ ሦስቱን መልእክታቱንና ወንጌሉን እንደጻፈ ይነገራል።[32]

ቅዱስ ዮሐንስ ከሐዋርያት ሁሉ ይልቅ ረዥም ዕድሜ (ወደ 99 ዓመት) በምድር ላይ የቆየ ሐዋርያ ነው። ከሐዋርያት ቀድሞ ያረፈው ታላቅ ወንድሙ ቅዱስ ያዕቆብ ሲሆን ከሐዋርያት መጨረሻ ከዚህ ምድር የተለየው የቅዱስ ያዕቆብ ወንድም ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።

አስቀድሞ ጌታ በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት (ዮሐ.21፥22) ዮሐንስ ሞትን አልቀመሰም። ነገር ግን እንደነ ኤልያስና ሄኖክ ሞትን እንዳያይ እግዚአብሔር ወደ ብሔረ ሕያዋን ወስዶታል።

## ዮሐንስና አስቸጋሪው ሽፍታ

አንድ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ ከኤፈሶን ከተማ ተነሥቶ ክርስቲያናችን ለማስተማር ሲዘዋወር ወደ አንድ ትልቅ ከተማ ገባ። በዚያች ከተማ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ምእመናን፣ ጊልስ ስለሚባልና በአሥራዎቹ ዕድሜ ክልል ስላለ ወጣት ታሪክ ነገሩት። የጊልስ እናትና አባት ሞተዋል። ነገር ግን በጠባዩ፣ በእምነቱ፣ በቅልጥፍናው ክርስቲያኖች ሁሉ ይወዱት ነበርና የሚንከባከበው፣ የሚያስትምረው ካጣ ሊበላሽ ይችላል ብለው ስለፈሩ ለቅዱስ ዮሐንስ አጫወቱት።

ቅዱስ ዮሐንስ ይህን ሲሰማ ወጣቱ ጊልስን ወደ ከተማዋ ጳጳስ ወስደውና «እንደ ልጅህ ተንከባከበው! እውነተኛ ክርስቲያን አድርገህም አሳድገው።» ብሎ ሰጠው የከተማዋ ጳጳስ ደግ ስለነበሩ ጊልስን በደስታ ተቀብለው የቅዱስ ዮሐንስንም ቃል ለመጠበቅ ቃል ገቡለት።

እውነትም የከተማዋ ጳጳስ ጊልስን መንከባከብ ጀመሩ። ዘወትር ያስትምሩታል! ለምግብም የሚቀርበው ከእርሳቸው ጋር ነው። በመጨረሻም ጊልስ የአካባቢው ምእመናን በተሰበሰቡበት ተጠመቀ።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን ነገሮች መቀየር ጀመሩ። እኚያ አባት ሥራ በጣም ስለ በዛባቸው ጊልስን መቼም ተጠምቋል ብለው እንደ በፊቱ

32 Dictionary of Saints, p.189



መቆጣጠሩንና ማስተማሩን ተውት። ጊልስም የለመደውን የአባትነት ፍቅር ሲያጣ ወደ ከተማ ወጣ ብሎ ከእኩዮቹ ጋር መቀራረብ ጀመረ። ጓደኞቹ መልካም አልነበሩም። ጠጭዎች፣ ቁማርተኞች እና ተደባዳቢዎች ነበሩ።

አንድ ቀን ማታ በአንድ መጠጥ ቤት ውስጥ ጊልስና ጓደኞቹ ሲጠጡ አመሹ። ሁሉም ሰክረው በያሉበት ሲወድቁ ጊልስ ብቻ ቀረ። በመጨረሻም የሁሉንም የመጠጥ ሒሳብ ከፍሎ ያለውን ገንዘብ ጨረሰ። በነጋታው ጊልስ ጓደኞቹን ለእናንተ ስል ገንዘቤን ሁሉ አባክንሁ! አሁን ባዶ ኪስ ሆኛለሁ ብሎ ነገራቸው።

ሁሉም ሳቁበትና «ጅሉ ጊልስ! እኛ ገንዘብ ከየት የምናገኝ ይመስልሃል? የምታገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅመህ ስረቅ» አሉት።

በዚህ መሠረት ጊልስና ሁለቱ ጓደኞቹ የአንድ ሰው ቤት ሰብረው ገብተው ገንዘቡንና ጌጣጌጡን ዘረፉ። በዚህም የተነሣ ጊልስ መስረቅ ማለት ቀላል ሥራ ነው ብሎ አመነ። ከዚያ በኋላ ጊልስና ጓደኞቹ የታወቁ ዘራፊዎች ሆኑ። እነርሱ ባሉበት መንገድ ማንም በጤናው ማለፍ አይችልም ነበር። አንድ ቀን ሰው ሲደበድቡ ነፍሱ በእጃቸው ስለ ጠፋች ጊልስና ጓደኞቹ ከተማዋን ጥለው ጠፉ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጊልስ ስም በአካባቢው ገነነ። ሰው ሁሉ ይፈራው ጀመር። እርሱና ግብረ አበሮቹ አላፊ አግዳሚውን አላስቀምጥ አሉ። መንገደኞች ሁሉ በሰላም መጓዝ፣ ነጋድያንም በጤና መነገድ አልቻሉም። ጊልስ አለቃቸው ነበር። መግደል እና መዝረፍ የዘወትር ኑሮአቸው ሆነ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ዮሐንስ ወንጌላዊው ዳግም ወደዚህች ከተማ መጣ። እኚያን ጳጳስ ስለወጣቱ ጊልስ ጠየቃቸው። አፈሩ፣ አዘኑ። «ያልከኝን አልሰማሁም፣ ያዘዝከኝን አልፈጸምሁም። ጊልስ ዛሬ ሰው ሁሉ የሚፈራው ወንበዴ ሆኗል። ዛሬ አላፊ አግዳሚውን አያስቀምጥም። ይህ ሁሉ የእኔ ስህተት ነው።» በማለት በፊቱ አለቀሱ።

ዮሐንስ ወንጌላዊ ይህን ሲሰማ በእጅጉ አዘነ። ወዲያው ጊልስ ያለበትን ጠየቀና በፈረስ እየጋለበ ተጓዘ። የአካባቢው ምእመናን «ጨካኞች ናቸው ይገድሉሃል» ቢሉትም አልተመለሰም።

በተባለው ቦታ ሊደርስ ሲል ሁለት ሽፍቶች አገኙት። ወዲያው ጩቤያቸውን መዝዘው ከፊቱ ቆሙ። ቅዱስ ዮሐንስም ፍቅር በተሞላው ንግግር «ከመግደላችሁ በፊት እባካችሁ ወደ አለቃችሁ ውሰዱኝ? ለእኔ እርሱ የድሮ ጓደኛዬ ነው።» አላቸው።

ሽፍቶቹም እየሳቁ ወደ አለቃቸው ዘንድ ወሰዱት። ጊልስ መጣ። ዮሐንስ በፈገግታና በፍቅር ተመለከተው። ጊልስ ዐወቀው። ደነገጠ። ዘወር ብሎም መሮጥ ጀመረ። ያ ታላቁ ሰው፣ ዮሐንስን ፈራ።

«ልጄ ለምን ትሸሻለህ እኔ አባትህ ምንም የሚጎዳ መሣሪያ አልያዝሁም» አለው ቅዱስ ዮሐንስ። ያ ጨካኝ የሽፍቶች አለቃ ምርር ብሎ አለቀሰ፣ አነባ። መሣሪያውን ሁሉ አምዘግዝጎ ጣለ። ጓደኞቹን «ደኅና ሁኑ። እኔ ወደ ጌታዬ መመለሴ ነውና» አለና ከቅዱስ ዮሐንስ ኋላ ተፈናጥጦ ወደ ጥንቱ ቦታው ተመለሰ። ትቷት ሄዶ በነበረችይቱ ቤተ ክርስቲያንም ዕድሜ ልኩን እግዚአብሔርን እያገለገለ ኖረ።[33]

## የቅዱስ ዮሐንስ መጻሕፍት

ቅዱስ ዮሐንስ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ አምስት መጻሕፍት አሉት። እነዚህም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

| ተ.ቁ. | የመጽሐፉ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ወንጌል | 1 |
| 2 | መልእክታት | 3 |
| 3 | ራእይ (የትንቢት) | 1 |
| | ድምር | 5 |

ከቅዱስ ጳውሎስ ቀጥሎ ለሐዲስ ኪዳን ብዙ መጻሕፍት በማበርከት ሁለተኛ ነው። በሐዋርያት ዝርዝር ውስጥም በማቴዎስና በሉቃስ ወንጌላት አራተኛ፣ በማርቆስ ወንጌል በሦስተኛ በሐዋርያት ሥራ ደግሞ በሁለተኛ ቦታ ተጽፏል።

---

33 Heroes of the Faith,p. 168-170



## የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል[34]

ከወንጌላት ውስጥ አራተኛውን ወንጌል የጻፈው ቅዱስ ዮሐንስ ነው። የተጻፈውም ከፍጥሞ ደሴት ግዞት ሲመለስ በ96 ዓ.ም አካባቢ ነው። የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ከሌሎች ሦስት ወንጌላት (ሲኖፕቲክስ) ይለያል። ምክንያቱም ከትረካ ይልቅ ነገረ መለኮታዊ (ቲዮሎጂካል) ይዘት አለው። የመጽሐፉ ዋና ዓላማ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እናምን ዘንድ አምነንም በስሙ ሕይወት ይሆንልን ዘንድ ነው።

የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ከሌሎች ወንጌላት ሁሉ በመጨረሻ የተጻፈ ወንጌል ሲሆን (የመጀመሪያው የቅዱስ ማርቆስ፣ ሁለተኛው የቅዱስ ማቴዎስ ሲሆን ሦስተኛው የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ነው።) በምዕራፎችና በቁጥሮች ብዛት የሦስተኛነትን ደረጃ ይዞአል። (21 ምዕራፎች ሲኖሩት 866 ቁጥሮችን አቅፏል።)

ቅዱስ ዮሐንስ:- ቅዱስ ማቴዎስና ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፉት የጌታን የዘር ሐረግ በመዘርዘር ደኃራዊ ልደቱን ከመግለጥ ይልቅ፣ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአባት መወለዱን «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» በማለት አብራርቷል። ዮሐ.1፥1–14።

በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት[35] ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው በኤፌሶን ሲሆን ኤፌሶን በኤጅያን ባሕር ወደብ ሆኖ ነበር። በዚያን ዘመን የእነ ሄራቅሊጠስ (500 ከክርስቶስ ልደት በፊት) የሎጎስ (Logos)[36] አመለካከት ከአይሁዳውያን አመለካከት ጋር ቀላቅለው የሚያስተምሩ ኢስጦኢኮች በታናሿ እስያ ስለነበሩ ቅዱስ ዮሐንስ የሎጎስ (ቃል) እውነተኛ ትርጓሜ ‹ቃል እግዚአብሔር ወልደ እግዚአብሔር ነው› ብሎ ይጽፍ ዘንድ ተነሣ። በመሆኑም ምሥጢረ መለኮትን አልቆ አምጥቆ ሊያስረዳ ፈልጎ በተመስጦ እያለ መልአከ እግዚአብሔር የኤጅያንን ባሕር በእንቁላል ቅርፊት ውኃውን እየቀዳ

---

34 Elkraza, vol.1.No.2. p.15, Vol.3. No.1 p.7

35 ወንጌል ቅዱስ – ተመልከት

36 ሉጎስ ማለት በግሪክ ቋንቋ ‹ቃል› ማለት ነው። ይህንን ‹ቃል› ለአካላዊ ቃል ለኢየሱስ ክርስቶስ መጠቀም የጀመረው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።

ወደ ደረቁ ምድር ሲገለብጥ ቅዱስ ዮሐንስ ተመለከተ። «እንዴት ይህን ባሕር በእንቁላል ቅርፊት ቀድተህ ለመጨረስ ትችላለህ» ብሎ ቅዱስ ዮሐንስ ቢጠይቀው «እኔስ ፍጡርን ነው። አንተ ተመራምር የማይደረስበትን ባሕርየ መለኮት እመረምራለሁ ብለህ ትለፋ የለምን?» ብሎ መለሰለት። ያን ጊዜም ቅዱስ ዮሐንስ የሥላሴን ምሥጢር ጠልቆ መተንተኑን አቁሞ ‹ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ...› ብሎ ሌላ ታሪክ መጻፍ ጀመረ።

ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ከሦስቱ ወንጌሎች (ሲኖፕቲክስ) የሚከተሉትን ነገሮች በመጻፉ ይለያል:-

ሀ. የተለዩ ታሪኮችን አስፍሯል:- ስለ ጌታ ትንሣኤ፤ በመግደላዊት ማርያም መታየቱን፤ የራሱን እና የቅዱስ ጴጥሮስን ሁኔታ ገልጧል። ዮሐ.20።

ለ. የተለዩ ተአምራትን አስፍሯል:-

1. ቃና ዘገሊላ (ም.2)
2. የመጻጉዕ መፈወስ (ም.5)
3. የዕውሩ መፈወስ (ም.9)
4. የአልዓዛር ትንሣኤ (ም.11)
5. ጌታ በተዘጋ በር ገብቶ ለደቀ መዛሙርቱ መገለጡ (ም.20፥19፤26)
6. የቅዱስ ጴጥሮስን 153 ዓሣ መያዝ (ም.21)

ሐ. የተለዩ ትምህርቶችን ይዟል

1. ለናትናኤል የተሰጠውን (ም.1፥47–51)
2. ለኒቆዲሞስ የተነገረውን (ም.3)
3. ለሳምራዊቷ ሴት የተሰጠውን (ም.4)
4. ለአይሁድ የተገለጠው (ም.5)
5. ስለ ምሥጢረ ቁርባን (ም.6፥30–70)



6. ለአይሁድ የሰጠው ትምህርት (ም.8)
7. አንቀጸ አባግዕ (ም.10)
8. በሕጽበተ እግር ጊዜ የተሰጡ ትምህርቶችና ስለ መንፈስ ቅዱስ (ም.13፥16)
9. ስለ እግዚአብሔር አብ (ም.17)
10. ለማርያም መግደላዊት፤ ለሐዋርያው ቶማስ የተሰጡ ትምህርቶችና ስለ ሥልጣነ ክህነት (ም.20)
11. አንቀጸ ኖላዊ (ም.21)
12. መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ጌታችን የተናገረው (ም.3፥27–36)

መ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁ መሆኑን መግለጡ ነው (ም.3፥16፤ ም.3፥18፤ 1፥18፤ 1፥14) ይህም የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ከተባሉት ከቅዱሳን ለመለየት የተጠቀመበት ነው።

ሠ. ጌታችን ደግሞ ደጋግሞ «እኔ ነኝ» በማለት ያስተማረበት ወንጌል ነው።

1. ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ (ም.11፥25)
2. እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ (ም.14፥6)
3. እውነተኛው የወይን ግንድ እኔ ነኝ (ም.15፥1)
4. እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። (ም.15፥5)
5. መልካም እረኛ እኔ ነኝ (ም.10፥11፤14)
6. የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ (ም.6፥35፤41)
7. እኔ እንደሆንኩ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ። (ም.8፥24)
8. እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ (ም.8፥12)
9. በሩ እኔ ነኝ (ም.10፥9)
10. እኔ ነኝ አትፍሩ (ም.6፥20) ወዘተ.

በተባለው ቦታ ሊደርስ ሲል ሁለት ሽፍቶች አገኙት። ወዲያው ጩቤያቸውን መዝዘው ከፊቱ ቆሙ። ቅዱስ ዮሐንስም ፍቅር በተሞላው ንግግር «ከመግደላችሁ በፊት እባካችሁ ወደ አለቃችሁ ውሰዱኝ? ለእኔ እርሱ የድሮ ጓደኛዬ ነው።» አላቸው።

ሽፍቶቹም እየሳቁ ወደ አለቃቸው ዘንድ ወሰዱት። ጊልስ መጣ። ዮሐንስ በፈገግታና በፍቅር ተመለከተው። ጊልስ ዐወቀው። ደነገጠ። ዘወር ብሎም መሮጥ ጀመረ። ያ ታላቁ ሰው፣ ዮሐንስን ፈራ።

«ልጄ ለምን ትሸሻለህ እኔ አባትህ ምንም የሚጎዳ መሣሪያ አልያዝሁም» አለው ቅዱስ ዮሐንስ። ያ ጨካኝ የሽፍቶች አለቃ ምርር ብሎ አለቀሰ፣ አነባ። መሣሪያውን ሁሉ አምዘግዝጎ ጣለ። ጓደኞቹን «ደኅና ሁኑ። እኔ ወደ ጌታዬ መመለሴ ነውና» አለና ከቅዱስ ዮሐንስ ኋላ ተፈናጥጦ ወደ ጥንቱ ቦታው ተመለሰ። ትቷት ሄዶ በነበረችይቱ ቤተ ክርስቲያንም ዕድሜ ልኩን እግዚአብሔርን እያገለገለ ኖረ።[33]

## የቅዱስ ዮሐንስ መጻሕፍት

ቅዱስ ዮሐንስ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ አምስት መጻሕፍት አሉት። እነዚህም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

| ተ.ቁ. | የመጽሐፉ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ወንጌል | 1 |
| 2 | መልእክታት | 3 |
| 3 | ራእይ (የትንቢት) | 1 |
| | ድምር | 5 |

ከቅዱስ ጳውሎስ ቀጥሎ ለሐዲስ ኪዳን ብዙ መጻሕፍት በማበርከት ሁለተኛ ነው። በሐዋርያት ዝርዝር ውስጥም በማቴዎስና በሉቃስ ወንጌላት አራተኛ፣ በማርቆስ ወንጌል በሦስተኛ በሐዋርያት ሥራ ደግሞ በሁለተኛ ቦታ ተጽፏል።

---

33 Heroes of the Faith,p. 168-170



## የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል[34]

ከወንጌላት ውስጥ አራተኛውን ወንጌል የጻፈው ቅዱስ ዮሐንስ ነው። የተጻፈውም ከፍጥሞ ደሴት ግዞት ሲመለስ በ96 ዓ.ም አካባቢ ነው። የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ከሌሎች ሦስት ወንጌላት (ሲኖፕቲክስ) ይለያል። ምክንያቱም ከትረካ ይልቅ ነገረ መለኮታዊ (ቲዮሎጂካል) ይዘት አለው። የመጽሐፉ ዋና ዓላማ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እናምን ዘንድ አምነንም በስሙ ሕይወት ይሆንልን ዘንድ ነው።

የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ከሌሎች ወንጌላት ሁሉ በመጨረሻ የተጻፈ ወንጌል ሲሆን (የመጀመሪያው የቅዱስ ማርቆስ፣ ሁለተኛው የቅዱስ ማቴዎስ ሲሆን ሦስተኛው የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ነው።) በምዕራፎችና በቁጥሮች ብዛት የሦስተኛነትን ደረጃ ይዞአል። (21 ምዕራፎች ሲኖሩት 866 ቁጥሮችን አቅፏል።)

ቅዱስ ዮሐንስ:- ቅዱስ ማቴዎስና ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፉት የጌታን የዘር ሐረግ በመዘርዘር ደኃራዊ ልደቱን ከመግለጥ ይልቅ፣ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአባት መወለዱን «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» በማለት አብራርቷል። ዮሐ.1፥1–14።

በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት[35] ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው በኤጅያን ባሕር ወደብ ሆኖ ነበር። በዚያን ዘመን የእነ ሄራቅሊጠስ (500 ከክርስቶስ ልደት በፊት) የሎጎስ (Logos)[36] አመለካከት ከአይሁዳውያን አመለካከት ጋር ቀላቅለው የሚያስተምሩ ኢስጦኢኮች በታናሿ እስያ ስለነበሩ ቅዱስ ዮሐንስ የሎጎስ (ቃል) እውነተኛ ትርጓሜ ‹ቃለ እግዚአብሔር ወልደ እግዚአብሔር ነው› ብሎ ይጽፍ ዘንድ ተነሣ። በመሆኑም ምሥጢረ መለኮትን አልቆ አምጥቶ ሊያስረዳ ፈልጎ በተመሰጠ እያለ መልአከ እግዚአብሔር የኤጅያንን ባሕር በአንቀልባ ቅርፊት ውኃውን እየቀዳ

---

34 Elkraza, vol.1.No.2. p.15, Vol.3. No.1 p.7

35 ወንጌል ቅዱስ – ተመልከት

36 ሎጎስ ማለት በግሪክ ቋንቋ (ቃል) ማለት ነው። ይህንን (ቃል) ለአካላዊ ቃል ለኢየሱስ ክርስቶስ መጠቀም የጀመረው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።

ወደ ደረቁ ምድር ሲገለብጥ ቅዱስ ዮሐንስ ተመለከተ። «እንዴት ይህን ባሕር በእንቁላል ቅርፊት ቀድተህ ለመጨረስ ትንግለህ» ብሎ ቅዱስ ዮሐንስ ቢጠይቀው «እኔስ ፍጡርን ነው፡፡ አንተ ተመራምር የማይደረስበትን ባሕርየ መለኮት እመረምራለሁ ብለህ ትለፋ የለምን?» ብሎ መለሰለት። ያን ጊዜም ቅዱስ ዮሐንስ የሥላሴን ምሥጢር ጠልቆ መተንተኑን አቁሞ ‹ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ...› ብሎ ሌላ ታሪክ መጻፍ ጀመረ።

ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ከሦስቱ ወንጌሎች (ሲኖፕቲክስ) የሚከተሉትን ነገሮች በመጻፉ ይለያል:-

ሀ. የተለዩ ታሪኮችን አስፍሯል:- ስለ ጌታ ትንሣኤ፣ በመግደላዊት ማርያም መታየቱን፣ የራሱን እና የቅዱስ ጴጥሮስን ሁኔታ ገልጧል። ዮሐ.20።

ለ. የተለዩ ተአምራትን አስፍሯል:-

1. ቃና ዘገሊላ (ም.2)
2. የመኳንንቱ መፈወስ (ም.5)
3. የዕውሩ መፈወስ (ም.9)
4. የአልዓዛር ትንሣኤ (ም.11)
5. ጌታ በተዘጋ በር ገብቶ ለደቀ መዛሙርቱ መገለጡ (ም.20፥19፤26)
6. የቅዱስ ጴጥሮስን 153 ዓሣ መያዝ (ም.21)

ሐ. የተለዩ ትምህርቶችን ይዟል

1. ለናትናኤል የተሰጠውን (ም.1፥47–51)
2. ለኒቆዲሞስ የተነገረውን (ም.3)
3. ለሳምራዊቷ ሴት የተሰጠውን (ም.4)
4. ለአይሁድ የተገለጠው (ም.5)
5. ስለ ምሥጢረ ቁርባን (ም.6፥30–70)



6. ለአይሁድ የሰጠው ትምህርት (ም.8)
7. አንቀጸ አባግዕ (ም.10)
8. በሕጽበተ እግር ጊዜ የተሰጡ ትምህርቶችና ስለ መንፈስ ቅዱስ (ም.13፥16)
9. ስለ እግዚአብሔር አብ (ም.17)
10. ለማርያም መግደላዊት፣ ለሐዋርያው ቶማስ የተሰጡ ትምህርቶችና ስለ ሥልጣነ ክህነት (ም.20)
11. አንቀጸ ኖላዊ (ም.21)
12. መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ጌታችን የተናገረው (ም.3፥27–36)

መ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁ መሆኑን መግለጡ ነው (ም.3፥16፤ ም.3፥18፤ 1፥18፤ 1፥14) ይህም የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ከተባሉት ከቅዱሳን ለመለየት የተጠቀመበት ነው።

ሠ. ጌታችን ደገሞ ደጋግሞ «እኔ ነኝ» በማለት ያስተማረበት ወንጌል ነው።

1. ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ (ም.11፥25)
2. እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ (ም.14፥6)
3. እውነተኛው የወይን ግንድ እኔ ነኝ (ም.15፥1)
4. እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። (ም.15፥5)
5. መልካም እረኛ እኔ ነኝ (ም.10፥11፤14)
6. የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ (ም.6፥35፤41)
7. እኔ እንደሆንኩ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ። (ም.8፥24)
8. እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ (ም.8፥12)
9. በሩ እኔ ነኝ (ም.10፥9)
10. እኔ ነኝ አትፍሩ (ም.6፥20) ወዘተ.

## የመጀመሪያዋ የዮሐንስ መልእክት

ቅዱስ ዮሐንስ በድምጥያኖስ (81–96 ዓ.ም) ዘመነ መንግሥት ለሰባት ዓመታት በፍጥሞ ደሴት ታሥር በኔርቫ (96 –98) ዘመነ መንግሥት ተፈታ።[37]

በ96 ዓ.ም አካባቢም የመጀመሪያዋን መልእክት ጻፈ። ቅዱስ ዮሐንስ በድምጥያኖስ ትዕዛዝ መታሠሩን ያዩት መናፍቃን:-

- ትንግኤ ሙታን የለም፤
- በነቢብ (በመናገር) በገቢር (በሥራ) የሚሠራውን እንጂ በኀልዮ (በሃሳብ) የሚሠራውን ኃጢአት እግዚአብሔር አያውቀውም፤
- ከጥምቀት በኋላ ምግባር መሥራት ጥቅም የለውም። እያሉ የክህደት ትምህርታቸውን በታናሿ እስያ ነዙት። ቅዱስ ዮሐንስ ከፍጥሞ ደሴት ግዞቱ ሲወጣ ለመናፍቃኑ የክህደት ትምህርት መልስ ይሆን ዘንድ ጻፈላቸው።[38]

## ሁለተኛዋ የዮሐንስ መልእክት

ከኤጅያን ደሴቶች በአንዱ፤ ቀለብ እየተሰፈረላት የነገሥታቱን ልጆች የምታሳድግ ሮምና የተባለች ሞግዚት ነበረች። ዮሐንስና ደቀ መዝሙሩ አብሮኮሮስ በዚህች ደሴት ለማስተማር መንገድ ፈልገው ‹የሮምና የአባቷ ባሮች ነበርን፤ ለብዙ ዘመን ጠፍተን ስንኖር አሁን መጣን› እያሉ በደሴቷ አስወሩ። ከንቱ ውዳሴ የሚያጠቃት ሴት ነበረችና ወደ ቤቷ ወስዳ ቅዱስ ዮሐንስን እንጨት ፈላጭ፤ አብሮኮሮስን ደግሞ ውኃ ቀጅ አደረገቻቸው።

አንድ ቀን ከምታሳድጋቸው አንዱን ይዛ ወደ ቤተ ጣዖት ስትገባ ዮሐንስና አብሮኮሮስ ተከትለዋት ገቡ። ያን ጊዜ በቤተ ጣዖቱ ያደረው ሰይጣን እነ ቅዱስ ዮሐንስን ሲያይ

የቤቱን ዕቃ አደናብሮ ወጣ። በዚህ መካከል አስከትላው የነበረው ልጅ በድንጋጤ ሞተ። ያን ጊዜ ‹የእናንተ መምጣት ነው ለዚህ ሁሉ

37 ሠለስቱ ሐዲሳት ገጽ 277። Adv. Haer. V.xxx; H.E.III. xviii; Devir III,9.

38 ሠለስቱ ሐዲሳት ገጽ 277–278



ያበቃኝ› ብላ ደበደበቻቸው። ቅዱስ ዮሐንስም ‹አስነሡልኝ አትይንምን?› ብሎ መለሰላት። «ያሁኑ ይባስ! ከመቼ ወዲህ ነው ደግሞ የሞተ ሰው የሚነሣው?› ብላ የበለጠ ተቆጣች። ያን ጊዜ እነ ቅዱስ ዮሐንስ ጸልየው አስነሡላት።

በዚህ ተአምር አምና ተጠምቃለች። በቤቷም የምእመናን ጉባኤ ተመሠረተ። እርስዋም ለዚያ እመምኔት አድርገው ሾሟት። ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በታሠረ ጊዜ በመናፍቃን የክህደት ትምህርት የተነሣ በቤቷ ያለው የክርስቲያኖች ጉባኤ መከፋፈል ደረሰበት፤ ጠብ ክርክር ተነሣ። ይህን የሰማው ቅዱስ ዮሐንስ በ96 ዓ.ም አካባቢ ለሮምና ጻፈላት። የድሮ ኑሮዋን አስታውሳ ያሁኑን መከራ እንድትረሳ። እመምኔትነቷም ለትዕቢት እንዳይሆንባት ታላቁ ሐዋርያ በድሮ ስሟ «እመቤቴ» እያለ በትህትና ይጠራታል።[39]

## ሦስተኛዋ የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

ይህች መልእክትም የተጻፈችበት ዘመን በ96 ዓ.ም እንደሆነ ይገመታል። ጋይዮስ በስደት ምክንያት የሚንከራተቱትን ክርስቲያኖች እየተቀበለ የሚያስተናግድ ደግ ሰው ነበር። ይህን ደግነቱን የሰማው ቅዱስ ዮሐንስ በዚያ የመከራ ዘመን እንዲህ ያለ ሰው በመገኘቱ እያመሰገነ እያበረታታ ጻፈለት።[40]

## የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ

የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ በግሪክ ቋንቋ ‹አቡቀለምሲስ› በመጽሐፍ ቅዱስ ሊታውንት ዘንድ ደግሞ ‹የሐዲስ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍ› ይባላል።

የተጻፈበት ምክንያት

የቅዱስ ዮሐንስ ሀገረ ስብከቱ ታናሽ እስያ ሲሆን ወደዚህ ቦታ የመጣው እናታችን ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ካረፈች ከ49 ዓ.ም በኋላ ነው። የቅዱስ ዮሐንስ መንበሩ ኤፌሶን ነበረች።

39 ሠለስቱ ሐዲሳት፤ ገጽ 304 –305

40 ዝኒ ከማሁ ገጽ 308 – 309

የኤፌሶን ከተማ በታናሿ እስያ ምዕራባዊ ክፍል በካይስቴር ወንዝ አጠገብ የተሠራች የወደብ ከተማ ነበረች። ነገር ግን የወንዙ ደለል ወደብዋን ስለዘጋው በኋላ ዘመን ወደብ መሆንዋ ቀርቶ ነበር። ይሁን እንጂ አማካይ የንግድ ማዕከል በመሆንዋ የወደብዋ መዘጋት ዕድገትዋን አላገደባትም።

ከሁሉም የበለጠ ከተማዋ የምትታወቀው በአርጤምስ ጣዖት ስም በተሠራው ቤተ ጣዖት ሲሆን ይህ ቤተ ጣዖት በዓለም ላይ ከነበሩት ከሰባቱ አስደናቂ ነገሮች አንዱ ነበር። ዋናው ቤተ ጣዖቱን የሠሩት የፋርስ ነገሥታት ሲሆኑ በ120 ዓመታት ውስጥ ተሠርቶ ማለቁ ይነገራል። ለቤተ ጣዖቱ መሥሪያ የዋለው፣ ሙሉ በሙሉ የከበረ ድንጋይ ሆኖ የቤቱ ከፍታ 400 ጫማ ነበር። ከ1000 ምሰሶዎች በላይ የነበሩት ሲሆን እያንዳንዳቸው 60 ጫማ ይረዝሙ ነበር። የተሠራውም ከጌታ ልደት በፊት 350 ዓመት ገደማ ነው።[41]

የኤፌሶን ሰዎች አርጤምስን ማምለክ እንዴት እንደጀመሩ የሚተረከው ታሪክ የሚከተለው ነው።

ኤፌሶን የሚለው ስም በዚያች ሀገር የነበረ የአንድ ገዥ ስም ነው። እርሱም ይህያን (ዮናን) የተባለው ሰው ልጅ ነው።

ኤፌሶን ከተማዋን ቆርቁሮ በስሙ የጠራት ሲሆን አርጤምስ የተባለች መልክ ከደም ግባት አሟልታ የያዘች ልጅ ነበረችው ነገር ግን ሰውን በንብረቱ፣ በገንዘቡ፣ በዘሩ፣ በርስቱ እያመካኘች ትንቅ ነበርና የሚያገባት አልተገኘም። አንዱን ያሟላው ሌላውን አያሟላምና። በመጨረሻ ግን ቆርኔሌዎስ የተባለ መተተኛ ሊያገባት ጠየቀ። እርስዋም ‹ከነገሥታት ዘር የለህ? ከከበሩት ሀብት የለህ በምንህ ልታኖረኝ ታገባኛለህ?› ብትለው ‹ዋናው ነገር ያንቺ መከበርና መፈራት ነውና እንድትከበሪ እንድትወደሺ ብሎም እንድትመለኪ አደርግሻለሁ› አላት። እርሷም ከንቱ ውዳሴ እጅግ የሚያጠቃት ሴት ስለነበረች በሃሳቡ ተስማማችበት።

ቆርኔሌዎስ ሕዝቡን እየሰበሰበ መተት የሚሠራበት አደባባይ ነበረው። ከዚህ አደባባይ ቆሞ በአስማት አጋንንትን እየጠራ ተአምር

41 ከዓለም አስደናቂ ነገሮች፣ ገጽ 2



በማሠራት ብዙዎችን ለማያውቁት አምላክ ያሰግዳቸው ነበር። አንድ ቀን እንደ ልማዱ አጋንንቱን በአስማት ጠርቶ «ለአርጤምስ ስገዱ፤ ያልሰገደ ቤቱ ይበረበራል፣ ሀብት ንብረቱ ይዘረፋል» ብሎ በብራና ጽፎ ሰጣቸውና በሚያስተምርበት አደባባይ ከአየር ላይ እንዲጥሉለት አዘዛቸው። አጋንንቱም እንደታዘዙት ሕዝቡን ሰብስቦ አስማት በሚሠራበት ሰዓት ከአየር ላይ ብራናውን ወረወሩት። ይህንን ያየው የኤፌሶን ሕዝብም «ከአየር ላይ በወረደው መልእክት» የተነሣ አርጤምስን ‹ከሰማይ የወረደች ናት› ብሎ ይሰግድላት ያመልካትም ጀመር።

ከሞተችም በኋላ ቤተ መቅደሷን ሠርተው፣ ምሥሏን ቀርጸው ማምለካቸውን ቀጠሉ። አንጥረኛው ሁሉ ምሥሏን እየሠራ በመሸጥ ሀብታም ሆነ።[42]

አስቀድሞ ቅዱስ ጳውሎስ በ49 ዓ.ም አካባቢ በሁለተኛው ጉዞ ወደ ኤፌሶን ገብቶ ለሦስት ዓመት ከሦስት ወር ያህል ሲያስተምር የአርጤምስን ምሥል እየሠራ ከሚሸጠው ከአንጥረኛው ከዲሜጥሮስ ችግር ስለተፈጠረበት ከተማዋን ለቆ ወጥቶ ነበር።

ወንጌላዊው ዮሐንስም ከ49 ዓ.ም በኋላ ወደ ኤፌሶን ከተማ ገብቶ ሲያስትምር መጀመሪያ የተቃወመው በአርጤምስ ቤተ መቅደስ የሚካሄደውን አምልኮ ጣዖት ነበር።

ድምጥያኖስ ቄሣር (ከ81 – 96 ዓ.ም) በሮማ ሲነግሥ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በርኅራኄ የሚያስተዳድር፣ ግጥምን፣ ጥበብንና ትምህርትን የሚወድ ንጉሥ ሆኖ በመቅረቡ ለጥቂት ጊዜያት ያህልም ቢሆን መምህራን ክርስትና ከመከራውና ከስደቱ ፋታ አግኝተው ስለነበር ወንጌላዊው ዮሐንስም የአርጤምስን አምልኮ ጣዖት መቃወሙ ብዙም ችግር አልፈጠረበትም ነበር።

ድምጥያኖስ ለ13 ዓመታት ያህል በደግነት ካስተዳደረ በኋላ አንጦኒዎስ ሳቱርኒው የተባለ ታማኝ የጦር አለቃው ስለከዳው በብስጭትና በበቀል የጭካኔ ተግባሩን ጀመረ። ይወደው የነበረውንም ትምህርትና ጥበብ ለማጥፋት ቆርጦ ተነሣ።

42 መለስተ ሐዲሳት፣ ገፅ 349–350

በዚህ ጊዜ ነው አረማውያኑ በዮሐንስ ላይ ያደረባቸውን ጥላቻ ለመወጣት መንገድ ያገኙት። በትምህርቱ የተነሣ በአረማውያን ተከ ስሶ በድምጥያኖስ ፊት ቀረበ። እርሱም በፈላ ውኃ በተሞላ በርሜል ውስጥ ካስቃየው በኋላ በፍጥሞ ደሴት አጋዘው።[43] አባታችን ቅዱስ ዮሐንስም በፍጥሞ ደሴት በጠባብ ዋሻ ውስጥ ለ7 ዓመታት (ከ88 –96 ዓ.ም) ያህል በግዞት ተቀምጦ ሳለ ነው ራእዩን ያየውና የጻፈው።

ፍጥሞ ከታናሿ እስያ (ዛሬ ቱርክ) 25 ማይልስ ርቀት ላይ የምትገኝ የኤጅያን ባሕር ደሴት ናት። በሮማውያን ዘመን ደሴቷ አምልኮ ጣዖትን አንቀበልም ያሉ ሁሉ የሚጋዙባት ቦታ ነበረች። ዛሬ በደሴትዋ ውስጥ ዮሐንስ ራእዩን ያየበትና የጻፈበት ዋሻ ይገኛል።

አባታችን ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ታሥሮ እያለ እንደ ወንድሞቹ ሐዋርያት ዞሮ ባለማስተማሩ ያዝን ይተክዝ ነበርና እግዚአብሔር የበለጠ ምሥጢርን ገለጠለት።

ከሐዋርያውያን አበው አንዱ ሄሬኔዎስ ዮሐንስ ራእዩን የጻፈው በድምጥያኖስ የመጨረሻ ዓመታት (81–96 ዓ.ም) በግዞት እያለ መሆኑን ገልጦአል።[44] አንዳንዶች ግን ራእዩን የጻፈው ከግዞት ተመልሶ በኤፌሶን ከተማ ነው ይላሉ። ይህ ግን ከራእዩ መጽሐፍ አንፃር ትክክል አይሆንም። ምክንያቱም በራእዩ መጽሐፍ ላይ ደግሞ ደጋግሞ ‹እንዲህ ብለህ ጻፍ አለኝ› የሚል ቃል ይገኛል። ይህም በዚያው ራእዩን ባየበት ሰዓት የጻፈው መሆኑን ያመለክታል።

አባ ጀሮም አባታችን ዮሐንስ የመጨረሻውን በምድር የኖረበትን የዕድሜ ዘመን በኤፌሶን ከተማ እንዳሳለፈው ጽፎአል። በዚህ ወቅትም እጅግ ከማርጀቱ የተነሣ ‹እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። ይህ የጌታችን ትዕዛዝ ነውና! ይህን ከጠበቃችሁ ይበቃችኋል› የምትለውን ቃል ብቻ ለደቀ መዛሙርቱ ይናገራቸው ነበር።[45]

በመጨረሻዋ ሰዓት ከደቀ መዛሙርቱ መለየት ቢቸግረው ይከተሉት የነበሩትን ወደ ውጭ ልኮ እርሱ ተሠወረ። ቢመለሱ ከመገናጸፊያውና ከመቋሚያው፣ ከመጽሐፉም በቀር አላገኙም።

---

43 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ሁለተኛ መጽሐፍ፣ ገጽ 179
44 Eusebius, 3:18
45 Dictionary of Saints, p.189.



የዮሐንስ ራእይ የተጻፈው በዚያን ዘመን ዮናናውያን ተብለው በሚጠሩት ሰባት የታናሿ እስያ ከተሞች ለሾማቸው ሊቃነ ጳጳሳት ነበር። መላእክት የተባሉትም እነርሱ ናቸው።[46]

መጽሐፉ በጠቅላላ ወደ 300 የሚጠጉ ምሳሌዎች የያዘ ሲሆን የክርስቲያኖችን ሰማያዊ ሕይወት፣ የጻድቃንን፣ የሰማዕታትን ክብር የሚያሳይ መጽሐፍ ነው።

ለምሳሌ በራእይ 1፥9 «በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርኩ» በማለት ክርስቲያኖች የሚኖሩትን ከዓለም የተለየ ነገር ግን በዓለም ውስጥ የሆነ ኑሮ አሣይቷል። ቅዱስ ዮሐንስ እንደሰውነቱ ቦታ ተወስኖለት፣ ድንበር ተሠርቶለት በፍጥሞ ደሴት ነበረ። ደግሞም መንፈሳዊ ነውና በመንፈሳዊው ዓለም ከቅዱሳን ጋር ነበር። «በመንፈስ ነበርኩ» ያለው ይኽንን ነው።

ለዚህ ነው ዛሬም ቦታ ድንበር ባላት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እያለን በሰማያዊ ዜማ፣ ሥርዓት፣ እምነትና አምልኮ ከጻድቃን፣ ከሰማዕታትና ከቅዱሳን መላእክት ጋር አንድ የምንሆነው።[47]

## ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ

ሀገሩ ቤተ ሳይዳ ነው። ዮሐ.1፥44። ናትናኤልን ወደ ጌታ ያቀረበው እርሱ ነው። ዮሐ.1፥46። ጌታችን 5000 ሕዝብ በመገበ ጊዜ ሐዋርያው ፊልጶስ የሕዝቡን ብዛት ተመልክቶ ለዚህ ሁሉ የሚበቃ እንጀራ የለንም ብሎ ነበር። ዮሐ.6፥5–7። ግሪኮች ከጌታ ጋር መገናኘት ሲፈልጉ ለሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ የነገራቸው እርሱ ነው። ዮሐ.20፥21 «ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል» ብሎ ጌታችንን በየዋህነት በመጠየቁ ምሥጢረ ሥላሴን ለመማር በቅቷል። ዮሐ.14፥8።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐረገ በኋላ ሐዋርያው ፊልጶስ በፍርግያ፣ በሰማርያና በጋዛ ወንጌልን ሰብኳል።[48] ብዙ ታሪክ

---

46 በግእዝ ቋንቋ መልአክ ማለት ሁለት ትርጉም አለው 1. መልእክተኛ 2. አለቃ ማለት ነው። (ወትሠይሚዮሙ መላእክተ በኩሉ ምድር– በምድር ላይ ገዦዎች (አለቆች) አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ እንዲል) በራእየ ዮሐንስ መጽሐፍ መልአክ ሲል አለቃ ማለት ነው።
47 An Introduction to the Book of Revelation, p.14,17.
48 St. Mark and the School of Alexandria, p. 9

ጸሐፊዎች ሐዋርያውን ከዲያቆኑ ፊልጶስ[49] ጋር ያምታቱታል። ዲያቆኑ ፊልጶስ በሐዋርያት አሳሳቢነት ማኅበረ ምእመናንን ሊያገለግሉ ከተመረጡት ሰባቱ ዲያቆናት መካከል አንዱ ነው። የሐዋ.6፥5። መኖሪያው በቂሳሪያ ሲሆን ባለትዳርና የአራት ሴቶች ልጆች አባት ነው። ሐዋ.21፥8። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ሲያደርግ ያስተናገደው ዲያቆኑ ፊልጶስ ነው። በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ የነበረው የኤፌሶኑ ፖሊቅራጠስ እንደጻፈው ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ወደ ታናሿ እስያ መጥቶ በሔራፖሊስ ከተማ ሲያስተምር በተቃዋሚዎቹ እጅ ተሰቅሎ በሰማዕትነት ዐርፏል።[50] የዚህ ሐዋርያ መቃብርም እስከ ዛሬ ድረስ በዚህችው ከተማ እንደሚገኝ ይነገራል።[51]

## 6. ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ

ሐዋርያው በርተሎሜዎስ ስሙ በሐዲስ ኪዳን ላይ የተገለጠው በሐዋርያት ዝርዝር ላይ ብቻ ነው። የምዕራቡ ዓለም ምሁራንና የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ስለዚህ ሐዋርያ ማንነት የተለያየ ሃሳብ አላቸው። ቀደም ብለን እንዳየነው ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ ራሱን የቻለ ሐዋርያ እንጂ የናትናኤል ሌላ ስሙ አይደለም።

በርተሎሜዎስ ክርስትናን የሰበከው በአርመንያና አካባቢዋ መሆኑንና አስቀድሞ ለአርመንያውያን ወንጌልን የሰበከውና መንበርዋንም ያቋቋመው እርሱ መሆኑን አርመኖች በታሪካቸው ይናገራሉ።[52] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ ደግሞ፣ ፓንተንስ ዘእስክንድርያ የተባለ ተጓዥ ሕንድን በጎበኘ ጊዜ (150–200 ዓ.ም) ሐዋርያው በርተሎሜዎስ ያመጣልን ነው ብለው የሕንድ ክርስቲያኖች በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈ የማቴዎስን ወንጌል እንዳሳዩት መግለጡን ጽፏል።[53]

49 የሐዋ.6፥3፤ 8፥26–39፤ 21፥8.
50 Oxford Dictionary of Christian Church, p.1062
51 Dictionary of Saints p.282
52 Jesus Our Saviour, p.
53 HE 5.10.3



የሃገራችን ሊቃውንትም በኢትዮጵያ ውስጥ መስበኩንና ሕዝቡን ያጠመቀባቸው ወንዞች እስከ ዛሬ ድረስ ‹ብረት› እና ሎሚ ‹ውኃ› እየተባሉ እንደሚጠሩ ይተርካሉ።[54]

በገድለ ሐዋርያት ተጽፎ እንደምናገኘው ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ በሐዋርያት ዕጣ የደረሰው አልዋሕ በተባለ ሀገር ነበር።[55] ቅዱስ ጴጥሮስ በርተሎሜዎስን ለማድረስ ሲል አብረው ወደ አልዋሕ ተጓዙ። ሁለቱም ሀገሩን አያውቁትም ነበርና ጉዟቸው በጥየቃ ነበር። በመጨረሻ አንድ ሚራራ ነጋዴ አገኙና እንዲያደርሳቸው ጠየቁት።

ነጋዴው ማንነታቸውን ሲጠይቃቸው የጌታችን ደቀ መዛሙርት ክርስቲያኖች መሆናቸውን ነገሩት። ያም ነጋዴ በመንገዱ የሰማውን አስታውሶ ‹እናንተ ሐዋርያት ሰው ብቻውን ካልኖረ አይጸድቅም ትላላችሁ። ደግሞም ባልና ሚስት ትለያያላችሁ ይባላል። እውነት ነው?› አለና ጠየቃቸው። «እኔ በምንም መንገድ ወደ ሀገሬ አልወስዳችሁም፤ ደግሞ ሚስቴ ትምህርታችሁን የሰማች እንደሆነ ትታኝ ትኮብላለች!»

ነጋዴው ትቷቸው ሄደ።

በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ እና ሐዋርያው በርተሎሜዎስ ተመካከሩ። ሌላ ነጋዴ ሲመጣም ቅዱስ ጴጥሮስ:- «ይህንን ባርያዬን በሀገረ አልዋሕልሸጠው ፈልጌአለሁ። እባክህ ወደ ሀገርህ ውሰደኝ» ሲል ጠየቀው። ያም ነጋዴ፡ «ለብዙ ጊዜ ከሀገሬ ወጥቼ የምኖር በመሆኔ ለቤቴ አገልጋይ የሚሆን ሰው እጥቼ እኖር ነበር። ዛሬ አገኘሁ። ለመሆኑ ሎያው ምንድነው?» ብሎ ጠየቃቸው። ቅዱስ ጴጥሮስም ቀለል አድርጎ «ወይን ጠባቂ ነው» አለው። ያ ነጋዴ እጅግ በጣም ብዙ ወይን ስለነበረው በ30 እስታቴር በርተሎሜዎስን ከቅዱስ ጴጥሮስ ገዛው። ቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘቡን ከነጋዴው ከተቀበለ በኋላ ‹አደራ ለሌላ ጌታ እንዳትሸጠው፤ መከራም እንዳታበዛበት› ሲል ነጋዴውን ለመነው።

54 ትንሣኤ 60/75፤ ገጽ 23
55 ገድለ ሐዋርያት፤ ገጽ 83–100

ባለጸጋው የግመሎቹን ሸክም ሲያስተካክል ቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘቡን ደብቆ ለበርተሎሜዎስ በመስጠት ‹ለድኾች መጽውተው› አለውና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

ነጋዴውና በርተሎሜዎስ በበረሃው ውስጥ መንገዳቸውን ቀጠሉ። አልዋሕ እንደደረሱም ነጋዴው በርተሎሜዎስን የወይን ጠባቂዎች አለቃ አድርጐ ሾመው። ወይን እየጠበቀ፣ እየኰተኰተ እና እየተከለ ለ40 ቀናት ያህል በሥራ ተጠምዶ ተቀመጠ። ‹ጌታዬ ሆይ ወንጌልህን ሳልሰብክ፣ ትዕዛዝህን ሳልፈጽም፣ ተቀምጬ መቅረቴ ነውን?› እያለ ያለቅስ ነበረ።

አንድ ቀን ባለጸጋው የወይኑን ቦታ ሊያይ ሲመጣ እባብ ከጉድጓድ ወጥቶ ነከሰውና መርዙ ኃይለኛ ስለነበር በሰውነቱ ውስጥ ተሠራጭቶ ለሞት አበቃው። ወዳጅ ዘመዶቹም ለለቅሶ ተሰበሰቡ። በርተሎሜዎስ ግን ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር። የቤቱም ሰዎች «አንተ ጨካኝ አሽከር ጌታህ ሲሞት እንደማልቀስ አፍጥጠህ ታየናለህን?» እያሉ ጮኹበት።

በርተሎሜዎስ ግን ጸሎቱን እስኪፈጽም ታገሣቸውና ያንን ባለጸጋ በስመ እግዚአብሔር ከሞት አስነሣው። ያም ባለጸጋ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ አፈፍ ብሎ ተነሥቶ ለዚህ ያበቃው በርተሎሜዎስ መሆኑን መሰከረ። በዚህም የተነሣ ባለጸጋውና የተሰበ ሰበውም ሕዝብ በተደረገው ተአምር ተገረሙ። በበርተሎሜዎስ ስብከትም አምነው ተጠመቁ። ከዚህ በኋላ በርተሎሜዎስ ጊስሚፌንና ጊኤንዶስ ወደ ተባሉ[56] ሀገሮች አመራ። እነዚህን ሀገሮች የሚገዛው የንጉሥ አክርጳ ሚስት እንኳን እስከትለወጥ ድረስ ብዙ ክርስቲያኖችን አፍርቷል። መኳንንቱና መሳፍንቱ የሕዝቡን መለወጥ፣ የአምልኮ ጣዖታቸውን መቅረት፣ ሕዝቡም ከእነርሱ ይልቅ ለበርተሎሜዎስ ቃል መታዘዙን ተመልክተው በቅንዓት ተነሡበት። ተከስሶም ወደ ንጉሥ አክርጳ ፍርድ ቤት ቀረበ። በዚያም የሞት ፍርድ ተፈርዶበት መስከረም 1 ቀን አሸዋ በተሞላ ከረጢት ውስጥ ከትተው ከነሕይወቱ ባሕር ውስጥ ወረወሩት። በዚያም ዐረፈ። በነጋታውም ምእመናን ከባሕር አውጥተው ቀበሩት።

አልዋሕ የተባለችው ሀገር በአርመንያ አካባቢ ትገኝ ይሆናል።

---

56 ዛሬ እነዚህ ሀገሮች እነማን እንደሆኑ አይታወቅም።



## 7. ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ‹ትንሣኤ ሙታን የለም› ብለው ያምኑ ከነበሩት ሰዱቃውያን ወገን እንደነበረ ይነገራል። ማቴ.22፥23። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን አሥሩ ሐዋርያት ሲነግሩት ‹የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ፣ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ፣ እጄንም በጐኑ ካላገባሁ አላምንም› ያለው በዚህ የተነሣ ነበር። ዮሐ.20፥25።

በኋላ ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቶማስ በእምነቱ እንዲጠነክር አስቀድሞ አሥሩ ባሉበት እንደተገለጠው ሁሉ ዳግመኛ ቶማስ ባለበት በዝግቤት ውስጥ ተገልጦ ቶማስ ያለው ሁሉ እንዲፈጸምለት አደረገ። ቶማስም ‹ጌታዬ አምላኬ› ብሎ አምኖ መስክሮአል።

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ከሐዋርያት ሁሉ ርቆ ወደ ምሥራቅ የተጓዘ ሐዋርያ ነው።

### የምሥራቋ የክርስቲያኖች ከተማ

በዮሐንስ ወንጌል 12፥20–22 ግሪኮች በሐዋርያው እንድርያስ አቅራቢነት ከጌታችን ጋር እንደተነጋገሩ ተገልጦአል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለነዚህ ግሪኮች ማንነት ባይገልጥልንም በቤተክርስቲያን ትውፊት ግን እነዚህ ግሪኮች በሮማ ግዛትና በፐርሺያ መካከል ይኖር ከነበረ አብጋር ዑካማ ከተባለ የዑር (ኤዴሳ) ንጉሥ የተላኩ ነበሩ።

አብጋር ጃንሆይ እንደማለት ነው። ለዑር ነገሥታት ስመ መንግሥታቸው ነው።[57] አብጋሮች በዑር (ኤዴሳ)[58] የነገሡት ከጌታችን ልደት በፊት 132 ዓመት – 216 ዓ.ም ድረስ ነው። አብጋር ዑካማ በማይድን በሽታ ተይዞ ሲሰቃይ ከግሪክ ነጋድያን የጌታችንን ዝና በመስማቱ የሚከተለውን ደብዳቤ ለጌታ ላከለት።

‹ተላከ ከአብጋር ዑካማ ለእውነተኛው መድኀን ለኢየሱስ ክርስቶስ፣ በኢየሩሳሌም ለተገለጥከው። ሰላም ላንተ ይሁን። ሥር ሳትምስ ቅጠል ሳትበጥስ ስለምታደርገው የማዳን ሥራና ስለ አንተ

---

57 ግብፆች – ፈርዖን፣ ሮማውያን– ቄሣር እንደሚሉት ማለት ነው።

58 በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ (ሮሐ) ትባላለች።

ዝና ሰምቻለሁ። እንደነገሩኝ ከሆነ ዕውሩን ታበራለህ፣ ሽባውን ትተረትራለህ፤ ይህን ስሰማ ወደ እኔ መጥተህ ከዚህ ከሚያሰቃየኝ የደዌ ዳኛ የአልጋ ቁራኛ ትገላግለኝ ዘንድ እለምንኻለሁ። ይህንንም ደብዳቤ ልኬብኻለሁ። አይሁድ ባንተ ላይ እንደተነሣሡብህ ሰምቼአለሁ። ሊገድሉህም ይፈልጋሉ አሉ። ምንም እንኳን ከተማዩ ጠባብ ብትሆን ውብናት! ለእኔና ለአንተም ትበቃናለችና ወደ እኔ ና!›

ጌታችን ከመልእክተኞቹ ደብዳቤውን ተቀብሎ ካነበበ በኋላ እንዲህ ብሎ መለሰለት።

‹አብጋር ሆይ አሁን ልጐበኝህ አልችልም፤ ነገር ግን ከትንሣኤዩ በኋላ ከደቀ መዛሙርቴ አንዱን እልክልኻለሁ›[59]

በዚህ ቃል ኪዳኑ መሠረት ከዕርገት በኋላ ጌታችን ቶማስን ወደ ዑር ላከው። ቶማስም ከሰባ ሁለቱ አርድዕት ወገን የሚሆነውን ደቀ መዝሙሩን ታዴዎስን (አዳይ) [60] ላከለት። ቅዱስ ታዴዎስም ኤዴሳ ገብቶ አብጋርን ፈውሶ ሀገሩን ቀደሰለት። ከአብጋር ጀምሮም ብዙ ሰዎች በክርስትና አምነው ተጠመቁ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ተተከለው እርስዋም በምሥራቅ እስያ የመጀመሪያዋ ክርስቲያን ከተማ መሆንዋ በታሪክ ይነገራል።

ሐዋርያው ቶማስ ታዴዎስን ወደ ኤዴሳ ከላከ በኋላ በቅድሚያ ወደ ፐርሺያ ከዚያም ወደ ሕንድ ተጓዘ። ቅዱስ ቶማስ ሕንድ የደረሰው በ46 ዓ.ም አካባቢ ነው።

## የሰማዩ ቤተ መንግሥት

በሕንድ የማላባር ግዛት በታክሻሲላ ከተማ የነበረው ንጉሥ ጐንዶፓረስ በኢየሩሳሌም ስለነበረው የሰሎሞን ቤተ መንግሥት ዝና እየሰማ እርሱም በግዛቱ ያን ዓይነት ቤተ መንግሥት ለማሠራት ይፈልግ ነበርና ነጋዴዎች በየሀገሩ ሲጓዙ የታወቀ ግንበኛ እንዲያመጡለት አዟቸው ነበር።

59 የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ገጽ 118

60 The New Inter. Dictionary. of the Christian Church. p.4; Doctrina Addai (Discovered in 1876)



ይህን መልእክት ከሰሙት ነጋዴዎች መካከል አንዱ ወደ ፐርሺያ ወረደ። ቅዱስ ቶማስ ወደ ሕንድ ተጉዞ ወንጌልን ለመስበክ መንገድ ሲፈልግ ከዚያ ነጋዴ ጋር ተገናኘ። ነጋዴው የቶማስን ከኢየሩሳሌም መምጣት ሲሰማ የግንበኝነት ሙያ ይችል እንደሆን ጠየቀው። ቶማስም በኢየሩሳሌም በነበረበት ጊዜ ሕንፃ በማነፅ ኑሮውን ይገፋ እንደነበር ለነጋዴው መለሰለት።

ነጋዴው በዚህ አጋጣሚ እጅግ ተደስቶ ቶማስን ወደ ሕንድ ማላባር ወሰደው። ንጉሡም የቶማስን ሙያ ሲሰማ ነፍስ አልቀረለትም። ንጉሡ ከታክሻሲላ ከተማ አጠገብ ወደሚገኘው ሜዳ ቶማስን ወሰደውና በሜካ የተሞላውን ሜዳ እያሳየ ቤተ መንግሥቱ የሚተከልበትን ቦታ አመላከተው። ቅዱስ ቶማስ የቤተ መንግሥቱን ዐቅድ ሲነግረው ንጉሥ ጐንዶፓረስ ተሠርቶ እስከሚያየው ቸኰለ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ንጉሡ ‹ለሠራተኛ መቅጠሪያ፣ ለድንጋይና ዕብነ በረድ፣ ለብርና ወርቅ፣ ለብረትና እንጨት መግዣ› እያለ ለቅዱስ ቶማስ ያለ የሌለውን ገንዘብ ይልክለት ጀመር።

ቅዱስ ቶማስ ገንዘቡን ሲያገኝ የተጓዘው ወደ ዝበያ ወይም ሠራተኛ ፍለጋ ሳይሆን ወደ ድኾች መንደር ነው። በዚያም ለተራቡት ምግብ፣ ለታረዙት ልብስ፣ በየቦታው ለወደቁት መጠለያ እየገዛ ማደል ጀመረ። በሽተኞችን እየፈወሰ እና የተቸገሩትን እያጽናና ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን መስበክ ያዘ።

ንጉሥ ጐንዶፓረስ ገንዘብ በላከ ቁጥር የሚገነባው ቤተ መንግሥቱ ሳይሆን የድኾችና የደካሞች ቤት ሆነ። ለቤት መሥሪያ የመደበው ገንዘብና ጊዜ እንደተጠናቀቀ ቤተ መንግሥቱን ሊጐበኝ ወጣ። ሜካው አልተነካም። ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ቀርቶ የወደቀ ድንጋይ የለም። ንጉሡ በዚያ በኩል የሚያልፍ አንድን መንገደኛ ጠራና ‹ቶማስ የታለ?› ሲል አፈጠጠበት።

‹ቶማስ የተራቡትን እያበላ፣ የተጠሙትን እያጠጣ፣ የታረዙትን እያለበሰ፣ ሕሙማኑን እየፈወሰ በድኾች መንደር ይገኛል› ሲል መንገደኛው መለሰለት።

‹እርሱ ባልከፋ! ታድያ የሠራልኝ ቤተ መንግሥት የታለ?› ንጉሡ መንገደኛው ላይ እንዳፈጠጠ ጠየቀው።

‹በድንጋይ የተሠራ ቤተ መንግሥት ላያዩ ይችላሉ ጌታዬ፤ ነገር ግን በሕዝብዎ ገጽታ ላይ ደስታና ፈገግታ ማንበብ ይችላሉ። አለው› መንገደኛው።

በዚህ ጊዜ ንጉሡ ያ ሁሉ ገንዘቡ እንደባከነበት መጠርጠር ጀመረ። ወዲያው ወታደሮቹ ቶማስን ፍለጋ አካባቢውን አጥለቀለቁት።

ቅዱስ ቶማስ ተይዞ እንደመጣ:-

‹ቤተ መንግሥቴን ለምን አልሠራህልኝም?› አለው ንጉሡ።

‹ሠርቻለሁ ጌታዬ› ቶማስ መለሰ።

‹የታለ? ሚካው እንኳን መች ተነሣ?›

‹እርግጥ በምድር ላይ የድንጋይ ቤተ መንግሥት ላያዩ ይችላሉ፤ እኔ ግን በሰማይ ላይ ቤተ መንግሥት ሠርቼልዎታለሁ።› አለው ቶማስ ለንጉሡ።

ያን ጊዜ ንጉሡ ተቆጣ። ቶማስን እጅ እግሩን እየቆራረጡ እንዲያሠቃዩት አዝዞ ወኅኒ አወረደው።

በዚያች ሌሊት የንጉሡ ወንድም የሆነው ልዑል ጋድ በድንገተኛ በሽታ መጣደፍ ጀመረ። ሊነጋጋ ሲልም ነፍሱ ወጣች።

የጋድ ነፍስ በመላእክት ታጅባ ወደ ሰማያት ወጣች። ካጀቧት ቅዱሳን መላእክት አንዱ ብዙ አብያተ መንግሥታትን እያሳያት ‹ትኖሪበት ዘንድ ደስ ያለሽን ምረጪ› አላት። የጋድ ነፍስም በአብያተ መንግሥታቱ መካከል የሚታየውን የሚያምር ቤተ መንግሥት መረጠች። ‹ይህ ቤተ መንግሥት ያንቺ አይደለም፤ ቶማስ ለንጉሥ ጐንዶፓረስ የሠራለት ሰማያዊ ቤተ መንግሥት ነው።› አላት። በዚህች ሰዓት የልዑል ጋድ ነፍስ ከሥጋው ጋር ተዋሐደች።

ጋድ ሊቀብሩት በተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ተንቀሳቀሰ። ከዚያም አፈፍ ብሎ ተነሣ። ልዑል ጋድ በዚያች ቅጽበት የተመለከተውን ሁሉ ለንጉሥ ጐንዶፓረስና ለተሰበሰቡት ሁሉ ነገራቸው።

ንጉሡ ይህንን ሲሰማ በቶማስ ላይ በሠራው ግፍ ሁሉ አዘነ። ተፀፀተም። ያ—ያሰበው ቤተ መንግሥት መሠራቱን ሲሰማ ቶማስን



ከወኅኒ አወጣው። እርሱና ቤተሰቡም በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ። ጐንዶፓረስም ‹ሌላም ቤተ መንግሥት ሥራልኝ› እያለ ያለውን ሁሉ ገንዘብ ለቶማስ ይሰጠው ጀመር። የማኅበር ባለጸጐችም አሠረ ፍኖቱን ተከተሉ።

ቅዱስ ቶማስ ከማኅበር ጀምሮ እስከ ቻይና በመዝለቅ ወንጌልን ሰብኳል። በመጨረሻም በ66 ዓ.ም በሚላፓር ከተማ የሚገኙ አምላክያን ጣዖት ቀዳውን ገፈው ስልቻ በመሥራት በሰውነቱ ጨው ነሥንሰው እያሰቃዩ ለሞት አብቅተውታል።

በ4ተኛው መ/ክ/ዘመን ዐፅሙ ወደ ኤዴሳ መጥቶ በክብር ዐርፎአል።[61]

## 8. ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ

በቤተክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት የማቴዎስ አባቱ ዲቁ እናቱ ደግሞ ክሩትስያ ትባላለች።[62] በማርቆስ ወንጌል ግን የአባቱ ስም እልፍዮስ ተብሎ ተጠርቷል። ማር.2፥14። ይህም የዲቁ ሌላ ስሙ ነው።

የመጀመሪያ ስሙ ሌዊ ሲሆን ማቴዎስ የሚለውን ስም ያወጣለት ጌታ ነው፤ ትርጉሙም ‹የተመረጠ› ማለት ነው። በሐዋርያት ዝርዝር ላይ በራሱ ወንጌልና በሐዋርያት ሥራ 8ተኛ፤ በማርቆስና ሉቃስ ወንጌል ደግሞ በሰባተኛ ቦታ ላይ ተቀምጦአል።

ማቴዎስ የቀድሞ ሥራው ቀራጭነት (ግብር ሰብሳቢ) ሲሆን ይሠራበት የነበረውም ቦታ በገሊላ ባሕር አጠገብ በምትገኘው ደግሞ የቅፍርናሆም ከተማ ነበር። ከቅፍርናሆም ገበያ ወደ ገሊላ ባሕር ወደብ በሚወስደው ዐቢይ መንገድ ዳር ሱቅ ከፍቶ ነጋዴዎችን ቀረጥ ያስከፍል ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ሲያስተምር ወደሚቀርጥበት ቦታ ጠጋ ብሎ ‹ተከተለኝ› አለው። ቅዱስ ማቴዎስ እርሱ የሚያገኘው አልበቃህ ብሎት ከዐቅም በላይ ገንዘብ እየቀረጠ

61 Heroes of the Faith· p.158-160; Jesus Our Saviour, coe. L.W. Brown., The Indian Christians of St. Thomas (1956)

62 ስንክሳር ጥቅምት 12

ነጋዴዎችን እንዳላስመረረ ድኾችን በነፃ የሚያበላ፣ ድውያንን በነፃ የሚፈውስ ሲያገኝ ተገርሞ ሥራውን ርግፍ አድርጐ ትቶ ተከተለው።

አባቶቻችን ቅዱስ ማቴዎስን የቊም ተገጣሩን አውጥቶ ጌታን የተከተለ ሐዋርያ ነው ይሉታል። ምክንያቱም ለሐዋርያነት በተመረጠ ጊዜ በቤቱ ድግስ ደግሞ ጌታን ጋብዟልና ነው። ማቴ.9፥10–13።

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በፍልስጥኤም፣ በፋርስ፣ በባቢሎን፣ በኢትዮጵያና በአረቢያ አካባቢ እንደሰበከ ይነገራል። ብዙ የምሥራቅም ሆነ የምዕራብ ሊቃውንት እንዲያውም፣ በሰማዕትነት ያረፈው በኢትዮጵያ ነው የሚል አመለካከት አላቸው።[63]

ይህ አመለካከት ግን ትክክል አለመሆኑን

1. በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ወይም ትውፊት አለመገኘቱ
2. የነቀዳግዊ ምኒልክ እና ንግሥተ ሳባ ዐፅም ሲገኝ የርሱ ግን አለመገኘቱ በዋና ማስረጃነት ያረጋግጣሉ።

እንዲያውም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚገለጠው በኢትዮጵያ አስቀድመው ወንጌልን የሰበኩት በዓለሃምሳን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በነበሩበት ወቅት በሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ካመኑት 3000 ምእመናን መካከል በነበሩት ኢትዮጵያውያን[64] (ዮሐንስ አፈወርቅ በበዓለሃምሳ ድርሳኑ እንደገለጠው።) ቀጥሎም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው።[65]

የቅዱስ ማቴዎስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ከነዚህ በኋላ ነው። በሌላው ዓለም ክርስትናን አስቀድመው የተቀበሉት ድኾችና በዝቅተኛ ኑሮ (lower class) የሚገኙት ሲሆኑ በኢትዮጵያ ግን አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን የነበረውን ትንቢት ያውቁትም ይጠብቁትም ስለነበር፤ ክርስትናው ቀድሞ የተሰበከው በነገሥታቱ አካባቢ (upper class) ነው። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም የንግሥት ሕንደኬ የገንዘብዋ አዛዥ (በጅሮንድ) በመሆኑ እርሱ የተቀበለውን

63 7th Book of Apocryphal Acts of the Apostles .

64 Migne PG.Vol.LII,Col.812

65 HE(Classical Library,) London. 1927.Vol. I.pp.104-110.



እምነት ረግጦ ማቴዎስን ለሰማዕትነት የሚዳርግ ሊኖር አይችልም። እንዲያውም ኢትዮጵያውያንን ከሌላው ዓለም ክርስቲያን ሕዝብ ልዩ የሚያደርገን ያንድም ሐዋርያ ደም ሳይፈስ ማመናችን ነው።

በርግጥ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን አስተምሮአል። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ሩፊኖስም ይህንኑ አረጋግጦአል።[66] የሀገራችን ሊቃውንትም ያስተማረው በትግራይ በስተምዕራብ በአድዋ አውራጃ ልዩ ስሙ ናዕዱር በተባለ ቦታ መሆኑን ያስትምራሉ።[67] አንድ በዐረብኛ የተጻፈ ስንክሣር ደግሞ በገጽ 76 ላይ ወንጌላዊው ማቴዎስ በትግራይ እንደሰበከ ይገልጣል።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ የሚያቀርቡት ሌላው ማስረጃ የማቴዎስ ወንጌልን ነው። ቅዱስ ማቴዎስ ከሌሎች ወንጌላውያን ተለይቶ የሰብአ ሰገልን (የጥበብ ሰዎች) ታሪክ የጻፈው በነዚህ ሀገሮች በማስተማሩ ነው።

የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ

የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ።

መዝ.71(72)፥10

የተርሴስና የደሴቶች – ፋርስና ባቢሎን

የዓረብና የሳባ – የመንና ኢትዮጵያ ናቸው።

ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከኢትዮጵያ በስተ ምሥራቅ ያለው ሀገር (እስከ ሕንድ) ምሥራቅ እየተባለ ይጠራል። ማቴዎስ በወንጌሉ ‹ከምሥራቅ የመጡ› ያለው በዚህ መሠረት ነው።

ገድለ ሐዋርያት ቅዱስ ማቴዎስ በግሪክ (አጵሎን የተባለ ጣዖት ይመለክበት በነበረ ቦታ) እንዳስተማረ ይናገራል።[68] በመጨረሻ ግን በፍልስጥኤም ሲያስትምር የአይሁድና የአረማውያንንም ትምህርት ሲቃወም፣ ድውያንን ሲፈውስ፣ አጋንንትን ሲያወጣ በማየታቸው የሀገሩ ሰዎች ወደ እሥር ቤት ጣሉት።

66 Rufinus: 9:1

67 ትንሣኤ 61/75፣ ገጽ 8–9

68 ገድለ ሐዋርያት፣ ገጽ 101

በእሥር ቤቱ ውስጥ እያለ አንድ እሥረኛ አጋጠመው። እሥረኛው ዘወትር ሐዘንና ትካዜ ያበዛል። ሐዋርያው ማቴዎስ አንድ ቀን ጠጋ ብሎ እያጽናናው ለምን እንደሚያዝንና እንደሚተክዝ ጠየቀው። «ጌታዬ ባለጸጋ ነው። እኔም በመርከቡ እየተመላለስኩ እነግድለት ነበር። ባለፈው ሰሞን ግን ከንግዱ ስመለስ አልቀናኝም። ማዕበል ተነሥቶ መርከቤ ከነዕቃዋ ሰጠመች፤ ገንዘቤን ባሕር በላው። እኔም በስንት መከራ ተርፌ መጣሁና ለጌታዬ የሆነውን ሁሉ ነገርኩት። እርሱ ግን በደረሰብኝ ከማዘን በመትረፌም ከመደሰት ይልቅ መርከቡን በማስጠሜ ተበሳጭቶ ለእሥር ዳረገኝ» አለው።

ቅዱስ ማቴዎስ «አይዞህ ከጥቂት ቀናት በኋላ ይፈታሃል» በማለት ማንም ተናግሮት፤ እርሱም አስቦት የማያውቅ ነገር ተናገረው። «ጌታህ ሊቀጣህ ይመጣል። በዚህ ጊዜ ‹እባክህ መርከብህ ከባሕር ወጥቷልና ላምጣው› በለው ወደ ባሕሩ ስትወርድ መርከብህን ታገኘዋለህ።» በማለት አጽናናው።

ቅዱስ ማቴዎስ የተናገረው አልቀረም ከጥቂት ቀናት በኋላ ያ ባለጸጋ ሊቀጣው አገልጋዩን ጠራው። እርሱም እንዲታገሠውና ጊዜ እንዲሰጠው ለመነው። አገልጋዩ ወደ ባሕር ወረደ። መርከቧ በባሕሩ ላይ ከነሙሉ ሀብቷ ትንሳፈፋለች። እየቀዘፈ አምጥቶ ለባለጸጋው የነገደውን ሁሉ አስረከበው። ባለጸጋውም የሆነውን ሁሉ እንዲነግረው አገልጋዩን ጠየቀው። አገልጋዩም «የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆነ ማቴዎስ መርከቤን እንደማገኝ ነገረኝ። እንዳለውም አገኘሁ።» ሲል መለሰለት። «ለመሆኑ የት ይገኛል?» አለ ባለጸጋው «በእሥር ቤቱ ውስጥ ወንጌልን እየሰበከ ይገኛል» አለው አገልጋዩም።

ያ ባለጸጋ ማቴዎስን አስጠርቶ ክርስትናን በመማር አምኖ ተጠመቀ። ቤተሰቡም ተከተሉት። ወሬውም በከተማው ሁሉ ተዳረሰ። ይህንን የሰሙት መኳንንትም ማቴዎስን ለንጉሡ ከሰሱት። ንጉሡም በመኳንንቱ ተመርቶ በማቴዎስ ላይ ሞትን ፈረደበት። ጥቅምት 12 ቀን አንገቱን ተሠይፎ ዐረፈ። ያ ባለጸጋም በድብቅ ወስዶ ቀበረው።[69]

69 ገድለ ሐዋርያት፤ ገጽ 101–118።



## የማቴዎስ ወንጌል

ይህ ወንጌል በምዕራፎች ብዛት የመጀመሪያው ወንጌል በመሆን 28 ምዕራፎች ዐቅፎአል። በቁጥሮች ብዛት ደግሞ ሁለተኛ ወንጌል ሆኖ 1068 ቁጥሮችን አካትቶአል። የተጻፈው ከማርቆስ ወንጌል ቀጥሎ በ58 ዓ.ም አካባቢ ነው። የጌታን ትምህርት በሰፊው በማቅረብ ቀዳሚውን ሥፍራ ይዞአል። ከ1068 ቁጥሮች መካከል 644ቱ የጌታ ትምህርቶች ናቸው። ይኸም ከወንጌሉ 60% ማለት ነው። በዚህ አቀራረቡ ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ሲዛመድ ከሉቃስና ከማርቆስ ወንጌል ይለያል።

ወንጌሉን የጻፈው ለአይሁድ በመሆኑ ከ150 በላይ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን አቅርቦአል። በዚህም የተነሣ ብሉይ ኪዳንን አብዝቶ በመጥቀስ ከሌሎቹ ወንጌሎች ይበልጣል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀድሞ በነቢያት የተነገረለት መሲሕ መሆኑን ለማስረገጥ ሲል አንድን ታሪክ ከጻፈ በኋላ ‹በዚህም...ተብሎ የተነገረው (በነቢይ የተጻፈው) ተፈጸመ› ብሎ ይመሰክራል።

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ትውፊትን በብዛት የተጠቀመ ሐዋርያ ነው።

ማቴዎስ ወንጌሉን ስለ ጻፈበት ቋንቋ ሦስት ዓይነት ሃሳብ ቀርቧል።

1. በዕብራይስጥ:- የቤተ ክርስቲያናችንን ሊቃውንት ጨምሮ ብዙ ምሁራን የተስማሙት ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌሉን በዕብራይስጥ ቋንቋ ጻፈው በሚለው ሃሳብ ነው[70] ነገር ግን እስካሁን ድረስ የዕብራይስጡ ዋና ቅጅ (original copy) አልተገኘም።

2. በአራማይክ:- ፓፒያስ የተባለው አባት በ2ኛው መ/ክ/ዘመን እንደገለጠው ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ አስቀድሞ የጌታችንን ትምህርቶችን በአራማይክ ቋንቋ ሎጂያ (logia) በተባለ መጽሐፍ ሰብስቦት ነበር።[71] በኋላም ወንጌሉን ሲጽፍ የጌታን ትምህርቶች የገለበጠው ከዚህ መጽሐፉ ነው።

70 ገድለ ሐዋርያት፤ ገጽ 101

71 ሎጂያ ማለት:- ቃላት (The Sayings) ማለት ነው ::

አራማይክ ከዕብራይስጥ ዘዬዎች (dialects) አንዱ ሲሆን በመጀመሪያው መ/ክ/ዘመን አካባቢ የመካከለኛው ምሥራቅ (በተለይም በፍልስጥኤም ምድር) ዋና ቋንቋ (lingua franca) ነበረ። ጌታም ወንጌሉን የሰበከው በአራማይክ ቋንቋ በመሆኑ ማቴዎስ የወንጌሉን መነሻ ረቂቅ በዚህ ቋንቋ ጽፎታል። በወንጌሉ ግን እጅግ በጣም ጥቂት ቃላትን (ለምሳሌ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ። ማቴ.27፥46) ብቻ ከመጠቀሙ በቀር የአራማይክ ቃላት ተተርጉመው ቀርበዋል እንጂ አጻጻፉ አራማይክን አልተከተለም።

፫. በግሪክ:- አብዛኞቹ ጥንታውያን ቅጂዎች የሚገኙት በግሪክ ቋንቋ በመሆኑ በግሪክ ቋንቋ ተጻፈ የሚል ሃሳብ አለ። ጥንታውያን አበው (Apologists) የማቴዎስን ወንጌል ሲጠቅሱ የተጠቀሙትም የግሪኩን ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት ግን የማቴዎስን ወንጌል ወደ ግሪክ (ፅርዕ) የተረጐመው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።[72]

የማቴዎስ ወንጌል ከማርቆስ ወንጌል በኋላ በሁለተኛነት ተጽፎ እያለ የመጀመሪያውን ተርታ ያገኘበት ዋናው ምክንያት አቀራረቡ ለብሉይ ኪዳንና ለሐዲስ ኪዳን ድልድይ ስለሆነና የብሉይ ትንቢትና ምሳሌ በሐዲስ ኪዳን መፈጸሙን ስለሚያሳይ ነው። ወንጌሉን የጻፈው በምድረ ይሁዳ ተቀምጦ እንደሆነ ይነገራል።[73]

## 9. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ (ወልደ እልፍዮስ)

በመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ዝርዝር ላይ በአራቱም ቦታ የዘጠነኛነት ሥፍራን ይዞአል። በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የጌታ ወንድም፣ ወልደ እልፍዮስ፣ ታናሹ ያዕቆብ እየተባለ ተጠርቷል።[74] ጸሎት ወዳድ በመሆኑ ለብዙ ሰዓታት መቆም ስለሚያበዛ እግሩ ያብጥበት ነበር። በዚህም የተነሣ እንደ አሥራ አንዱ ሐዋርያት ተዘዋውሮ ለማስተማር ባለመቻሉ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ በመሆን ተሾመ።[75]

72 ትርጓሜ ወንጌል የማቴዎስ ወንጌል፤ መቅድም፤ ትንሣኤ 131/81፤ ገጽ 18።
73 ELkraza, Vol.1, No.9. Sept.p.15
74 «ያዕቆቦች» የሚለውን ርዕስ ተመልከት
75 ገድለ ሐዋርያት፤ ገጽ 78



በ50 ዓ.ም አካባቢ በኢየሩሳሌም የተደረገችውን ሲኖዶስ በሊቀ መንበርነት የመራውም እርሱ ነው። የሐዋ.15፥13። በኢየሩሳሌም መንበር ለ28 ዓመታት ያህል አገልግሏል።

በኢየሩሳሌም ከተማ ቴርዮብስጣ የተባለች ደግ ሴት ትኖር ነበር። ባልዋ አማንዮስ የሚባል ከአይሁድ ምሁራን ወገን የነበረ ሰው ነው። 20 ዓመት በትዳር ሲኖሩ ልጅ አልነበራቸውም። አንድ ቀን የቅዱስ ያዕቆብን ዝና ሰማችና ወደእርሱ መጥታ «እባክህ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጠኝ ጸልይልኝ› ብላ ለመነችው። ቅዱስ ያዕቆብም «አይዞሽ አትዘኚ፤ እመኚ እንጂ ይደረግልሻል» ብሎ አጽናንቶ ወደ ቤቷ ሰደዳት።

ቅዱስ ያዕቆብ ይህን በነገራት በዓመቱ ወንድ ልጅ ስለወለደች ወደ ቅዱስ ያዕቆብ ዘንድ ወስዳ አስባረከችው። ስትመለስም የሆነውን ሁሉ ለባልዋ አጫወተችው። እርሱ ግን እጅግ ስለተበሳጨ ‹የክርስቲያኖች ኃይል እየጠነከረ ከሄደማ ያሠጋናል› የሚል ሃሳብ ስለተቀረፀበት ለወቅቱ የኢየሩሳሌም ሊቀ ካህናት ለሐናንያ ነግሮ አይሁድን በማሳመፅ ምክንያት ፈጥረው ያዕቆብን አሠሩት።[76]

ሊቀ ካህናቱ አይሁድን በቤተ መቅደሱ ዙርያ ከሰበሰበ በኋላ ቅዱስ ያዕቆብን ወደ መቅደሱ ጫፍ አውጥቶ ‹በዚህ ሕዝብ ፊት ክርስቶስን ክደህ አስተምር› ሲል አዘዘው። ዜና አይሁድን የጻፈው ዮሴፍ ወልደ ኩርዮን እንደገለጠው ቅዱስ ያዕቆብ ጌታን በመካድ ፈንታ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከሩን ቀጠለ። በዚህ የተናደዱት የአይሁድ አለቆች ያዕቆብን ከቤተ መቅደሱ ጫፍ ወረወሩት። ከዚያም በሥር የተሰባሰቡት አይሁድ በድንጋይ ደብድበው ገደሉት። ይህም እንደ ዮሴፍ ወልደኩርዮን ዘገባ የካቲት 10 ቀን 62 ዓ.ም ነው።[77]

ከዮሴፍ ወልደ ኩርዮን በኋላ 100 ዓመት ቆይቶ ወደ ክርስትና የተመለሰው ሄገስጶስም (Hegesippus) ይህንኑ ታሪክ ከተረከ በኋላ ‹ቅዱስ ያዕቆብን ሊወረውሩት ሲዘጋጁ ‹ሥጋዬን ወርውሩት፣ ነፍሴን ግን ክርስቶስ እጆቹን ዘርግቶ ይቀበላታል› ማለቱን ገልጦአል።[78]

76 ገድለ ሐዋርያት፤ ገጽ፥73–82
77 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 169።
78 ትንሣኤ 65/75፤ ገጽ 10–11

## የያዕቆብ መልእክት

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ከ35 ዓ.ም የቅዱስ እስጢፋኖስ ሞት ጀምሮ በሚደርሰው የክርስቲያኖች መከራ የተነሣ በየሀገሩ ለተበተኑ፣ ከይሁዲነት ለተመለሱ ክርስቲያኖች መጽናኛ ይሆናቸው ዘንድ መልእክቲቱን በ50 ዓ.ም አካባቢ ጽፎላቸዋል።[79]

የያዕቆብ መልእክት ‹የምክር መልእክት›፣ ‹አባታዊ መልእክት› በመባል ይጠራል። ክርስቲያኖች በኑሮአቸው በውስጥና በውጭ የሚያጋጥሙዋቸውን ነገሮች እያነሣ የሚመክር አባት ነው። ስለ ሕይወት፣ ስለፈተና፣ ስለ ሃይማኖት፣ ስለ ምግባር፣ ስለ ንግግር፣ ስለ ጸሎት፣ እርስ በርስ ስለ መረዳዳት፣ የወደቁትን ስለማንሣት ወዘተ. ያልመከረው ምክር የለም።

መልእክቲቱ በጠቅላላ ወደ 28 የሚጠጉ ነጥቦችን የያዘች ናት። ከ13 ጊዜ በላይ ‹ወንድሞቼ ሆይ› እያለ በትህትና ይጽፋልና ‹የፍቅርና የትህትና መልእክት› በመባልም ትጠራለች።

## 10. ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ[80]

ሐዋርያው ታዴዎስ በሐዋርያት ዝርዝር፣ በማቴዎስና የማርቆስ ወንጌሎች ታዴዎስ (ልብድዮስ) ብለው ሲጠሩት፣ ሉቃስ ደግሞ በወንጌሉ የያዕቆብ ይሁዳ፣ በሐዋርያት ሥራ ደግሞ ‹የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ› ይለዋል። የጌታችን ወንድሞች ከተባሉት መካከል አንዱ ነው። በአራቱም የሐዋርያት ዝርዝር የአሥረኛ ቦታ ይዞ ይገኛል።

በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት የታዴዎስ ሀገረ ስብከቱ ሶርያ ነው። ከኢየሩሳሌም 150 ኪ.ሜ ርቀት ላይ። ቅዱስ ጴጥሮስ ለሐዋርያት እንደ አባት የሚታይ በመሆኑ ታዴዎስን ወደ ሀገረ ስብከቱ ለማድረስ አብሮት ተጉዞ ነበር። በከተማዋ አጠገብ ሲደርሱም አንድ ሽማግሌ ሲያርሱ አገኙዋቸውና ቅዱስ ጴጥሮስ ጠጋ ብሎ

‹እባክዎ የምንበላው ነገር ይሰጡንን?› በማለት ጠየቃቸው። እኒያም ሽማግሌ ደግ ስለነበሩ። ‹ከቤቴ እስካመጣላችሁ ድረስ በሮቼን ጠብቁልኝ› ብለው ወደ መንደር ገቡ።

ሁለቱ ሐዋርያት የገበሬውን ደግነት ተመልክተው ታዴዎስ ጠምዶ ሲያርስ ቅዱስ ጴጥሮስ መዝራት ጀመረ።

ታዴዎስ ቀንተ ከመ ይሕርስ ገራህተ  
ወጴጥሮስ ዘርዐ ፴ አትልምተ  
በቅለ ሶቤሃ ወፈረየ ሰዊተ  
ሰብአ ሀገር አንከሩ እስመርእዩ ዘንተ

እንዳለው ባለቅኔው የተዘራው እህል በአንድ ቀን በቅሎ፣ አሽቶ ገበሬው ምግብ ይዞ ሲመለስ ጠበቀው። ይህን ታላቅ ተአምር የተመለከተው ገበሬ ባየው ነገር ሁሉ እየተደነቀ ሁለቱን ሐዋርያት ‹እናንተ ከሰማይ የወረዳችሁ አማልክት ናችሁን?› ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም የመጡበትን ምክንያትና ሀገር አስረዱት። ወንጌልንም ሰበኩለት።

ገበሬው በአድናቆት እሸቱን ታቅፎ ለሚስቱ ሊያሳይ ወደ ቤቱ ሮጠ። የከተማዋ ሰዎችም ነገሩ ገርሞዋቸው ከበቡት። እርሱም ያየውንና የሰማውን ሁሉ ተረከላቸው።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። የከተማዋ መኳንንትም ነገሩን በሰሙ ጊዜ:- ‹ይህ ከአሥራ ሁለቱ አስማተኞች ወገን ሳይሆን አይቀርምና ወደ ከተማችን እንዳይገባ ምን እናድርግ› ተባባሉ። ከመካከላቸውም አንዱ «እነዚህ አሥራ ሁለቱ አስማተኞች ዝሙትን ይፀየፋሉና ዘማዊት ሴት በከተማችን በር እናቁም» ብሎ ስለመከራቸው በከተማቸው መግቢያ በር ላይ የታወቀች ዘማዊት ራቁትዋን አድርገው አቆሙዋት።

ሐዋርያው ታዴዎስ ገጠር ገጠሩን ሲያስተምር ውሎ ወደ ማታ ወደ ከተማዋ ሲመጣ ያቺን ዘማዊት ሴት በከተማው በር ቆማ አያት። የምታደርገው ሁሉ የሚያጸይፍ ነበር። ያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። በዚህ ሰዓት ወደ አየር ወጥታ በነፋስ አውታር ተንጠለጠለች። የሀገሩም ሰዎች በሚያዩት ነገር እስኪገረሙ ድረስ ትጮህ ነበር። እርሱም ወደ ከተማዋ ገብቶ ወንጌልን መስበኩን ቀጠለ። ያችንም

79 የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 206

80 ሐዋርያው ታዴዎስ ከሰባ ሁለቱ አርድእት ወገን ከሆነው ታዴዎስ ይለያል። የታዴዎስ ረድእ ስም ብዙ ጊዜ በተለያዩ ጽሑፎች ላይ ከሐዋርያው ታዴዎስ ጋር ሲምታታ ይታያል። ታዴዎስ ረድእ የሐዋርያው ቶማስ ደቀ መዝሙር የነበረ፣ አቢጋርን የፈወሰ፣ የሶርያ ቤተ ክርስቲያንን የሰበከ፣ በሌላ ስሙ አዳይ እየተባለ የሚጠራው ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 117። (New Inter.Dictionary of Christian Church,p.12)

ሴት ከተንጠለጠለችበት አውርዶ አሳምኖ በማጥመቅ በቤትዋ የክርስቲያኖችን ጉባዔ መሥርቷል።

በከተማዋ ውስጥ እያስተማረ ለአያሌ ቀናት ሰነበተ። አንድ ቀን ‹ባለጸጋ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብታልፍ ይቀላል› እያለ ሲያስተምር አንድ ባለጸጋ ሰማና በአጠገቡ ወደሚያልፉት የግመል ነጋድያን እያመለከተ:- ‹እስቲ የተናገርከውን አድርገህ አሳየኝ› በማለት ጠየቀው። ሐዋርያው ታዴዎስም አንድ ብረት አንጣሪ ክርስቲያን ወዳጅ ነበረውና መርፌ ሠርቶ እንዲያመጣለት ላከበት። ያም ወዳጁ የጠቀመው መስሎት ቀዳዳውን አስፍቶ ሰጠው። ታዴዎስ ግን ቀዳዳው እንደ ሌላው መርፌ እንዲሆን አስደርጎ፣ ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ ‹ላመን ሁሉ ይቻላል› ነውና ግመሏን በመርፌ ቀዳዳ አሾልኮ አሳየው።

በዚህም የተነሣ በዙሪያው የነበሩት ሁሉ በትምህርቱ አመኑ።

ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ ከሶርያ በኋላ በፐርሺያ አውራጃዎች ሲያስተምር ቆይቶ ሐምሌ 2 ቀን በሰማዕትነት ዐርፎአል።[81]

አስቀድመን በሐዋርያው ቶማስ ታሪክ እንዳየነው ኤዴሳ (ዑር) በቶማስ ደቀ መዝሙር በታዴዎስ (አዳይ) (ከሰባ ሁለቱ አርድዕት ወገን በሆነው) ስብከትና በንጉሥ አብጋር ዑካማ ጥረት ያመነች ከተማ በመሆንዋ ሐዋርያው ታዴዎስ በዚህች ሀገር ሰብኮ ቢሆን ኖሮ መልካም አቀባበል በጠበቀው ነበር።

ስለዚህም ሐዋርያው ታዴዎስ የሰበከው በኤዴሳ ነው ሊባለት ያስቸግራል። ምናልባት ከተማዋ ታዋቂ የንጉሥ መናገሻ በመሆንዋ አካባቢው (ግዛቷ) በሙሉ በስሟ ተጠርቶ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ የእሥራኤልን ምድር ኢየሩሳሌም እንደምንለው ማለት ነው።

ሐዋርያው ታዴዎስ በፐርሺያ በሰፊው ማስተማሩንና በሰማዕትነት ያረፈውም በዚያ መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተስማምተውበታል።[82]

---

81 ስንክሣር ሐምሌ 2፤ ገድለ ሐዋርያት፣ ገጽ 251-254፤ ትንሣኤ 104/78፣ገጽ6።

82 Dictionary of Saints p.206, Oxford Christian Dictionary, p. New Catholic Encyclopaedia, p.16-17.



## የሐዋርያው የይሁዳ (ታዴዎስ) መልእክት

መልእክቲቱ የተጻፈችው ከሐዋርያው ከቅዱስ ጴጥሮስ መልእክታት በኋላ መሆኑን ሐዋርያው ከቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት መጥቀሱ ያመላክተናል። 2ጴጥ.3፥2። በመሆኑም በ65 ዓ.ም አካባቢ መጻፍዋ ይነገራል።

ሐዋርያው ይሁዳ (ታዴዎስ) መልእክቱን የጻፈው በግኖስቲኮች ትምህርት ግራ ተጋብተው ለነበሩ የታናሺ እስያና የመካከለኛው ምሥራቅ ክርስቲያኖች ነው።

መልእክቱን ሲጽፍ የሙሴን ገድል ከሚናገረው መጽሐፍ (ዜና ሙሴ) (The assumption of Moses) መጥቀሱ ሐዋርያት ለአዋልድ መጻሕፍት ይሰጡት የነበረውን ክብር ይገልጥልናል። በተጨማሪ ደግሞ ከመጽሐፈ ሄኖክ ጠቅሶ ጽፎአልና የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር 66 ብቻ አለመሆኑን ያስረዳል።

## 11. ሐዋርያው ስምዖን (ቀነናዊ)

ሐዋርያው ስምዖን ከአራቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ዝርዝሮች መካከል ማቴዎስና ማርቆስ በአሥራ አንደኛው ሥፍራ ሲያስቀምጡት ሐዋርያው ቅዱስ ሉቃስ ደግሞ በወንጌሉና በሐዋርያት ሥራ በአሥረኛ ቦታ አስፍሮታል።

የሐዋርያው ስምዖን ሌላው ስሙ ናትናኤል ነው። ስምዖን የመጀመሪያ ስሙ ሲሆን ናትናኤል ብሎ የሰየመው ጌታ ነው። ትርጉሙም ‹የእግዚአብሔር ስጦታ› ማለት ነው። የተወለደው በናዝሬት ቃና ዘገሊላ ሲሆን ነገዱ ከብንያም ነው። የትውልድ ዘመኑ ጌታችን በተወለደበት ዘመን አካባቢ ነው። ምክንያቱም ሄሮድስ የቤተ ልሔም ሕፃናትን በሚያስፈጅበት ጊዜ እናቱ ከበለስ ሥር ደብቃ አትርፋዋለች። ጌታም ፊልጶስ ናትናኤልን ሲጠራው ‹ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ ሥር ሳለህ ዐውቅሃለሁ› ያለው ለዚህ ነው።

ቅዱስ አውግስጢኖስ ደግሞ ናትናኤልን ‹ምሁረ ኦሪት ነበረ› ይለዋል። ምክንያቱም ፊልጶስ ሲጠራው ‹ከናዝሬት መልካም ነገር አይወጣም› በማለት የነቢያትን ቃል የጠቀሰው የመጻሕፍትን ቃል በማወቁ ነበርና። ዮሐ.1፥44-52።

ስምዖን (ናትናኤል) የቀነናውያን ቡድን አባል ለመሆን የበቃው በዚህ ለኦሪት ሕግ በነበረው ቅንዓት ሳይሆን አይቀርም። ይህ ቡድን በወቅቱ በሮማውያን ላይ ዐምፀው ለተነሡት አይሁድ የተሰጠ ‹ከነነዓት› ከሚለው የአራማይክ ቃል የተገኘ ስም ሲሆን ትርጉሙም ቀናተኛ ማለት ነው። እነዚህ ቀነናውያን ለኦሪት እምነትና ለሀገረ አይሁድ ቀናዕያን የሆኑና ሮማውያንን ከርስታቸው ለማስወጣት ውስጥ ለውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ናቸው። ስምዖን የነዚህ አባል ስለነበር ቀነናዊ እየተባለ ይጠራል።

ስምዖን ሐዋርያው በሶርያ፣ በባቢሎን በግብፅ[83] እና ኑቢያ አስተምሮአል። ብዙ ዘመኑን ያሳለፈውም በዚሁ በሰሜን አፍሪካ በማስተማር ነው። በመጨረሻም በግብፅ ሲያስተምር ሕዝቡ በትምህርቱ አምነው በመብዛታቸው አረማውያኑ ስለቀኑበት ሁከት አስነሥተው ‹የማንፈልገውን ሃይማኖት ተቀበሉ ይለናል› በማለት ለግብፁ ንጉሥ እንድርያኖስ ከሰሱት ንጉሡም በሠራዊቱ አስይዞ በማስመጣት ሐምሌ አሥር ቀን በሠይፍ አስገድሎታል።[84]

## 12. ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ

ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ ጌታን አሳልፎ በመሸጡ ክብሩን ባቃለለውና በኋላም በገዛ እጁ ታንቆ በሞተው በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ የተሾመ ሐዋርያ ነው። የሐዋ.1፥15–26። አስቀድሞ ቁጥሩ ከሰባ ሁለቱ አርድእት እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አወሳብዮስ መስክሮአል።[85] ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ‹ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ከእኛ ዘንድ እስካረገበት ድረስ፣ ጌታ ኢየሱስ በኛ መካከል በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ ከእኛ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች፣ ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምሥክር ይሆን ዘንድ ይገባል።» የሐዋ.1፥21–22። ብሎ የተናገረውም ለዚሁ ነበር።

በገድለ ሐዋርያት እንደተገለጠው ማትያስ ይሰብክበት ዘንድ ዕጣ የደረሰው ‹በላዕተ ሰብእ› የሚባሉ ሰዎች ወደሚኖሩበት ሀገር ነው። ይህ ሀገር ምናልባት በእስኩቴስ (ሩሲያ) ሳይኖር አይቀርም።

83 The See of St. Mark and The School of Alexandria, p. 9

84 ስንክሳር፣ ሐምሌ 10

85 Eusebius: 1:13:3



ምክንያቱም አውሳብዮስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጽሐፉ ይህ ቦታ በጥንቱ ዓለም አጠራር በርባሮስ ይባል የነበረው መሆኑን ሲገልጥ[86] ዜና አይሁድን የጻፈው ዮሴፍ ወልደ ኩርዮን ደግሞ የበርባሮስ (እስኩቴስ) ሰዎች በዚያ ዘመን ጨካኞችና ከአራዊት ያልተሻሉ አረመኔዎች እንደነበሩ ገልጦአል።[87]

ማትያስ በዚህ ሀገር ሲያስትምር እነዚህ ሰዎች ያዙትና ዓይኑን አውጥተው እንደ እንስሳ ሣር ያበሉት ጀመር። ምክንያቱም የዚህ ሀገር ሰዎች ሰውን ከመብላታቸው በፊት ዓይኑን አጥፍተው ለ40 ቀናት ያህል ሣር ማብላት ልማዳቸው ስለነበር ነው።

ሐዋርያው ማትያስ ለ40 ቀናት በእሥር ቤት ተቀመጠ። እግዚአብሔር ጽናቱን ስለሰጠው። ያቀረቡለትን ሣር ሳይበላ በጾም አሳለፈው። በዐርባኛውም ቀን ማትያስ ሣሩን ከፊቱ ከምር ሲዘምር እንድርያስ ከእግዚአብሔር ተልኮ በተዘጋው በር ገባ። በደስታና በናፍቆት ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ ‹እንደ በጐች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ የሚለው ቃል ዛሬ በአንተ ተፈጸመ› ሲል የጌታን ቃል አስታወሰው። ከእሥር ቤትም ይዞት ወጣ። አብረውት በዚያው ታሥረው የነበሩ 123 ሰዎችም ወጡ።

ይህንን ተአምር ያዩት የሀገሪቱ ሰዎች በትምህርቱ አምነው ተጠመቁ። ለነዚህ ሰዎችም መጽሐፍ ጽፎ እንደሰጣቸው እነ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ መስክረዋል።

> ‹ከአንተ በፊት የነበሩ ነገሮችን አድንቅ ተጨማሪ ዕውቀት ለማግኘት ይህን የመጀመሪያ መሠረት አድርግ›
>
> ቀሌምንጦስ

እንዲሁም ከአዋልድ ወገን ከሚመደበው የማትያስ መጽሐፍ ‹ከሥጋ ጋር መታገል፣ ለሥጋዊ ምኞትም ድል አለመሆን ይገባል› የሚለው ቃል ተገኘ ተብሎ በጥንት ጸሐፍት ተጠቅሶአል።[88]

ቅዱስ ማትያስ ከዚህ በኋላ ደማስቆ ገብቶ ስብከተ ወንጌሉን ቀጥሏል። የደማስቆ ሰዎች ግን አስቀድመው ከኢየሩሳሌም ወደ

86 ዝኒ ከማሁ 3፥1

87 Josephus, Against Apian, p. 237

88 የፊሊስ ኪዳን አዋልድ፣ ገጽ 12–13።

ከተማዋ በገቡት አይሁድና በአረማውያንም ቅስቀሳ ተቃዋሚዎች ተነሥተው በብረት አልጋ በማስተኛት ከሥሩ ለሰባት ቀናት ያህል እሳት ለቀቁበት። በሰባተኛው ቀን ሲመለሱ አንዳች ጉዳት ሳይደርስበት በማግኘታቸው በትምህርቱ አምነው ተጠምቀዋል። በመጨረሻም በሀገረ ይሁዳ ሲያስተምር ከኖረ በኋላ ፊላዎን በተባለች ቦታ ሸምግሎ ዕድሜም ጠግቦ ዐርፎአል።

በዓለ ዕረፍቱም መጋቢት 8 ቀን ይከበራል።[89]

## ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

### ከልደቱ እስከ ጥምቀቱ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ዘሩ ከዕብራውያን፣ ከብንያም ነገድ ሲሆን የተወለደውም በጠርሴስ ከተማ ነው።[90] ጠርሴስ በንግድዋ የታወቀች የኪልቂያ ዋና ከተማ ናት። በከተማዋ እስከ አምስት መቶ ሺህ የሚገመቱ ከየሀገሩ የተሰባሰቡ ሕዝቦች ነበሩባት። ሮማውያን በሥራቸው ለሚተዳደሩት ሕዝቦች ሮማዊ ዜግነትን ይሰጡ ስለነበር፥ የቅዱስ ጳውሎስ አባት በዜግነት ሮማዊ ነበር። ይህም ለቅዱስ ጳውሎስ ተላልፎለታል።

ቅዱስ ጳውሎስ በ15 ዓመት ዕድሜው ወደ ትውልድ ሀገሩ በመመለስ በኢየሩሳሌም ከነበረው የታወቀው የገማልያል ትምህርት ቤት ገባ።[91] በዚያም የአይሁድን ሕግና ሥርዓት እየተማረ እስከ 30 ዓመቱ ቆየ። ገማልያል ፈሪሳዊ ስለነበር ጳውሎስም ይህን ተቀብሎታል። በ30 ዓመቱ የአይሁድ ሸንጎ (ሳን ኼድሪን) አካል ሆኖ ተቆጠረ።[92]

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ዘመን ቅዱስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ስለነበረ ሁኔታዎቹን ሁሉ ያውቃል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአይሁድ ሸንጎ አባልነት ለሁለት ዓመታት በሠራበት ወቅት ለኦሪታዊ እምነቱ ቀናተኛ ፈሪሳዊ

89 ትንግሌ 66/75፤ ገጽ 8።
90 ዜና ሐዋርያት፤ ገጽ 322
91 ትንግሌ ቁ. 96/78፤ ገጽ 15–16
92 ዜና ሐዋርያት፤ ገጽ 322



በመሆኑ ክርስቲያኖችን በማናቸውም አጋጣሚ ይቃወም ነበር። እንዲያውም ሊቀዲያቆናት እስጢፋኖስ በማስተማሩ ምክንያት ተከሶ ለአይሁድ ሸንጎ በቀረበ ጊዜ የተከራከረው እርሱ ነበር። በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት ሲያርፍም የወጋሪዎችን ልብስ ይጠብቅ የነበረው እርሱ ነው። ቅዱስ አውግስጢኖስ ‹በእስጢፋኖስ ጸሎት፣ ቤተ ክርስቲያን የጠፋውን ጳውሎስን አገኘች።› በማለት ተናግሯል።

በ32 ዓመት ዕድሜው ከኢየሩሳሌም 223 ኪ.ሜ ርቀት በስተሰሜን በኩል በምትገኘው የደማስቆ ከተማ ብዙ ክርስቲያኖች መኖራቸውን ሲሰማ ወደ ሊቀ ካህናቱ ቀርቦ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት የሚያስችለውን የፈቃድ ደብዳቤ አገኘ። ከዚህ በኋላ ጭፍሮችን አስከትሎ ወደ ደማስቆ አመራ። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ከተማዋ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው ነበር ከሰማይ የወረደው ብርሃን አካባቢውን ያለበሰውና ‹ሳውል ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ?› የሚለውን ድምፅ የሰማው። ሐዋርያው ጳውሎስም ‹ጌታ ሆይ ማን ነህ?› ብሎ ጠየቀ። ‹አንተ

የምታሳድደኝ እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ። የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብኻል› ሲል መድኃኒታችን ተናገረው። ያን ጊዜም በወደቀበት ሆኖ እየተንቀጠቀጠ ‹ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?› ሲል ጠየቀ። ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ወደ ደማስቆ እንዲገባ ተነገረው። የሐዋ.9፥1።

የሐዋርያው ዓይኖች ለማየት አልቻሉም። እየተመራ ወደ ደማስቆ ገባ። ለሦስት ቀናት ያህልም እህል ሳይቀምስ ቆየ። በዚያች ዕለት እግዚአብሔር አምላክ በደማስቆ ለሚገኘው እና ሐናንያ ለተባለው አባት በራእይ ተገለጠለት። ቅዱስ ጳውሎስም ያለበትን አድራሻ ነገረውና ሄዶ እንዲያጠምቀው አዘዘው። ሐናንያ አስቀድሞ የቅዱስ ጳውሎስን ማንነት ያውቃል። አብዛኞቹ በደማስቆ የሚገኙት ክርስቲያኖች ከኢየሩሳሌም በስደት የመጡ ናቸው።[93] ያን ስደት ያስነሣው ደግሞ በቅዱስ እስጢፋኖስ ላይ የደረሰው መከራ ነው። በዚህ የቅዱስ እስጢፋኖስ ሰማዕትነት ደግሞ ዋናው ተዋናይ ሐዋርያው ጳውሎስ ነበር።

93 Wors, II,20.2; VII, VIII 7

ይህን የሚያውቀው ሐናንያ በቅድሚያ ከእግዚአብሔር ጋር መከራከር ጀምሮ ነበር። እግዚአብሔር አያውቀው ይመስል ስለ ቅዱስ ጳውሎስ ማስረዳት ጀመረ። በመጨረሻ ግን ‹ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእሥራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ፤ ስለ ስሜስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አመለክተዋለሁና› በማለት እግዚአብሔር ሐናንያን ላከው።

ሐናንያ ቅዱስ ጳውሎስን ካጠመቀውና ካስተማረውም በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ዓረብ ሀገር መሄዱን ራሱ ተናግሮአል። ገላ.1፥17።[94]

ለ3 ዓመታት በዓረቢያ በረሃ ከቆየ በኋላ ወደ ደማስቆ ከተማ ተመለሰ።[95] በዚያም በነበሩ አይሁድ መካከል በፊት ያሳድደው የነበረውን ኢየሱስ ክርስቶስን መስበክ ጀመረ። ከዚያ በፊት በፈሪሳዊነቱና ለአይሁድ ሕግ በነበረው ቅንዓት የሚታወቀው ጳውሎስ ዛሬ ወንጌል ሲሰብክ በማየታቸው አይሁድ ተነሡበት። በዚህም የተነሣ የደማስቆ ክርስቲያኖች በቅርጫት አውርደው ወደ ኢየሩሳሌም ላኩት።

ቅዱስ ጳውሎስ ኢየሩሳሌም ሲደርስ የገጠመው ሁለት ችግር ነበር። በቅድሚያ አይሁድ ጳውሎስን እንደሚያውቁት እና እንደለመዱት ሆኖ ስላላገኙት ሊገድሉት ተነሡ። በሌላ በኩል ደግሞ ክርስቲያኖች የቅዱስ ጳውሎስን መመለስ ሊያምኑ አልቻሉም። በመጨረሻ ግን በርናባስ ወደ ሐዋርያት ዘንድ ወስዶ የጳውሎስን መመለስ በመተረክ እንዲያምኑት አደረጋቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም በድፍረት በማስተማሩ አይሁድ ስለተቃወሙት ከተማዋን ትቶ በቂሳርያ በኩል ወደ ትውልድ ሀገሩ ጠርሴስ ተመለሰ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጠርሴስ ከተማ ለዘጠኝ ዓመታት ቆይቷል። ከኢየሩሳሌም ውጭ የአሕዛብ ከተማ በነበረችው በአንጾኪያ የክርስትና ሃይማኖት ተስፋፋ። ከኢየሩሳሌም የተሰደዱት

94 Coptic Orthodox Church,The Epistle of St Paul to Galatians, p.128

95 አባቶቻችን ቅዱስ ጳውሎስ ሦስቱን ዓመት በዓረቢያ በረሃ በሱባዔ እንዳሳለፈው ይተረጉሙታል።



ክርስቲያኖች የአንጾኪያን ሕዝብ ተግተው በማስተማራቸው ዝናው እስከ ኢየሩሳሌም ደረሰ። በዚህም ምክንያት በኢየሩሳሌም የነበሩት አበው በርናባስን ወደ አንጾኪያ ላኩት። በርናባስ የግሪክ ቋንቋ ችሎታ ያለውን፤ ከማንኛውም ሰው ጋር መግባባት የሚችለውን፤ ደግሞም እግዚአብሔር ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን የመረጠውን ቅዱስ ጳውሎስን ከጠርሴስ በማምጣት በአንጾኪያ ሥራቸውን ጀመሩ።

በገላትያ መልእክቱ ምዕራፍ 2 ላይ ራሱ እንደገለጠው ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ከአንጾኪያ ክርስቲያኖች የሰበሰበውን ርዳታ ይዞ ወጣ።[96] በዚህም በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረውን መለያየት ክርስትና አንድ እንዳደረገው አስመስክሮአል።

## ጉዞዎቹ

### የመጀመሪያው የቅዱስ ጳውሎስ ጉዞ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ከተመለሰ በኋላ በልዑል እግዚአብሔር ጥሪ (የሐዋ.13፥1–3) በአሕዛብ ሀገር ወንጌልን ለመስበክ ከበርናባስ ጋር ወጡ። በዚህ ጉዞአቸው በጠቅላላ ወደ 2000 ኪ.ሜ የሚደርስ መንገድ በእግር ተጉዟል። ይህም ጉዞ የተከናወነው በ46 ዓ.ም አካባቢ ነው። የተሸፈኑትም ሀገሮች ሲሊንውቂያ፤ ቆጵሮስ፤ ስልማና፤ ጳፉ፤ ጰርጌን፤ ገላትያ፤ ጵስድያ፤ ኢቆንዮን፤ ሊቃኦንያ፤ ልስጥራ፤ ደርቤን፤ ጵንፍልያ፤ አታልያ እና አንጾኪያ ናቸው።

### ሁለተኛው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ጉዞ

ሁለተኛው ጉዞ የተከናወነው በ50 ዓ.ም ገደማ ነው። በመጀመሪያው ጉዞ ማርቆስ አብሮ ተጉዞ ነበር። ነገር ግን ጵንፍልያ ከተማ ሲደርስ እናቱ ስለናፈቀችው መመለስ በመፈለጉ በርናባስ ወደ ኢየሩሳሌም ይዞት መጣ። ስለዚህም በሁለተኛው ጉዞው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲላስን ይዞ ወደ ኪልቂያ ሶርያ ሲጓዝ በርናባስ ደግሞ ማርቆስን አስከትሎ ወደ ቆጵሮስ ሄደ። በዚህ ጉዞው ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ግሪክ ደርሶአል። የተጓዘባቸውና ያስተማረባቸው ከተሞችም:-

96 9 ዓመት በጠርሴስ 5 ዓመት በአንጾኪያ

ደርብያ፣ ልስጥራ፣ ፍርግያ፣ ገላትያ፣ ሚስያ፣ ጢሮአዳ፣ ሳሞትራቄ፣ ናፓሊ፣ ፊልጵስዩስ፣ ተሰሎንቄ፣ በርያ፣ አቴና፣ ቆሮንቶስ፣ አንክራኦስ፣ ኤፌሶን፣ ቂሳርያ፣ ኢየሩሳሌም እና አንጾኪያ ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጁ ጢሞቴዎስን ያገኘው በዚሁ ጉዞው በልስጥራ ከተማ ነው።

## ሦስተኛው የቅዱስ ጳውሎስ ጉዞ

ይህ ጉዞ የተከናወነው በ54 ዓ.ም ሲሆን የተሸፈኑትም ሀገሮች የሚከተሉት ነበሩ።

ገላትያ፣ ፍርግያ፣ ኤፌሶን፣ መቄዶንያ፣ ፊልጵስዩስ፣ ቆሮንቶስ፣ ጢሮአዳ፣ አሶን፣ ሚሊጢኒን፣ አንጠቀከስዩ፣ ትሮጊሊዩም፣ መስጡ፣ ቆስ፣ ሩድ፣ ጳጥራ፣ ጢሮስ፣ ጵቶልማይስ፣ ቂሳርያ፣ ኢየሩሳሌም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከልዩ ልዩ ሀገሮች ክርስቲያኖች የሰበሰበውን ዕርዳታ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በመያዝ ሦስተኛውን ጉዞ አጠናቅቆ ኢየሩሳሌም ገባ። ነገር ግን ኢየሩሳሌም የገባበት ጊዜ የፋሲካ በዓል ስለነበር ከልዩ ልዩ ሀገሮች የተሰበሰቡ አይሁድ በከተማዋ ነበሩ። እነዚህ በዝርወት የሚኖሩ አይሁድ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን በየሀገራቸው በትምህርቱ የተነሣ ሲቃወሙት የነበሩ ናቸው።

እነኚህ አይሁድ ቅዱስ ጳውሎስን በኢየሩሳሌም ሲያዩት ታላቅ ተቃውሞ አነሡበት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ተቃውሞአቸውን ለመግታት እንደ አይሁድ ሕግ በቤተ መቅደስ የመንጻት ሥርዓት መፈጸም ጀመረ። ነገር ግን ከኤፌሶን የተከተለውን ጥሮፊሞስን ወደ መቅደስ ያስገባው ስለመሰላቸው ተቃውሞአቸው በረታ። የሐዋ.22፥29። ከተማውንም አወኩት፤ ይህ ነበር ቅዱስ ጳውሎስን በ58 ዓ.ም ለሮም እሥር የዳረገው።[97] ክብዙ መከራና ስቃይ በኋላ ታሥሮ ሮም ገባ። በዚያም በቁም እሥር ሆኖ ለሁለት ዓመታት

ያህል ወንጌልን ሰበከ። የሁለቱን ዓመት የቁም እሥር እንደጨረሰ ወደ ኔሮን ፍርድ ቤት ቀረበ። ይህም በ60ዎቹ ዓ.ም ነው። በፍርድ

97 መጽሔት አሚን፤ ገጽ 29።



ቤቱ በተደረገው ምርመራ የሮሜን ሕግ የሚቃወም ምንም ወንጀል ስላልተገኘበት በነፃ ተለቀቀ፤ ከዚህ በኋላ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አራተኛውንና የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ያልመዘገበውን ጉዞውን ያደረገው።

ይህ ጉዞው በመታሠሩ አዝነው ተክዘው የነበሩ ክርስቲያኖችን ለማጽናናት የጀመራቸውን ሥራዎች ፍጻሜ ለማየት የተደረገ ጉዞ ነው። በዚህም ጉዞው ኢየሩሳሌምን፣ ኤፌሶንን፣ ሉዶቅያን፣ መቄዶንያን፣ ቀርጤስን፣ ጢሮአዳን፣ ድልማጥያን፣ እልዋሪቆን፣ ኒቆጵልዮን፣ ብረንዲስን፣ ጐብኝቷል።[98] በዚህ የመጨረሻ የስብከት ጉዞው ለአራት ዓመታት ያህል ቆይቷል።

በመጨረሻ በ64 ዓ.ም ኔሮን በጥጋቡ የሮማ ከተማ ስትቃጠል ምን እንደምትመስል ማየት እፈልጋለሁ ብሎ አቃጠላት።[99] የሮም ሕዝብ በከተማው መቃጠል በማዘኑና በማመፁ ነገሩን ሁሉ በክርስቲያኖች ላይ አሳበበ። በዚህም የተነሣ ክርስቲያን የተባለ ሁሉ መሰደድ፣ መሠየፍ፣ መታረድ ዕጣ ፈንታው ሆነ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በኒቆጵልዮን ከተማ ሲያስተምር በ65 ዓ.ም ተይዞ ወደ ወኅኒ ገባ። ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር በጨለማ ቤት ታሥሮ ከቆየ በኋላ በ74 ዓመት ዕድሜው[100] በሮማ ከተማ በአስትያ መንገድ[101] አንገቱን ተሠይፎ በ67 ዓ.ም ሐምሌ አምስት ቀን በሰማዕትነት ዐረፈ።

## የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት

### 1. ወደ ሮሜ ሰዎች

ሮሜ ጥንት ሮምየ ትባል ነበር። በ730 ዓ.ም ኑሚቶር የሚባል ንጉሥ በሮም ነገሠ። ወራሽ ልጅ ስላልነበረው የሀገሩ ሰዎች ‹የእኅትህ ልጅ ይወርስሻል› የሚል ንግርት ነበራቸው። በኋላም እኅቱ ሬያበልብያ መንታ ልጆችን መውለዷን ሲሰማ ንግርቱ ደረሰ ብሎ

98 ዜና ሐዋርያት፤ ገጽ 320።
99 የኢትዮጵያ ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ፤ ገጽ 163
100 ዜና ሐዋርያት፤ ገጽ 322
101 በ2ኛው መ/ክ/ዘ የነበረው ጋይዮስ የተባለው ታሪክ ጸሐፊ ቅዱስ ጳውሎስ በአስትያ መንገድ መሠየፉን ጽፏል። ትንሣኤ ቁ.104/78፤ ገጽ 9።

ፈራ። ላያቸው እፈልጋለሁ ብሎ ልጆቹን ካስመጣ በኋላ በቅርጫት አድርጎ በወታደሮች እጅ አስጣላቸው። ልጆቹንም አንድ ገበሬ ሲያለቅሱ አግኝቷቸው ወደ ቤቱ በመውሰድ ጡረኛ አድርጎ አሳደጋቸው።

እነዚህ ሁለት ልጆች ካደጉ በኋላ አሞሌዎስ የተባለውን ንጉሥ ርም አቸንፈው ከተማዋን በመያዝ ነገሡባት። በኋላ ግን ሮሙለስ የተባለው ወንድሙ ሮማኖስን ገድሎ ብቻውን በመንገሥ ከተማዋን ሮማ ብሎ በስሙ ጠራት።

ከጌታችን ልደት በፊት 61 ዓመት አስቀድሞ ፓምፔ የተባለው ሮማዊ የሶርያ ገዥ በደማስቆ በኩል አልፎ ከአይሁድ ጋር በመዋጋት ኢየሩሳሌምን ከያዘ በኋላ አይሁድን ማርኮ ወደ ሮሜ ስለወሰዳቸው[102] ከሮማ ነዋሪዎች መካከል ብዙ አይሁድ ይገኙ ነበር።

ቅዱስ ጳውሎስ በ52 ዓ.ም ከአቴና ወጥቶ ወደ ቆሮንቶስ በሄደ ጊዜ በቀላውዴዎስ ቄሣር አዋጅ ከሮሜ ተሰደው የመጡ አቂላንና ጵርስቅላን አገኘ። ከእነርሱም ጋር አንድ ዓመት ከስድስት ወር ያህል ቆየ። አቂላና ጵርስቅላ በሮሜ ስለሚገኙ ክርስቲያኖች ለቅዱስ ጳውሎስ ነገሩት። እነዚህ የሮም ክርስቲያኖች በበዓለ ሃምሳ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ያመኑና (የሐዋ.2፥10።) በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ ሮሜ በገቡ ክርስቲያኖች የተሰበኩ ናቸው። የሮሜ ቤተክርስቲያን ምእመናን ከሁለት ወገን የተገኙ ነበሩ። ከአይሁድ እና ከአረማውያን። ሁለቱም በክርስትና የአንዲት ቤተክርስቲያን ልጆች መሆናቸውን ረስተው በጥንቱ ልማዳቸው የተነሣ ክርክር ፈጠሩ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች መልእክቱን ሊጽፍ የተነሣው በዚህ ምክንያት ነበር።

ቅዱስ ጳውሎስ ከሮሜ ክርስቲያኖች መካከል የሚያውቃቸው ሰዎች ስላልነበሩ አቂላና ጵርስቅላ ከከተማዋ ክርስቲያኖች የአንዳንዶቹን ስም ሰጡት። እርሱም መልእክቱን አዘጋጅቶ የአንክራኦስ ቤተክርስቲያን ዐቃቢት በነበረችው በፌቤን እጅ በ54 ዓ.ም አካባቢ ላከላቸው። ሮሜ.16፥1።

---

102 ዜና ሐዋርያት፣ ገጽ 168–71



## 2. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

የመጀመሪያዋ:- ቆሮንቶስ የአካያይ ሁለተኛ ከተማ ስትሆን የምትገኘውም በግሪክ ውስጥ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛ ጉዞው በ50 ዓ.ም አካባቢ ወደ ከተማዋ ገብቶ አስተምሮአል። በሦስተኛ ጉዞው በ54 ዓ.ም ደግሞ በኤፌሶን እያለ ልጁ ጢሞቴዎስን ቤተ ክርስቲያንዋን ጐብኝቶ ይመለስ ዘንድ ልኮላቸዋል።

ጢሞቴዎስ በቆሮንቶስ እያለ የቀለዮኤ ወገኖች የሆኑ የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ ኤፌሶን መጥተው ነበርና ስለ ቤተክርስቲያንዋ ሁኔታ ለቅዱስ ጳውሎስ ነገሩት። በምእመናን መካከል መለያየት ተነሥቶ ነበር። የመለያየቱ ዋና ዋና ምክንያቶችም:-

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮ ከሄደ በኋላ ከእስክንድርያ የመጣው አጵሎስ[103] የተማረ ሊቅ ስለነበር ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ጀመሩ።

በሌላ በኩል ደግሞ በጌታችን ዘመን ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተው ትምህርቱን የመስማት ተአምራቱን የማየት ዕድል የገጠማቸውና እንዲሁም ደግሞ ለበዓለ ሃምሳ በኢየሩሳሌም እያሉ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት አምነው የተጠመቁም ነበሩ።

እነዚህ በልዩ ልዩ ምክንያት ያመኑ ክርስቲያኖች በሃሳብ አልጣጣም ሲሉ ‹እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ እኔ የጴጥሮስ ነኝ፤ እኔ የአጵሎስ ነኝ› እያሉ መከፋፈል ጀመሩ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ችግር ከቀለዮኤ ቤተ ሰዎች ሲሰማ የመጀመሪያ መልእክቱን ጻፈላቸው[104]

2. የቆሮንቶስ ሰዎች በዝሙት የታወቁ ነበሩ። በዚያ ዘመን ‹ቆሮንቶሳዊ› ማለት ዘማዊ የሚለውን ትርጉም ይዞ ነበር። አባታቸው በሕይወት እያለ የእንጀራ እናታቸውን እስከማግባት ደርሰው ነበር። ይህንን እኩይ ምግባር ትተው በንስሐ ይመለሱ ዘንድ ጽፎላቸዋል።[105]

---

103 አጵሎስ አስቀድሞ አይሁዳዊ የነበረ ሰው ነው። በኋላ ግን ተጠምቆ ክርስቲያን በመሆን በተለይ ለአይሁድ ብሉይን በሐዲስ እያስማማ ያስተምር ነበርና ትምህርቱ ጠንካርና ጠልቆ ያለ ነበር።
104 ዜና ሐዋርያት፣ ገጽ 127– 1ቆሮ.5፥1
105 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 129

3. የቆሮንቶስ ሴቶች ወደ ፍርድ ሸንጎ ገብተው (ሳይከናነቡ) ያለባሕሉ ለባሎቻቸው እያገዙ መሟገቱን አዲስ ወግ አድርገውት ነበር። ይህ ጉዳይ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመለሱም ተከትሏቸው መጣ። ባሎቻቸው በሌሉበት መርሐ ግብሩ ለቤተሰብ የተያዘ ይመስል እኔ ተተክቼ ካልሰበክሁ ማለት ጀመሩ። ቅዳሴ ካልገባን እያሉም አስቸገሩ። በዚህም የተነሣ ቤተክርስቲያኒቱ ነውረኛ ሴቶች የተሰበሰቡባት ናት እየተባለች በዓለማውያን ዘንድ ስለተነቀፈች ቅዱስ ጳውሎስ ፀጉራቸውን እንዲከናነቡ፣ በሥርዓት እንዲኖሩ፣ በሥርዓትም እንዲማሩ መከራቸው።[106]

4. የቆሮንቶስ ሰዎች የአምልኮ ጣዖት ባሕላቸውን ወደ ቤተክርስቲያን ሥርዓት እያስገቡ አስቸገሩ። ወደ ቅዱስ ቁርባን (ወደ ቅዳሴ) ሲመጡ ሁሉም ለየግሉ ወይንና ሕብስት ይዞ ይመጣና እስኪጠግቡ በልተው፣ እስኪሰክሩ ጠጥተው ይጨቃጨቁ፣ ይደባደቡም ጀመር። ይባስ ብለው ደግሞ ወይንና ሕብስት ማምጣት ያልቻሉ ደኾችን እንዳይቆርቡ ከለከሉ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሥርዓተ ቁርባንን ያስተማራቸው ይህን ክፉ ዐመላቸውን ለማረም ነው።

5. ሌላው የቆሮንቶስ ሰዎች ችግራቸው በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መቀናናታቸው ነበር። ‹እኔም ከማን አንሳለሁ› እያሉ ሁሉም ነቢያት፣ ተርጓሚዎች፣ ሰባክያን፣ በልሳን ተናጋሪዎች ስለሆኑ አድማጭ ምእመን ጠፋ። ሁሉም ራሳቸውን ከፍ በማድረጋቸው ጭቅጭቅ ተጀመረ።

ለነዚህ ሁሉ ችግሮች ክርስቲያናዊ መልሶችን ጽፎ በጢሞቴዎስና በእስጢፋኖስ፣ በፈርዶናጥስና በአካያቆስ እጅ ላከላቸው። 1ቆሮ.15፥32–58፤ 16፥1–24። የተላከችው በ54 ዓ.ም አካባቢ ነው።

ሁለተኛዋ:- ልጁ ጢሞቴዎስ የመጀመሪያዋን መልእክት አድርሶ ከተመለሰ በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ የላከው መልእክት በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ዘንድ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነ ለማወቅ

106 ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 136



ቲቶን ላከው። እርሱ ወደ መቄዶንያ ለመሻገር አስቦ ስለነበር። በጢሮአዳ ለመገናኘት ተቀጣጠሩ። ይሁን እንጂ ቅዱስ ጳውሎስ ቲቶን በጢሮአዳ ሊያገኘው አልቻለም። ስለዚህም ወደ መቄዶንያ አለፈ። ቲቶንም በዚያ አገኘው።

ቲቶ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የላከው መልእክት ብዙዎቹን በክፉ ሥራቸው እንዲፀፀቱ ንስሐም እንደገቡ ማድረጉን ነገረው ያባቱን ሚስት ያገባውንም ከማኅበረ ምእመናን አግልለውታል። የምፅዋቱንም ገንዘብ አዋጥተው እየጠበቁት ነው።

በዚህ ሁሉ መሐል ግን ከአይሁድ ወገን የሆኑ ሐሳውያን መምህራን ወደ ወጋቸውና ልማዳቸው ሕዝቡን ለመለወጥ በመምከራቸው ብዙዎች እየተታለሉ ወደ ትምህርታቸው ተስበዋል። ሌሎች ደግሞ በሐዋርያው ተግሣፅ በመደናገጥ ሐዘናቸው ከልክ ያለፈ ሆኖአል።

ቅዱስ ጳውሎስ ሁለተኛዋን መልእክት የላከላቸው ንስሐ ገብተው በመመለሳቸው ለማመስገን የተደናገጡትን ደግሞ ለማረጋጋት ከሐሰት መምህራንም እንዲጠበቁ ለማድረግ ነው።[107] መልእክቲቱ በ55 ዓ.ም አካባቢ ተጽፋ በቲቶና በሉቃስ እጅ ተላከች።

## 3. ወደ ገላትያ ሰዎች

ገላትያ በታናሿ እስያ ትገኝ የነበረች አውራጃ ናት። ዛሬ ቱርክ በተባለው ሀገር ውስጥ ትገኛለች። በአውራጃው ውስጥ ጵስድያ፣ አንጾኪያ፣ ኢቆንዮን፣ ልስጥራንና ደርቤን የተባሉ ከተሞች ይገኛሉ። አውራጃዋ በመሥራቅ ከጳንጦንስና ከቀጰዶቅያ፣ በምዕራብ ከፍርግያ፣ በሰሜን ከቢታንያ፣ በደቡብ ኮሊቃእንያ ትዋሰናለች።[108] ጉዋል የተባሉ ሕዝቦች ይኖሩባት ስለነበር ገላትያ ተብላለች።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያውን ሐዋርያዊ ጉዞ ወደ አሕዛብ ሀገር ባደረገ ጊዜ በ46 ዓ.ም ገላትያን ጎብኝቷት ነበር። በ54 ዓ.ም ሁለተኛው ጉዞው በፍርግያ አልፎ ገላትያ በመግባት በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ አስትምሮዋቸው ሄዶአል።

107 ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 148–158

108 ዝኒ ከማሁ ገጽ 159።

ነገር ግን እርሱ የመጀመሪያ ጉዞውን ፈጽሞ ከተመለሰ በኋላ የአይሁድ መምህራን ወደ ገላትያ ገብተው ካልተገረዛችሁና የአይሁድን ወግ ካልጠበቃችሁ አትድኑም እያሉ አወኩዋቸው። ይህ አልበቃቸው ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን:-

- እንደሌሎቹ ሐዋርያት ጌታን አላየም
- ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት እኩል አይቆጠርም
- ከሐዋርያት እንጂ ከጌታ ስላልተማረ ክብሩ ያነሰ ነው
- እርሱ ተገርዞ እናንተን ጽድቅ እንዳታገኙ አትገረዙ እያለ ያታልላችኋል።
- ሐዋርያት ከአይሁድ ተፋቅረው ሕገ ኦሪትን ጠብቀው ሥርዓተ አይሁድን አክብረው በኢየሩሳሌም እየኖሩ እርሱ ግን እናንተን አላዋቂ አድርጎ የሐሰት ትምህርት ያስተምራችኋል።

እያሉ ክህደትና ጥርጥር ስለነዙባቸው ለነዚህ ሐሳውያን መምህራን መልስ፣ ለእምነታቸውም ማጽኛ ይሆናቸው ዘንድ በሶርያ አንጾኪያ እያለ ጽፎ በ48 ዓ.ም በቲቶ እጅ ላከላቸው። ይህች መልእክቱ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የመጀመሪያዋ መሆንዋ ይነገራል። የገላትያ መልእክት ‹የነፃነት መልእክት› በመባል ትጠራለች። ምክንያቱም ክርስቲያኖች በጌታችን ሞትና ትንሣኤ ያገኘነውን ጸጋና ክብር፤ ከኃጢአት ባርነት እንዴት ነፃ እንደወጣንም የምትናገር በመሆንዋ ነው።

## 4. ወደ ኤፌሶን ሰዎች

በታናሺ እስያ በምዕራብ በኩል በከይስተር ወንዝ አጠገብ የተሠራች የልድያ የወደብ ከተማ ነበረች። ከተማዋ በንግድ ማዕከልነትዋና በአርጤምስ (ቤተ ጣዖቷ) የታወቀች ናት። የፋርስ ግዛት ሆና ስትኖር ታላቁ እስክንድር፣ ንጉሠ ፋርስ ዳርዮስን ድል አድርጎ ከተማዋን የግሪክ ግዛት አደረጋት።

ከጌታ ልደት በፊት 190 ዓመት አስቀድሞ ሮማውያን አንጥርኩስ የተባለውን ንጉር ድል አድርገው ለጴርጋሞን ንጉሥ ግዛቱን ደረቡለት። ከእርሱ ሞት በኋላ ግን የሮማ ግዛት ሆነች። አይሁድ በስደትና በንግድ ሄደው ምኩራብ ሠርተው ይኖሩባት ነበር።



በ46 ዓ.ም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ ጉዞው ከአቂላና ጵርስቅላ ጋር ከቆሮንቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ጥቂት ወራት በኤፌሶን ቆይቶ ነበር። በሁለተኛው ጉዞው በ50 ዓ.ም በኤፌሶን ከተማ ሁለት ዓመት ከሦስት ወር አስተምሯል። በኋላም የአርጤምስን ምሥል ከሚሠራው ከአንጥረኛው ከድሜጥሮስ ጋር በተነሣው ጭቅጭቅ ምክንያት ከተማዋን ትቶ በመውጣት ወደ መቄዶንያ ሲጓዝ ጢሞቴዎስን ሊቀጳጳስ አድርጎ ሾመላቸው።

በ58 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ተይዞ ወደ ሮሜ በመሄድ ፀቁም እሥር በነበረ ጊዜ የኤፌሶን ሰዎች በእምነት በምግባር መጽናታቸውን በመስማቱ ይህችን መልእክት ላከላቸው። መልእክቲቱን ያደረሰላት ቲኪቆስ የተባለው ደቀ መዝሙሩ ነው።

## 5. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

ፊልጵስዩስ የመቄዶንያ ከተማ ናት። የተቆረቆረችው በሰሜን በኩል ከባሕር ጠረፍ 10 ምዕራፍ ርቀት ላይ ነው። በጥንት ዘመን አሌኒደስ ትባል ነበር። በኋላ ግን የመቄዶንያው ንጉሥ ፊልጶስ 2ኛ ግዛቷን አስፍቶ በስሙ ሰየማት።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው ጉዞው አስተምሮባታል። በ50 ዓ.ም ቲቶን ወደ ቆሮንቶስ በላከውም ጊዜ እስኪመለስለት ድረስ በከተማ ቆይቶ ነበር።

በ51 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘው በፊልጵስዩስ አልፎ በጢሮአዳ በኩል ስለነበር እግረ መንገዱን አስተምሮባታል።

በሮም በመጀመሪያ እሥራቱ በ58 ዓ.ም የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች በአፍሮዲጡ እጅ ስጦታን ላኩለት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመከራው የማይዘነጉት፣ የማይበረግጉ ልጆችን ስላገኘ ተደስቶባቸዋል። ስለዚህም መልእክቲቱ በደስታ የተሞላች ናት። ደግሞ ደጋግሞ ‹ደስ ይበላችሁ› ይላቸዋል።

እርሱ መታሠሩን የሰሙ ቢጽ ሐሳውያን እኛም መምህራን ብለው በፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ላይ ችግር ፈጥረውባቸው ነበር። ለእነዚህ ትምህርት መልስ ሰጥቷል። በተጨማሪ ደግሞ በከተማዋ የነበሩት አይሁድ እኛ የአብርሃም ዘር ነን እያሉ በአሕዛብ ላይ ስለተመኩባቸው ‹እኔ እኮ የብንያም ዘር ነኝ› እያለ መልስ አሳጣቸው። በፊልጵ 2፥24

ላይ በቶሎ እንደሚመጣ ስለጻፈላቸው የመፈታቱን ነገር ሰምቶ ነበረ። መልእክቲቱን የጻፈው በመፈታቱ ዋዜማ በ60 ዓ.ም አካባቢ ሲሆን ያደረሰለት አፍሮዲጡ የተባለው ደቀ መዝሙር ነው።

## 6. ወደ ቈላስይስ ሰዎች

ቈላስይስ በታናሿ እስያ ውስጥ በፍርግያ በስተደቡብ በሊኮስ ወንዝ አጠገብ የተቆረቆረች የፍርግያ ዋና ከተማ ናት። ከምዕራቡ ዓለም ወደ ምሥራቅ በሚወስደው መንገድ ዳር ስለምትገኝ ዋና የንግድ ማዕከል ስትሆን በተለይ በበግ ፀጉር ምርቷ የታወቀች ነበረች።

ወደዚህች ከተማ ገብቶ ወንጌልን በቅድሚያ የሰበከው ኤጳፍራስ የተባለው የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ነው። ቆላ.1÷7። ቈላስይስ የፊልሞናና የአክርጳስ ሀገር በመሆንዋ እነርሱም ወንጌልን አስተምረውባታል። በፊልሞና ርስት ላይም ቤተክርስቲያን ተሠርታ ነበር። ፊል.2

በመጀመሪያ እሥራቱ በሮሜ እያለ እነ ኤጳፍራስ ሊጠይቁት በመጡ ጊዜ ቢጽሐሳውያን የፍልስፍና መርዛቸውን እየረጩ መሆናቸውን ነገሩት። በኋላ የመጣው የፊልሞና አገልጋይ አናሲሞስም የቆላስይስን ሰዎች የኑሮ ሁኔታ ነግሮት ነበር። በዚህም የተነሣ:-

1. ለግሪክና ለኤፌሶን ፈላስፎች መልስ የሚሆን የእግዚአብሔርን ማንነት፣ የጌታችንን አዳኝነት በመግለጥ፣
2. ስለማኀበራዊ ኑሮአቸውም የባልና የሚስትን፣ የመንፈሳዊ ሰው ጠባያትን እየዘረዘረ ጻፈላቸው።

መልእክቲቱ በ58 ዓ.ም አካባቢ ተጽፋ በቲኪቆስና አናሲምስ እጅ ተላከች።

## 7. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

ቀድሞ የመቄዶንያ ዋና ወደብ ነበረች። ዛሬ ግን በግሪክ ሥር ናት። ስሟ ቀድሞ ቴርማ ይባል ነበር። ትርጕሙም ፍል ውኃ ማለት ነው። ይህም ስም በአጠገብዋ ከነበረው የፍል ውኃ የተወሰደ ነበር። በኋላ ግን ከሳንደር የተባለ ገዥ የታላቁን እስክንድር እኅት ሰሎኒቃን ስላገባ ከተማዋን በሚስቱ ሰየማት።



ከአውሮፓ ወደ እስያ በሚያልፈው ዋና መስመር ላይ ስለምትገኝ ከተማዋ ዋና የንግድ ማዕከል ነበረች። በ50 ዓ.ም ቅዱስ ጳውሎስ ሲላስንና ጢሞቴዎስን አስከትሎ በመምጣት ለ3 ሳምንት ያህል አስተምሮባት ነበር። ነገር ግን በምኵራብ ሲያስተምር አሪታችንን ሊያሳልፍብን ነው በሚል ፍርሃት ተነሣሥተው አይሁድ ስለተቃወሙት ከተማዋን ለቆ ወደ ቤርያ አመራ። የቤርያ አይሁድ ግን የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት በትክክል ይማሩ ነበርና የተሰሎንቄ አይሁድ ዜናቸውን በሰሙ ጊዜ እጅግ ስለተበሳጩ ወደ ቤርያ ሄደው በዚያም ቅዱስ ጳውሎስን ተቃወሙት። በዚህም የተነሣ ምእመናን ወደ አቴና ላኩት። ፀአቴና በኩል አልፎ ቆሮንቶስ ሲገባ ከሲላስና ጢሞቴዎስ ጋር ተገናኘ።

የመጀመሪያይቱ መልእክት:- ሲላስና ጢሞቴዎስ በቆሮንቶስ ቅዱስ ጳውሎስን ሲያገኙት ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች መንፈሳዊ ችግር አወሩለት።

- እርስ በርሳቸው የተፋቀሩ እየመሰላቸው ሚስት ያለው ለሌላው ሰጠው።
- ያለን ይበቃናል እያሉ ሥራ መሥራት አቆሙ
- አይሁድ ደግሞ መከራ ስላበዙባቸውና የገዛ ወጋቸውን ስለሚኑባቸው ጽድቅ በዚህ የሚገኝ ከሆነማ እያሉ በክርስትና ሕይወታቸው ተስፋ የቆረጡ ነበሩ።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን የተሰሎንቄ ሰዎች ችግር በሰማ ጊዜ አስቀድመው በያዙት እምነት ይጸኑ ዘንድ ትክክለኛውንም ትምህርተ ክርስትና ያውቁ ዘንድ ይህችን መልእክት በ50 ዓ.ም አካባቢ ጽፎ በስልዋኖስ (በዕብራይስጥ ሲላስ ይባላል) እና በጢሞቴዎስ እጅ ላከላቸው።

ሁለተኛይቱ መልእክት:- ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ክርስቲያኖች የላካቸው ጢሞቴዎስና ሲላስ መልእክቲቱን አድርሰው ሲመለሱ ስለ ዳግም ምፅዓት በመጀመሪያዋ መልእክቱ የጻፈላቸውን ተመልክተው ‹የማንሞተው እኛ› የሚል ቃል ስለነበረው ‹ዳግም ምፅዓት በቅዱስ ጳውሎስ ዘመን ይደረጋል› በማለት ሕዝቡን ያሸበሩ መናፍቃን ፀመነሣታቸው የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በጥርጥርና

በፍርሃት መዋጣቸውን ነገሩት። በዚህም የተነሣ እጅግ በማዘኑ በ51 ዓ.ም ጽፎ በፊተኞቹ መልእክተኞች እጅ ይህችን ሁለተኛ መልእክት ላከላቸው።

## 8. ወደ ጢሞቴዎስ

*የመጀመሪያይቱ መልእክት*:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የኤፌሶን ሊቀጳጳስ አድርጎ ሾሞት ነበር። ነገር ግን የሥርዓተ ኖላዊን (ሥርዓተ ክህነት) ነገር የሚያስተምርበት ጊዜ አላገኘም። አሁን ግን የሁለት ዓመቱን የቁም እሥር ጨርሶ ከሮም በመውጣቱ በ60 ዓ.ም አካባቢ በሎዶቅያ ጥቂት የዕረፍት ጊዜ በማግኘቱ ለልጁ ለጢሞቴዎስ ስለ ሊቀጵጵስናው ሥራ ጻፈለት። ይህች የመጀመሪያዋ መልእክቱ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ሥርዓተ ኖሎት ከጻፋቸው መካከል የመጀመሪያይቱ ናት። መልእክቲቱ ሁለት ክፍል ሲኖራት የመጀመሪያው ስለ ሥርዓተ ኖሎት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በኤፌሶን ከተማ እና በአካባቢዋ ተስፋፍቶ ለነበረው የግኖስቲኮች ፍልስፍና የሰጠውን ክርስቲያናዊ ምላሽ የያዘ ነው። መልእክቲቱ በ60 ዓ.ም አካባቢ ተጽፋ በቲቶ እጅ ለጢሞቴዎስ ተላከች።

*ሁለተኛይቱ መልእክት*:- በሁለተኛው እሥራቱ በሮም ወኅኒ ቤት እያለ የጻፋት የመሰናበቻ መልእክቱ ናት። አሁን በዕድሜ ገፍቷል፤ የ74 ዓመት ሽማግሌ ነው። ከአንድ ዓመት በላይ በጨለማ እሥር ቤት በመኖሩ ዓይኖቹ ደክመዋል። ጊዜ ሞቱም እንደደረሰ ታውቆታል። 2ጢሞ.4፥6–8። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ፤ ጢሞቴዎስ በኤፌሶን እየተዘዋዋረ ሲያስተምር ግማሹ አምና እየካደ፣ የቀረው በፍልስፍና እየተራቀቀ ሌላው በአምልኮ ጣዖት እየተወሰደ ቢያስቸግረው እየተዘዋወረ መስበኩን አቁሞ በረሃ ገብቶ መጸለይን መረጠ።[109]

ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን እንደሰማ በደረሰበት ፈተና ያጽናናው ዘንድ እንዲሁም የመጨረሻ ምክሩን ያበረክትለት ዘንድ፤ በኑሮውም ሁሉ ያገኘውን መንፈሳዊ ጥበብ ያወርሰው ዘንድ ይህችን መልእክት በ66 ዓ.ም ጽፎ በአንክርሎስ እጅ ላከለት።

---

109 የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ትርጓሜ፤ ወደ ጢሞቴዎስ ሁለተኛይቱ፤ መቅድመ መልእክት



ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህችን መልእክት ከጻፈ በኋላ የቆየው አንድ ዓመት ከሦስት ወር ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ በሰማዕትነት ዐርፏል።

## 9. ወደ ቲቶ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቲቶን የቀርጤስ ሊቀ ጳጳስ አድርጎ ሾሞት ነበር። ቀርጤስ በሜዲትራንያን ባሕር የምትገኝ ደሴት ናት። በውስጧም ብዙ አይሁድ ይኖሩባት ነበር። ከእነዚህም መካከል ለበዓለ ሃምሳ ወጥተው በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት አምነው የተጠመቁም ነበሩ። የሐዋ.2፥11። እነዚህ ክርስቲያኖች ወደ ደሴቷ ሲመለሱ ማኅበረ ክርስቲያን መሥርተው ነበር።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ እሥራቱ ወደ ሮሜ በመርከብ ሲወሰድ በደሴቷ ቢያርፍም (የሐዋ.27፥12) በዘበኛ ይጠበቅ ስለነበር ሊያስተምራቸው አልቻለም። ከሁለት ዓመቱ የቁም እሥር ሲለቀቅ ግን ወደ ደሴቷ ገብቶ አስተምሯቸዋል።

ከቀርጤስ ወደ ኤፌሶን ጢሮአዳና መቄዶንያ ቆይቶም ወደ ድልማጥያና እልዋሪቆ በመግባት ካስተማረ በኋላ በመጨረሻ መቄዶንያ አጠገብ ወዳለው ወደ ኒቆጵልዮን ገብቶ ጥቂት ዕረፍትን ባደረገ ጊዜ ለቀርጤሱ ሊቀ ጳጳስ ለቲቶ ሥርዓተ ኖሎትን በተመለከተ ይህችን መልእክት ጻፈለት።

መልእክቲቱ የተጻፈችው በ63 ዓ.ም አካባቢ ሲሆን ለቲቶ ያደረሳትም አርጣ የተባለው ደቀ መዝሙሩ ነው።

## 10. ወደ ፊልሞና

የፊልሞና ሀገሩ ቆላስይስ ነው። ወደ ኤፌሶን ለሥራ በሄደ ጊዜ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በመገናኘቱ ከእነቤተሰቡ አምኖ ተጠምቋል። ከኤፌሶን ወደ ቆላስይስ ዳግም ተመልሶ መኖር በጀመረ ጊዜ አናሲሞስ የተባለ አገልጋዩ የሚጠብቃቸው የፊልሞና ከብቶች ስለጠፋበት አገሩን ጥሎ ወደ ሮሜ ኰበለለ።

አናሲሞስ ሮሜ ሲገባ ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ እሥራቱ ላይ ነበር። አናሲሞስም የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ሰምቶ አምኖ ተጠመቀ። የደረሰበትንም ለቅዱስ ጳውሎስ አጫወተው። እርሱም

ይህችን የማስታረቂያ መልእክት ለፊልሞናና ለሚስቱ ለአፍብያ እንዲሁም ለልጁ ለአክርጳስ ጽፎ በራሱ በአናሲሞስ እጅ ላከላቸው። የተጻፈችው ከመጀመሪያ እሥራቱ ሊወጣ አካባቢ በ60 ዓ.ም ነው።

## 11. ወደ ዕብራውያን

በዚህች መልእክት ላይ እንደ ሌሎች ሁሉ የጸሐፊው ስም ባለመገለጡ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሊታውንቱ የተለያየ ሃሳብ ይዘዋል። የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ቀሌምንጦስ የቅዱስ ሉቃስ ነው ይላል። ነገር ግን የቅዱስ ሉቃስ ሥዕላዊ አገላለጥ በመልእክቲቱ ላይ እንደ ወንጌሉና እንደ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ስለማይታይ ተቀባይነት አላገኘም። የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግን የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መሆኑን አስረድቷል።[110]

ከጥንት ዘመን ጀምሮ እያሌ የቤተ ክርስቲያን አበው በየመጻሕፍቶቻቸው የዕብራውያንን መልእክት ሲጠቅሱ የቅዱስ ጳውሎስ መሆኑን ገልጠዋል። ለዚህም ዋነኛ ማስረጃ አድርገው ያቀረቡት በመልእክቱ መጨረሻ የደቀ መዝሙሩ የጢሞቴዎስ ስም መጠቀሱን ነው። ዕብ.13፥23።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህችን መልእክት የላከበት ዋናው ምክንያት በኢየሩሳሌም የነበሩ ከይሁዲነት የተመለሱ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም በነበሩ አይሁድ ይደርስባቸው በነበረው መከራ ተመርረው ወደ አይሁድ ሥርዓትና ወግ ዘወር ማለት በመጀመራቸው ነው።

የኢየሩሳሌም አይሁድ የሮማውያን ጭቆና ስላንገፈገፋቸው ዓመፅ ጀመሩ። በዚህ ዓመፃቸው ክርስቲያኖች ስላልተሳተፉላቸው ዘወትር ይወቅሷቸው ነበር። አንዳንድ ክርስቲያኖችም የሀገር ነገር ሆኖባቸው ከአይሁድ ጋር ለመተባበር ተነሡ። አይሁድ ግን በእኛ ወግና ሥርዓት ካልተመራችሁ አንድ ለመሆን አንችልም አሏቸው። በዚህ የተነሣ ክርስትናቸውን ወደ ጐን ጥለው አይሁድን በሁሉም ነገር መምሰል ጀመሩ። መልእክቲቱ ይህን ችግር ለመፍታት የተጻፈች ናት።

---

110 ዜና ሐዋርያት፣ ገጽ 250



ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በላከው መልእክቱ ስሙን ያልጻፈበት ምክንያት አለው።

1ኛ. አስቀድሞ የእነርሱ ተማሪና ለወጋቸውም ቀናተኛ ስለነበረ ስሙን ቢያዩ ኖሮ በበቀል ስሜት ስለማይቀበሉት፣

2ኛ. ዘመኑ አይሁድ በሮማውያን ላይ ለማመፅ የተዘጋጁበት ጊዜ በመሆኑ በሮም መንግሥት ሥር ታሥሮ እያለ በስሙ ደብዳቤ ቢጽፍ ኖሮ ሮማውያን ምክንያት አግኝተው እሥራቱን ወደ ፖለቲካ እንዳያዞሩበት፣

3ኛ. ቀድሞውኑ ያሳሠሩት እነርሱ ናቸውና ገና ስሙን ሲያዩ አሪት አለፈች ሊለን ነው ብለው ከማንበብ እንዳይከለከሉ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ብሉይን ከሐዲስ አስማምቶ የሚያውቅ ነበር። የብሉይ ኪዳኑን ምሳሌ (ሙሴ፣ መልከጼዴቅ፣ አብርሃም፣ ከነዓን፣ ደብተራ ኦሪት፣ መሥዋዕተ ኦሪት፣ እሥራኤል ዘሥጋ) እያነሣ በሐዲስ ኪዳን ያላቸውን ትርጓሜ አሳይቷቸዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መምጣት ሱባዔ የተቆጠረለት ትንቢት የተነገረለት እንጂ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ አለመሆኑን አስረድቷቸዋል።

በመጀመሪያዋ እሥራቱ በሮሜ እያለ በ60 ዓ.ም አካባቢ ጽፎ በጢሞቴዎስ እጅ ልኮላቸዋል።

### ማጠቃለያ — ስለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

ዕውቀትን ከትህትና ደርቦ የያዘ ነበረ:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም በሚገኘው በታላቁ የአይሁድ ትምህርት ቤት በሊቁ በገማልያል እግር ሥር ብሉይ ኪዳንን የተማረ ነበር። በኋላም ትምህርተ ክርስትናን ከሐዋርያት አግኝቷል። ይህን ሁሉ ዕውቀት ይዞ ሁል ጊዜ ኑሮው የትህትና ነበር። እኔ ጭንጋፍ ነኝ እስከማለትም ደርሶ ነበር። (1ቆሮ.15፥8)

ትጉህና ታታሪ ነበረ:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለ42 ዓመታት ያህል በሐዋርያነት አገልግሉአል። እስከ እስጳኝ ድረስ ሄዶም አስተምሯል። በባሕር እና በእግር፣ ተመላልሷል። በ12ቱም ሐዋርያት ሀገረ ስብከት እየገባ ወንድሞቹን አግዞአቸዋል።

ትዕግሥተኛ ነበረ:- ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው ቀዳግዊ መልእክቱ እንደገለጠው (11፥25–33) ብዙ ፈተናዎችን አልፏል። ሁለት ጊዜ ታሥሯል ተደብድቧል፣ በረሃብ ተገርፏል ይህ ሁሉ ቢሆንም በኑሮው ደስተኛ ነበር። በሮሜ ታሥሮ እያለ ለፊልጵስዩስ ሰዎች መልእክት ሲጽፍ በደስታ የተሞላ ነበረ። በመጀመሪያ ጉዞው ያልተቀበሉትን ከተሞች በሁለተኛው አልያም በሦስተኛ ጉዞው ጎበኛቸው እንጂ እምቢ አሉኝ ብሎ ተስፋ አልቆረጠም።

ጥበበኛ ነበረ:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን የቤተ ክርስቲያን አበው ‹መዶሻ› ይሉታል። መዶሻ ግዕድናቱን ቀጥቅጦ አንድ ያደርጋቸዋል፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በትምህርቱ ሕዝብንና አሕዛብን አንድ ያደረገ ሐዋርያ ነው። በ50 ዓ.ም አካባቢ ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ ቲቶንና በርናባስን አስከትሎ ነበር። ቲቶን ከአሕዛብ ወገን በርናባስን ደግሞ ከአይሁድ።

ቅዱስ ጳውሎስ ሰውን እንዴት መቅረብ እንደሚቻል የሚያውቅ ሰው ነበረ:- ከተራ ሰዎች እስከ ነገሥታት ቤተሰቦች በፍቅር እየሳበ ክርስቲያን አድርጓቸዋል። በመልእክቱ መጨረሻ የቤተክርስቲያንን ልጆች በስማቸው እየጠራ ሰላምታ ማቅረብ የዘወትር ልማዱ ነበረ። ይህም ሁሉም በልቡ እንደታተመ ያውቁ ዘንድ ነው።

ጸሐፊ ነበር:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቃል ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል ነውና ያስተማራቸውን ክርስቲያኖች እንዲሁ አይተዋቸውም። ለሃይማኖታቸው ማጽኛ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው መመሪያ የሚሆኑ መልእክታትን ጽፎላቸዋል። አብዛኛዎቹ መልእክታት በእሥር ቤት ውስጥ ነው። ለመጓዝ የሚያስችለው



አመቺ ጊዜ ሲያገኝ በአካል፣ በቃል ያስተምራቸዋል። ሲታሠር መንቀሳቀስ ሲከለከል ደግሞ ጣቶቹ ብዕር ይጨብጣሉ። መልእክቶቹ በየሀገረ ስብከቱ ይላካሉ።

ሥራ ወዳድ ነበር:- ቅዱስ ጳውሎስ ሌት ተቀን ለስብከተ ወንጌል ቢባክንም ለምእመናን እንዳይከብድባቸው ድንኳን እየሰፋ የዕለት ጉርሱን የዓመት ልብሱን ያገኝ ነበር። የሐዋ.18፥3፣4። ለዚህም ነው ‹ሊሠራ የማይወድ ቢኖር አይብላ› እያለ ያስተምር የነበረው። 2ተሰ.3፥10።

የምሥራቅ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲተላለፍ የኖረውን ትውፊት በማሰባሰብ ስለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተክለ ሰውነት እንዲህ ይላሉ።

ጭንቅላቱ ትልቅ ሲሆን ራሰ በራ ነበር። የሁለቱም ቅንድቦቹ ጠጉር የተጋጠመ፣ ዓይኖቹ ሰማያዊ ቀለም ያላቸው ሲሆን ዘወትር ብሩሃን ነበሩ። አፍንጫው ትልቅና ቀጥ ብሎ የወረደ ጽሕሙና ረዘም ረጃጅም ናቸው። አንገቱ አጠር ያለ ሆኖ ትከሻው ክብና ጉባባ እግሮቹ ደግሞ ከጉልበቱ ላይ የተቃረቡ ናቸው። ቁመቱ አጠር ያለ ደንዳና ሰው (ከድንክ የረዘመ) እንደነበር ይነገርለታል።

## ምዕራፍ ሦስት

# ሌሎች በአንደኛው መ/ክ/ዘ የተነሡ ቅዱሳን

በዚህ ክፍለ ዘመን የወንጌል ፋና በዓለም እንዲበራ ችቦውን ይዘው የዘመቱት ሐዋርያት ብቻ ሳይሆን ከእነርሱ ቀጥለው የሚጠሩት አርድእት እና ቅዱሳት አንስት እንዲሁም የእነርሱን ፈለግ የተከተሉ ሰማዕታት ጭምር ናቸው። ሕይወታቸውን ለቤተክርስቲያን እስከመስጠት ድረስ በኃጢአት ጨልሞ ከነበረው ዓለም ጋር ከተጋደሉት ቅዱሳን መካከል ጥቂቶቹን እነሆ።

## ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ

ቅዱስ ሉቃስ ሀገሩ አንጾኪያ ነው። አስቀድሞ ከ72ቱ አርድእት ወገን የተቈጠረ ሲሆን ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ወደ አንጾኪያ ወርዶ ወንጌልን ሰብኳል ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጋር የተገናኘውም በዚሁ ነው። ቅዱስ ሉቃስ የሕክምና ሙያ የነበረው ሲሆን ያጠናውም ከአቴናና ከእስክንድርያ ሊቃውንት መሆኑ ታውቋል። ከዚህ ሙያው በተጨማሪ የሥነ ሥዕል ችሎታም እንደነበረው ይነገራል። ይህንን ችሎታውንም በወንጌሉና በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ላይ ባለው ሥዕላዊ አገላለጥ ከማንፀባረቁም ሌላ በእጁ የተሣሉ ሥዕሎች በተለያዩ ሀገሮች ይገኛሉ።[111]

ቅዱስ ሉቃስ የድንግልና ሕይወት የነበረው ወንጌላዊ ነው። የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር በመሆን በሰማዕትነት እስካረፈበት ጊዜ ድረስ አገልግሎታል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ67 ዓ.ም በሮማ በሰማዕትነት ሲያርፍ ሉቃስ ወደ ድልማጥያ መጣ። በዚያም

111 የቅዱስ ሉቃስ ሥዕሎች እመቤታችን ልጇን አቅፋ (ምስለ ፍቁር ወልዳ) የሣላቸው ሲሆኑ በኢትዮጵያ በተድባበ ማርያም፣ በደብረ ዘመዱ፣ በዋሸራ፣ በጅበላ ሲገኙ ተመሳሳዩም በስፔን ቅድስት ማርያም ካቴድራል እንደሚገኝ ይነገራል።



በሽምግልና ዘመኑ ወንጌልን በመስበክ ላይ እያለ አይሁድና ካህናተ ጣዖት ተባብረው ትምህርቱን በመቃወም ተነሡበት። መስከረም 20 ቀን 68 ዓ.ም አይሁድና አረማውያን ጉባዔ አድርገው ነገር በመሥራት ለሮም ንጉሥ ከሰሱት። በዚያን ዘመን ኔሮን እብደቱ ያየለበት ጊዜ በመሆኑ የቅዱስ ሉቃስን ክርሚ ማምለጥና ወደ ድልማጥያ መምጣት ሲሰማ 200 ወታደሮችን ላከበት ቅዱስ ሉቃስም የሰዎችን መምጣት በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ያስተምራቸው የነበሩትን ምእመናን ወደየቤታቸው ላከና በድልማጥያ አጠገብ ወደሚገኘው ባሕር ተጠጋ።

በባሕሩ አጠገብ አንድ ዓሣ አስጋሪ ቆሟል። ቅዱስ ሉቃስ ወደ ዓሣ አስጋሪው ቀረበና ጨዋታ ጀመሩ። ቀስ በቀስም ወንጌል ይሰብክለት ጀመር። ዓሣ አስጋሪውም ቅዱስ ሉቃስ የሚነግረውን ሁሉ ሥራውን አቁሞ በደስታ ያዳምጠው ነበር። በመጨረሻ ‹እንካ እነዚህ የሕይወትን መንገድ ይመሩሃል› አለና የያዛቸውን መጻሕፍት ሁሉ ሰጠው። ያም ዓሣ አስጋሪ እጅግ ተደስቶ ዕቃ በሚያስቅምጥበት ቦታ በክብር አኖራቸው።

ቅዱስ ሉቃስ መጽሐፉን ሰጥቶት ዘወር ሲል የኔሮን ወታደሮች ተረባረቡና ያዙት። ከዚያም ወደሮም ተወሰደና በኔሮን ፍርድ ቤት ቀረበ። ጥቅምት 22 ቀን አንገቱን ተሠይፎ በአሸዋ በተሞላ ከረጢት አስገብተው በተወለደ በ84 ዓመቱ ወደ ባሕር ወረወሩት። ቅዱሳት መጻሕፍቱን ግን ያ ዓሣ አስጋሪ ለዚህ ትውልድ አትርፏቸዋል።[112]

## የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ በዓይኑ የተመለከተውን ከሐዋርያትም የሰማውን ጠንቅቆ በማሰባሰብ 24 ምዕራፍ፣ 1149 ቁጥሮች የያዘ ወንጌል አበርክቶልናል። ወንጌሉን የጻፈው ከ58–60 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ቅዱስ ጳውሎስ በእሥር ላይ እያለ ባገኘው ዕረፍት መሆኑ ይነገራል።[113]

ወንጌሉ የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ሲሆን የተጻፈለትም ቴዎፍሎስ ለተባለ የመቄዶንያ (ግሪክ) ባለሥልጣን ነው። ወንጌሉ ‹የአሕዛብ

112 ገድለ ሐዋርያት፣ ገጽ 119–125፣ ትንሣኤ ቁ.61/75፣ ገጽ 5

113 Elkraza, Vol.1 No 9 (sept.) p.15

ወንጌል› እየተባለ ይጠራል፤ የተጻፈው ለእነርሱ ስለሆነ ነው። በዚህም የተነሣ:-

- እንደ አሕዛብ ልማድ ትረካን አብዝቶላቸዋል
- አሕዛብ ሱባዔ የመቁጠር ትንቢት የመጠበቅ ልማድ ስለሌላቸው ከነቢያት ትንቢት በብዛት አልጠቀሰም።
- የጻፈው በግሪክ ቋንቋ ስለሆነ የዕብራይስጥን ቃላት ተርጕሟቸዋል።
- አሕዛብ ከአማልክቶቻቸው መኻል የፍቅር አምላክ የሚሏቸው አሉ።

ለምሳሌ:- ለግሪኮች ቬነስ የፍቅር አምላካቸው ናት። ከዚህ ውጪ ያሉትን ቁጡ፤ መዓተኛ፤ ቶሎ የሚፈርዱ፤ ቀንበር የሚያበዙ አድርገው ስለሚያምኑ እጅግ በጣም ይፈሩአቸዋል። ወንጌላዊው ሉቃስ ይህንን የአረማውያንን ልማድ ስለሚያውቅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር በልዩ ልዩ ሁኔታ ገልጦላቸዋል። ለምሳሌ:- ለጠፋው ልጅ አባቱ ያሳየውን የምሕረት ፍቅር (15፥11–82)፤ ጌታ ለዘማዊቷ ያሳየውን ርኅራኄ (23፥7)

- ከዚህም ሌላ ጌታችን ለድኾችና ለተጠሉት የሚራራ አምላክ መሆኑን በወንጌሉ ገልጧል። ለምሳሌ:- የአልዓዛርና የነዌ ታሪክ (16፥19–31)
- ቅዱስ ሉቃስ በሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ዘንድ ‹ሰባኬ መንፈስ ቅዱስ› ይባላል። (1፥35፤ 12፥12፤ 4፥1፤ 11፥13) ስለመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ደግሞ ደጋግሞ ገልጧል።
- ‹ሰባኬ ጸሎትም› ይባላል። ከሌሎች ወንጌላት በበለጠ ሁኔታ የጌታን ደጋግሞ መጸለይ ጽፏልና።
- ‹ወንጌለ አንስት›ም ይባላል። ስለ እመቤታችን፤ ስለ ኤልሳቤጥ። 1፥3–56 ስለማርያም እንተ እፍረት 7፥38–50 እና ስለ የናይኗ ሴት 7፥11–17 ጽፏልና።

የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል በአገላለጡ ከሌሎች ይለያል። አቀራረቡ ሥዕላዊ መግለጫን የተከተለ ነው። ሠዓሊነቱ በመጻሕፍቱም ላይ



ተንፀባርቋል። እንዲሁም በሌሎች ወንጌላት የሌሉ ታሪኮችን አስፍሯል።

1. የዘካርያስና ኤልሳቤጥ፤ 1፥5–25
2. የእመቤታችን ብሥራት እና የጌታችንን መወለድ 1፥26–56
3. የጠፋው በግ፤ 15፥3–7
4. የጠፋው ድሪም፤ 15፥8–10
5. የጠፋው ልጅ፤ 15፥11–32
6. አልዓዛርና ነዌ፤ 16፥19–31
7. ርኅሩኁ ሳምራዊ፤ 10፥29–37
8. የኒቆዲሞስና (አንዳንድ ሊቃውንት ከቀለዮጳ ጋር የነበረው ሰው ሉቃስ ነው ብለው ይተረጕማሉ። በቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ግን ኒቆዲሞስ መሆኑ ተመዝግቧል። ግብረ ሕማማት፤ ገጽ 451) የቀለዮጳ፤ 24፥13–35። እነዚህ ታሪኩች በሉቃስ ወንጌል ብቻ የሚገኙ ናቸው።

## የሐዋርያት ሥራ

የሐዋርያት ሥራን የጻፈው ቅዱስ ሉቃስ ነው። ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ ከ1–34 ዓ.ም ያለውን የክርስትና ታሪክ ካሰፈረ በኋላ ቀጣዩንና ከ34–58 ዓ.ም ያለውን ደግሞ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ላይ ጽፏል።

ከምዕራፍ 1–8 ያለው የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በኢየሩሳሌም የሚያሳይ ሲሆን ከምዕራፍ 9–12 ያለው ታሪክ ደግሞ በእስጢፋኖስ ሰማዕትነት በተነሣው ስደት የተበተኑት የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ልጆች በአካባቢው ያደረጉትን ሐዋርያዊ ጉዞ የሚያሳይ ነው። ከምዕራፍ 13 ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ደግሞ የቅዱስ ጳውሎስን ጉዞዎች ተከትሎ የጻፈውና ክርስትና በታናሿ እስያና በአውሮፓ እንዴት እንደተሰበከ የሚያሳየው ክፍል ነው።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው የሮም እሥራቱ በቁም እሥር ላይ ሆኖ ወንጌልን እንዲሰብክ

ተፈቅዶለት በነበረ ሰዓት በሮም ከሚኖሩ አይሁድ ጋር በ58 ዓ.ም ስለሃይማኖት ያደረገውን ውይይት ተርኮ ያጠናቅቃል።

ወንጌላዊው ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን የጻፈው በ58 (በ59 ዓ.ም) ነው። ምክንያቱም ከዚህ ዓመተ ምሕረት በኋላ የተከናወኑትን ለምሳሌ በ60 ዓ.ም የቅዱስ ጳውሎስን መፈታት ዘግይቶም በ64 ዓ.ም የደረሰውን የሮማ መቃጠልና የአይሁድን ዓመፅ በመጽሐፉ ስላልገለጠው ነው።

ቅዱስ ሉቃስ ሐዋርያው ጳውሎስን ተከትሎ ታሪኩን ሲያሰባስብ ከኖረ በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሚ ሲታሠር ዕረፍት በማግኘቱ አጠናቅሮ በመጽሐፍ መልክ በማዘጋጀት ለቴዎፍሎስ ልኮለታል።

ሉቃስ ዘላሕም:- አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ቅዱስ ሉቃስ ለምን በላም እንደሚመሰል ሲናገር፤ ‹የመድኃኒታችንን መሥዋዕትነት ሐዲስዋ እምቦሳ በወለደችው በንጹሕ ላም ፍሪዳ መስሎ ይናገራልና›[114] ይለዋል። እንዲሁም በከብቶች በረት መወለዱን ስለሚናገርና ታሪኩም የላም ወተት ለሕፃን ልጅ ተላል ምግብ እንደሆነ ሁሉ ለአዲስ አማኝ ተለል ብሉ የተረበ ስለሆነ በላም ተመስሏል።

## ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ

በትውልዱ ዕብራዊ ሲሆን ቤተሰቦቹ ግን ይኖሩ የነበሩት በሰሜን አፍሪካ ሲሬኒካ (ቀሬና) በተባለችውና በዛሬዋ ሊቢያ ምዕራባዊ ጠረፍ በተቆረቆረችው ደግቅ ከተማ ነበር። ነገር ግን የሰሜን አፍሪካ ዘላን ጐሳዎች የሆኑት በርበሮች በየጊዜው በከተማዋ ጥቃት እየሠነዘሩ ሀብት ንብረታቸውን እየዘረፉ ስላስቸገሩዋቸው እናቱ ማርያምና አባቱ አርስጦቡሎስ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ኢየሩሳሌም በመመለስ ቤት ሠርተው ተቀመጡ።

ቅዱስ ማርቆስ ገና በልጅነቱ ኢየሩሳሌም ለመኖር በመታደሉ በዚያን ዘመን ይሰጥ የነበረውን ትምህርት የማግኘት ዕድል

114 ትንሣኤ 61/75፤ ገጽ 5



ገጥሞታል። የላቲን፤ የግሪክና የዕብራይስጥ ቋንቋዎችን አጥምሮ ያውቅ ነበር። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ አውራጃዎች እየተዘዋወረ ሲያስተምር ማርቆስ ገና ሕፃን ነበረ። በምሴተ ሐሙስ ለሐዋርያት ‹ወደ ከተማ ሂዱ በማድጋ ውኃ የተሸከመ ጉብዝም ያገኛችኋልና ተከተሉት› በማለት ፋሲካን ሊያዘጋጁለት የመረጠውን ቤት እንዲያሳያቸው የጠቆማቸው ወጣት ቅዱስ ማርቆስን መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይተረጉማሉ። ማር.14፥13።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቀራንዮ በሚጓዝበት ዕለት ቅዱስ ማርቆስ ዕርቃኑን በነጠላው ሸፍኖ ይከተለው ነበር። ነገር ግን አይሁድ ሊይዙት ባሰቡ ጊዜ ጨርቁን ጎ ኑ ራቁቱን ሸሸ። ማር.13፥50። ይህም በዚያ ጊዜ ገና ልጅ እንደነበር ያመለክታል።

የማርቆስ እናት ማርያም ባውፍልያ ትባላለች። ቤቷን ለክርስቲያኖች መሰብሰቢያነት የሰጠች ደግ ሴት ነበረች። ጌታም የመጀመሪያውን የሐዲስ ኪዳን ቁርባን ለሐዋርያት ያቀረባቸው በርስዋ ቤት የላይኛው ፎቅ ላይ ነበር። በበዓለ ሃምሳም መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደላቸው በርስዋ ቤት ተሰባስበው ሲጸልዩ ነው።

በርናባስ ለቅዱስ ማርቆስ አጎቱ ነው። የቅዱስ ማርቆስ አባት አርስጦቡሎስና በርናባስ በእናት የሚገናኙ ወንድማማቾች ናቸው። የእነርሱን እኅቱ ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስ ስላገባት ቅዱስ ማርቆስ አክስቱን ለመጠየቅ ሲሄድ ከቅዱስ ጴጥሮስ ተዋወቀ።[115]

ሐዋርያት ዓለምን ዕጣ በዕጣ ተከፋፍለው ሲወጡ ቅዱስ ማርቆስ በበርናባስ አቅራቢነት ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በመጀመሪያው ጉዞው በ46 ዓ.ም ለስብከተ ወንጌል ወጥቶ ነበር። ነገር ግን በጵንፍልያ ከተማ እናቴ ናፈቀችኝ ስላለ (የሐዋ.13፥13) በርናባስ ይዞት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። ከዚያ በኋላ የኖረው ከሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ነው።

ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በታናሿ እስያ አድርገው እስከ ሮም ድረስ ሰብከዋል። በመጨረሻ በ60 ዓ.ም ወደ ሰሜን አፍሪካ መጣ። በዓባይ

115 መጽሔት አሚን፤ ገጽ 39

ዶሊታ በኩል አድርጎ በዘመኑ ታዋቂ የንግድ፣ የባሕልና የፖለቲካ ማዕከል ወደ ነበረችው እስክንድርያ ደረሰ። እስክንድርያ የጣዖት አምላኪዎች ከተማ ስለነበረች ቅዱስ ማርቆስ ወንጌልን እንዴት እንደሚሰብክላቸው እያሰበ በከተማዋ ውስጥ ይዘዋወር ጀመር። በመጨረሻ ከመዘዋወሩ ብዛት የተነሣ ያደረገው የጠፍር ጫማ ተበጠሰ። ወዲያው በአጠገቡ ወደ ነበረ አንያኖስ ወደሚባል ጫማ ሰፊ አመራ።

አንያኖስ የቅዱስ ማርቆስን ጫማ ሲሰፋ መስፊያው እጁን ወጋው። በዚህ ጊዜ ‹ኢስታኦስ› ብሎ በዮናናውያን ቋንቋ ጮኸ። ትርጉሙም ‹አንድ አምላክ› ማለት ነው።

ያን ጊዜ ቅዱስ ማርቆስ ጠጋ ብሎ ለመሆኑ ‹አሁን የጠራኸውን አምላክ ታውቀዋለህን?› በማለት ጠየቀው። አንያኖስም ‹ሲሉ እሰማለሁ እንጂ አላውቀውም› ሲል መለሰለት። ቅዱስ ማርቆስም የቆሰለ እጁን በተዓምራት ፈወሰለትና የወንጌልን የምሥራች አሰማው። አንያኖስም ማርቆስን ይዞ ወደ ቤቱ በመውሰድ ቤተሰቡን ያስተምር ዘንድ ጋበዘው። የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያንም በግብፅ ውስጥ በአንያኖስ ቤት ተመሠረተች።

ቅዱስ ማርቆስ በእስክንድርያ ከአስተማረ በኋላ ወደ ትውልድ ሀገሩ ሲረናይካ (ቀሬና) በመሄድ ወንጌልን በመስበክ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አንፆአል።

በ68 ዓ.ም አካባቢ የትንሣኤን በዓል ለማክበር ቅዱስ ማርቆስን የእስክንድርያ ክርስቲያኖች ስለጠሩት በቅድስት ባውክልያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቅዳሴ ላይ እያለ ግብፃውያን አምላክያን ጣዖት ተነሡበት። ያ ዓመት የግብፅ ክርስቲያኖች የትንሣኤ ዕለት ከታወቀው የግብፃውያን ጣዖት ሰራፒየም በዓል ጋር ገጠመ። በዚህ የተነሣ የጣዖቱን በዓል ሊያከብሩ የተሰበሰቡት ጣዖት አምላክያን ቤተ ክርስቲያኑን ሰብረው በመግባት ቅዱስ ማርቆስን ያዙት። ከሠረገላ ጋር በማሠር ቀኑን ሙሉ መንገድ ለመንገድ ሲጐትቱት ዋሉ። ማታ ወደ ወኅኒ ተወረወረ።

በነጋታው እንዲሁ በሠረገላ አሥረው ሲጐትቱት ከዋሉ በኋላ ሚያዝያ 30 ቀን በዚያው ዕለት ዐረፈ። ሥጋውንም ለማቃጠል እንጨት ሰብስበው እሳት ሊያያይዙ ሲሉ ኃይለኛ ዝናብ ዶፉን



አወረደው። በዚህም ጊዜ አረማውያኑ ዝናቡን ሸሽተው ወደየቤታቸው ተበተኑ። የእስክንድርያ ምእመናንም ሥጋውን ደብቀው በመውሰድ በቅድስት ባውክልያ ቤተ ክርስቲያን ዐሳረፉት።[116]

በ820 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የቬኒስ ነጋዴያን ዐፅሙን ሰርቀው በመውሰድ በከተማቸው በሳንማርኮ ቤተ ክርስቲያን አስቀመጡት።[117]

## የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል

ከወንጌላውያን መካከል የመጀመሪያውን ወንጌል የጻፈው ቅዱስ ማርቆስ ነው። ከጥንት ዘመን ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን አበው ቅዱስ ማርቆስ የጻፈው የቅዱስ ጴጥሮስን ወንጌል መሆኑን ተናግረዋል። ከሐዋርያን አበው አንዱ ፓፒያስ እንደገለጠው (140 ዓ.ም) ቅዱስ ማርቆስ የቅዱስ ጴጥሮስን ቃል በመቀበል ወንጌሉን ጽፏል።[118]

የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ከወንጌላት ሁሉ አጭሩ ወንጌል ነው። 16 ምዕራፎችንና 661 ቁጥሮችን ይዟል። ከትረካ ይልቅ ድርጊቶችን አከታትሎ ያስቀምጣቸዋል። ቅዱስ ማቴዎስ በወንጌሉ በምዕራፍ 8፥14–15 ያስቀመጠውን የቅዱስ ጴጥሮስ አማት መፈወስ ታሪክ ቅዱስ ማርቆስ ግን በመጀመሪያው ምዕራፍ ቁጥር 30 ላይ ጽፎታል።

ወንጌሉን የጻፈው ለአረማውያን ያውም ለሮማውያን በመሆኑ ከሌሎች ወንጌላውያን (ቅዱስ ማቴዎስና ቅዱስ ዮሐንስ) የተለየ አገላለጥና አጻጻፍ ተጠቅሟል። የተጻፈበት ቋንቋ ሮማይስጥ ነው። ሮማውያን በዘመናቸው ኃያላን ነን ብለው ይታበዩ ስለነበርና ያለ እኛ ማን አለ? የሚል ኩራት ስለነበራቸው የወንጌሉ አጻጻፍ ከእነርሱ በላይ ኃያል መኖሩን ለመግለጥ ነው። ገና ወንጌሉን ሲጀምር የጌታን ሥልጣን በአጋንንት ላይ (1፥27)፣ በበሽታ ላይ (1፥34) የማስተማር ሥልጣኑን (1፥22) በመግለጥ የጌታችንን ኃያልነት አሳይቷል።

በሮማውያን ባሕል መሠረት አንድ ንጉሥ ሲመጣ አጋፋሪው ከፊቱ በፈረስ ይቀድማል። እርሱም የንጉሡን መምጣት እያወጀ

116 St. Mark and the See of Alexandria, p. 37

117 Dictionary of Saints, p.232

118 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 232

ያልፋል። በዚህ ባሕል መሠረትም ቅዱስ ማርቆስ በወንጌሉ የዮሐንስ መጥምቁን ታሪክ አስቀድሞ ጽፏል።

የወንጌሉ ትምህርት ዋና መልእክቱ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት፤ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ መሆኑን መግለጥ ነውና ሲጀምር ያስተላለፈውን ይህን መልእክት (1፥1) በወንጌሉ ማጠናቀቂያ ላይም በሮማዊው መኰንን ምሥክርነት ደምድሞታል። 15፥39። በወንጌሉም ውስጥ 1፥11፤ 9፥7፤ 14፥61፤ 12፥6፤ 3፥11፤ 5፥7 ደጋግሞ ገልጦታል።

የጻፈው ለአረማውያን በመሆኑ የአራማይክን ቃላትና የዕብራውያንን ባሕል ሊያውቁት ስለማይችሉ ተርጕሞላቸዋል። ለምሳሌ:-

- ቦአኔርጌስ – የነጐድጓድ ልጆች (3፥17)
- ጣቢታ ቁሚ – አንቺ ብላቴና ተነሺ (5፥41)
- ቁርባን – መባዕ (7፥11)
- ኤፍታህ – ተከፈት (7፥34)
- አባ–አባት (14፥36)
- ኤሎሄ፤ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ – አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ (15፥34)
- ጎልጎታ የራስ ቅል (15፥22)
- የአይሁድን ባሕልና የቦታ ስሞች አብራርቶላቸዋል። ለምሳሌም
- የመታጠብን ባሕል (7፥2–4)
- ፋሲካን በሚያርዱበት በቂጣ በዓል መጀመሪያ (በማለት ስለበዓሉ ዘርዝሯል) 14፥12
- በመሸ ጊዜ የሰንበት ዋዜማ የሆነ የማዘጋጀት ቀን ነበረ። የጻፈው ለአይሁድ ቢሆን ኑሮ ‹የማዘጋጀት ቀን› የሚለው ብቻ በቂ ነበር። ምክንያቱም የማዘጋጀት ቀን በሰንበት ዋዜማ መሆኑን ያውቃሉና። ዲናር ግን የሮማ ገንዘብ ስለነበር አልተረጐመውም (6፥37)



- ሰዱቃውያን – ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ። (12፥18) በማለት እምነታቸውን ገልጦታል።
- ሴቲቱም ግሪክ ትውልድዋም ሲሮፊኒቃዊት ነበረች። (7፥26)
- ዮርዳኖስ – ‹ወንዝ› የሚል ቅጽል አስቀምጧል። አይሁድ ቢሆኑ ወንዝነቱን መግለጥ አያስፈልግም ነበር። (1፥5)
- ደብረ ዘይትን ‹በመቅደስ ትይዩ› ብሎ ቦታውን ገልጦታል። (ሮማውያን ስለማያውቁት)
- ቤተ ፋጌንና ቢታንያን – ‹ከደብረ ዘይት አጠገብ ወዳሉት› ብሎ መልክዓ ምድራዊ ገለጣ ጨምሮላቸዋል። (11፥1)
- አንድ መንገድ አላፊም – የእሌክስንድሮስና የሩፎስ አባት (ሩፎስ በሮም የነበረ ሰው ነው። ሮሜ 16፥13)[119]

ቅዱስ ማርቆስ በወንጌሉ የጌታን ሥራ ሲገልጥ ከትህትና ሥራው ጐን ሁል ጊዜ የኃይል ሥራውን አብሮ ያቀርባል። ምክንያቱም ሮማውያን አማልክቶቻቸውን የሚያውቋቸው በኃይላቸው ስለሆነ አሳንሰው እንዳይመለከቱትና የዓለም ንጉሥ፤ ጌታ፤ ፈጣሪ መሆኑን እንዲረዱት ነው። ለምሳሌ:-

- በባሕር (በመርከብ) ሄደ – ተአምራት አደረገ (4፥41፤ 6፥48፤54)
- ለሞት እየቀረበ – ተአምራት አደረገ (15፥33)
- ተራበ – በበለስዋ ላይ ተአምር ሠራ[120] (11፥12–20/119)

## ቅዱስ ጢሞቴዎስ

ቅዱስ ጢሞቴዎስ ሀገሩ በደርቤን ልስጥራ ነው። አያቱ ሎይድ እናቱ ኤዎንቄ እንደምትባል ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል። 2ጢሞ.1፥5 በእናቱ ከአይሁድ ወገን ሲሆን በአባቱ ደግሞ የግሪክ ሰው ነው። የሐዋ.16፥1።

119 Elkraza, Vol.2, No.2, p.9

120 Elkraza, Vol.1, No 3, August 1992.

ቅዱስ ጢሞቴዎስ የወንጌልን ቃል የሰማው በልስጥራ ከነበሩ ክርስቲያኖች ሲሆን ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር የተገናኙት በ50 ዓ.ም ሁለተኛውን ሐዋርያዊ ጉዞ ባደረገ ጊዜ ነበር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጢሞቴዎስ የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ሆነ። በዋለበት እየዋለ ባደረበት እያደረ ትምህርተ ክርስትናን በሚገባ ተማረ። ቅዱስ ጢሞቴዎስ የመንፈስ ቅዱስ አባቱ ቅዱስ ጳውሎስን በብዙ መንገድ አገልግሎታል።

1. መልእክት በማድረስ:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት የላካቸውን መልእክታት በብዛት ያደረሰለት ቅዱስ ጢሞቴዎስ ነው። እነዚህ ቦታዎች በእግር፣ በባሕር፣ በከብት፣ የሚኬድባቸው ናቸው። ሌት ተቀን መጓዝን ይጠይቃሉ። ጢሞቴዎስ ግን ያለመሰልቸት የአባቱን የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት በማድረሱ ዛሬ እኛ አንብበን ሕይወት እንድናገኝባቸው አድርጓል።

2. በማስተማር:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን በመላው ዓለም ለመስበክ ካስቻሉት መንገዶች ዋናው ደቀ መዛሙርቱን በአምሳሉ ቀርጾ በመንፈሳዊ ሕይወት ኮትኩቶ ማሰለፉ ነበር። ከነዚህ የቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጆች ታላቁ ቅዱስ ጢሞቴዎስ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ባልደረሰባቸውና እንዳያስተምር በተከለከለባቸው አካባቢዎች ቅዱስ ጢሞቴዎስን በመላክ ትምህርተ ወንጌል እንዲስፋፋ አድርጓል።

3. በችግሩ ጊዜ መርዳት:- ቅዱስ ጳውሎስ በሚታሠርበት ጊዜ ሁሉ ከጎኑ ካልተለዩት ደቀ መዛሙርቱ መካከል አንዱ የሆነው ጢሞቴዎስ መከራ ያላስበረገገው፣ ድካም፣ ችግርና ረሃብ ያልፈታው በዓላማው እስከመ ጨረሻ የጸና የቅዱስ ጳውሎስ ልጅ ነው።

ቅዱስ ጢሞቴዎስን ቅዱስ ጳውሎስ የኤፌሶን ሊቀ ጳጳስ አድርጎ ሾሞት ነበር። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ የኤፌሶን ሀገረ ስብከት የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ጢሞቴዎስ መሆኑን መስክሯል።[121] በዚህ ምንበሩ እስከ 67 ዓ.ም ድረስ አብያተ

121 Eusebius: Hist. Eccl. 1 III. C 4



ክርስቲያናትን እያስተከለ፣ ትምህርተ ወንጌልን እያስፋፋ አገልግሏል። ቅዱስ ጳውሎስ በ67 ዓ.ም በሮም አደባባይ በሰማዕትነት እስካረፈበት ቀን ድረስ ከሀገረ ስብከቱ ሥራ በተጨማሪ ቅዱስ ጳውሎስንም በየጊዜው ያገለግለው ነበር።

ከቅዱስ ጳውሎስ ዕረፍት በኋላ ወደ መንበሩ ለመጨረሻ ጊዜ በመመለስ ለ33 ዓመታት ያህል ከኤፌሶን ሳይወጣ ቤተክርስቲያንን በመንፈሳዊ አባትነቱ አገልግሏል።

ኤፌሶናውያን በዓመት አንድ ጊዜ የጣዖታቸውን የአርጤምስን በዓል ያከብሩ ነበር። ይህ በዓል የሚከበረው እያንዳንዱ ሰው ፊቱን በጨርቅ ተሸፍኖ ከቤቱ በመውጣት ያገኘውን ሰው ሁሉ እየፈለሰ ከፍ ዝቅ በማድረግና እናት አናቱን በዱላ እየቀጠቀጠ በመዝፈን ነበር።[122]

በ97 ዓ.ም ኤፌሶናውያን ይህን በዓላቸውን ሲያከብሩ ድርጊታቸው ጢሞቴዎስን ልቡን ስለነካው ሊያስተምራቸው ወደ ውጭ ቢወጣ እርሱንም ተሸክመው በመደብደብ መንገድ ላይ በሞትና በሕይወት መካከል ጥለውት ሄዱ። ተማሪዎቹም ወድቆ ሲያገኙት ጥቂት ጥቂት ብቻ ይተነፍስ ነበር። በአጥር አሾልከው በከተማዋ አጠገብ ወደሚገኝ መንደር ወስደው አስተኙት። ለ30 ቀናት ያህል በሕመም ተሰቃይቶ ዐረፈ። ደቀ መዛሙርቱ ሥጋውን ፒዮን በተባለው ተራራ ቀበሩት።[123]

በ356 ዓ.ም አፅሙ ወደ ቁስጥንጥንያ ተወስዶ በክብር ተቀመጠ። ቅዱስ ጢሞቴዎስ ጾም በጣም ይወድ ስለነበር ሥጋ፣ ቅቤ፣ ወይን፣ ወዘተ. እንዲያው በአጠቃላይ የላመ የጣመ መቅመስ አይወድም ነበር። በዚህ የተነሣ ሰውነቱ የመነመነ ሥራው ግን የፈጠነ ነበር።[124] ቅዱስ ጳውሎስ ‹ጥቂት ወይን ጠጣ› በማለት የመከረው ሰውነቱ በበሽታ እንዳይጠቃ መድኃኒት ይሆነው ዘንድ ነበር።

122 William Cave D.D., Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, Vol.1 p.114

123 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 114–115

124 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 115

# ቅዱስ ቲቶ

ትውልዱ በቆርንቶስ[125] ወገኑ ከግሪካውያን[126] የሆነ የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዛሙር ሲሆን ከቅዱስ ጳውሎስም ጋር የተገናኘው በአንጾኪያ ነው። ከዚያም ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ተመርጦ በ50 ዓ.ም (51) ወደ ኢየሩሳሌም ከወጡት የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን አበው አንዱ ነው። ገላ.2፥1–14። እንደ ቅዱስ ጢሞቴዎስ እርሱም ቅዱስ ጳውሎስን በመከተል አገልግሎታል። አውሳብዮስ እንደተናገረው ቅዱስ ጳውሎስ ቲቶን ለቀርጤስ የመጀመሪያው ሊቀጳጳስ አድርጎ ሾሞት ነበር።[127]

ቅዱስ ጳውሎስ በ67 ዓ.ም እስኪያርፍ ድረስ እንደጢሞቴዎስ ሁሉ እየተመላለሰ ሲያገለግለው ከቆየ በኋላ ሰማዕትነትን ሲቀበል ከእነ ቅዱስ ሉቃስ ጋር በመሆን ከቀበረው በኋላ ወደ ሀገረ ስብከቱ ተመልሷል። በቀርጤስ ዋና ከተማ በጎርቲና[128] ሲያገለግል ቆይቶ በ94 ዓመት ዕድሜው ዐርፏል።

## ቅዱስ በርናባስ

ቅዱስ በርናባስ የተወለደው በቆጵሮስ ደሴት በሰላሚስ ከተማ ሲሆን የቅዱስ ማርቆስ አጎት መሆኑ በቤተክርስቲያን ትውፊት ይነገራል። በቆጵሮስ በ60 ዓመት ከጌታችን ልደት በፊት ተማርከው የገቡ አይሁድ ነበሩ። የቅዱስ በርናባስ ቤተሰቦች ወደ ቆጵሮስ የገቡት በዚህ የተነሣ ነው። ትውልደ ነገዱ ከሌዋውያን ሲሆን ቤተሰቦቹ ይማርላቸው ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ላኩት። በዚያም የገማልያል ተማሪ በመሆን ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በአንድ የትምህርት ገበታ ተምረዋል።

በኢየሩሳሌም እያለ ወደ እኅቱ ወደ ማርያም የማርቆስ እናት ቤት ሲሄድ የጌታን ትምህርትና ተአምራት የመስማትና የማየት ዕድል አግኝቷል። በይሁዳ ምትክ የሐዋርያትን ክብር ለማግኘት ከታጩት

125 John Chrysostom Ham.i. Tit. S.1 Vol. xi. p.729

126 Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, p.119

127 Eusebius Hist. Eccl. 1.iii.c.4

128 Dictionary of Saints, p.331



መካከል ዮሴፍ የተባለው እርሱ መሆኑን ዮሐንስ አፈወርቅ ገልጧል።[129]

ቆጥሩ ከ72ቱ አርድዕት ሲሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚጠጉ ድኾች ስለበዙ መሬቱን ሸጦ ዋጋውን ለሐዋርያት አስረከበ። የሐዋ.14፥39። ቅዱስ ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሐዋርያት ሲመጣ ቀድሞ ያውቀው ስለነበር የመሰከረለት እርሱ ነው። በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት ክርስቲያኖች በየሀገሩ ሲበተኑ አስቀድሞ ፊልጶስ ወንጌላዊ ይሰብክበት ወደነበረው የአንጾኪያ ከተማ ሄደ። በዚያን ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ በቆጵሮስ ከተማ ያስተምር ነበር። በአንጾኪያ ወደ ነበረችው ቤተ ክርስቲያን ክርስትናን ተቀብለው የሚመጡ አረማውያንና አይሁድ እየበዙ በመምጣታቸው በርናባስ ጳውሎስን ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቅዱስ ማርቆስ የተነሣ እስኪለያዩ ድረስ አብረው ነበሩ።

ከቅዱስ ጳውሎስ ተለይቶ ቅዱስ ማርቆስን በመያዝ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጣ በኋላ አስቀድሞ ወደ ሮም፣ በኋላም ወደ እስክንድርያ፣ ከዚያም ወደ ይሁዳ በመምጣት ተዘዋውሮ ወንጌልን ከሰበከ በኋላ በመጨረሻ ወደ ሀገሩ ገባ።[130]

በቆጵሮስ በነበረችው ቤተ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስናን አቋሞ የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ በመሆን አረማውያንን እያጠመቀ ወንጌልን በማስተማር ላይ እያለ ከሶርያ የፈለሱ አይሁድ ወደ ቆጵሮስ መጡ። እነዚህ አይሁድ በምኩራባቸው ሲያስተምር ቢያዩት እጅግ ስለተበሳጩ ብዙ ካሰቃዩት በኋላ በ61 ዓ.ም አካባቢ በድንጋይ ወግረው ገደሉት።[131፡132]

## ሊቀ ዲያቆናት ቅዱስ እስጢፋኖስ

‹እስጢፋኖስ› ማለት በግሪክ ቋንቋ ‹አክሊል› ማለት ሲሆን ከአባቱ ከስምዖንና ከእናቱ ከሐና (ትውልዳቸው ከነገደ ብንያም ነው) የተወለደው ሐናስ በተባለ ስፍራ ነው። በማኅበረ ምእመናን መካከል በአረማውያንና በአይሁድ ሴቶች ጠብ የተነሣ መንቃቀፍ ተጀመረ።

129 John Chrysostom Ham. xi. in Act. Apost S.1.Vol.ix,p.90

130 Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, p.99-100

131 Alexand. Ib. n.18 et.seg

132 Lives of the Most Eminent Fathers, p.100 : Oxford Christian Dictionary, p. 132 New Catholic Encyclopaedia V.2, p.102

በዚህም ምክንያት ምእመናንን በሚገባ የሚያስተዳድሩ ዲያቆናት ለቤተክርስቲያኗ አስፈለጓት። ቅዱስ እስጢፋኖስ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን አገልጋይነት ከተሾሙት ሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ነበር።

ቅዱስ እስጢፋኖስ የሌሎች ስድስት ዲያቆናት አለቃ በመሆን (ሊቀ ዲያቆናት) ምእመናንን ከማገልገል ባሻገር ድውያንን በመፈወስ ትምህርተ ወንጌልን በማስፋፋት የበረታ ከመሆኑ በተጨማሪ ዲዳ ደንቆሮ ባገኘ ጊዜም እፍ ካለበት ይፈወስ ነበር።

እንዲያውም አንድ ጊዜ ናዖስ የሚባል ጠንቋይ ወደ አንድ በሬ ሄዶ በጆሮው ሹክ ቢለው ከሁለት ክፍል አለ። ቅዱስ እስጢፋኖስም በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የሞተውን አንሥቶ የተከፈለውን ገጥሞ ‹ናዖስን ጠርተኸው ና› ብሎ አዘዘው። ያም በሬ እንደ በለዓም አህያ በሰው ልሳን እየተናገረ ጠንቋዩ ናዖስን ‹ቅዱስ እስጢፋኖስ ይፈልግሃል› እያለ መጣራት ጀመረ።

አስቀድሞ በዚህ መሰሪ ተታሎ የነበረው ሕዝብ ቅዱስ እስጢፋኖስ ባደረገው ተአምር እየተገረመ አምኖ ተጠመቀ። ይህም አይሁድን በቅንዓት በቅዱስ እስጢፋኖስ ላይ እንዲነሣሡ አደረጋቸው።

በዘመኑ ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ብቻ 480 ምኩራባት ነበሩ።[133] እነዚህ ምኩራባት በተለያዩ ሀገሮች የሚኖሩ አይሁድ ለራሳቸው በኢየሩሳሌም ማረፊያ ይሆኗቸው ዘንድ ያሰሯቸው ሲሆኑ ልጆቻቸውን በመላክ የሚያስተምሩባቸው ትምህርት ቤቶች አብረው ነበሯቸው።[134] ከእነዚህ መካከል አምስቱ ምኩራባት ተባብረው በእስጢፋኖስ ላይ ተነሡበት። እነርሱም:-

1. በርም የነበሩና በኋላም ከባርነት ነፃ የወጡ አይሁድ ያሥሩት፤
2. የቀሬና አይሁድ፤
3. የእስክንድርያ አይሁድ፤
4. የኪልቅያ አይሁድ[135] እና
5. የታናሿ እስያ አይሁድ ናቸው።

133 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 54
134 ዝኒ ከማሁ፣
135 ቅዱስ አውሳብዮስ በእስጢፋኖስ ሞት ሊተባበር የቢታው ቤቶች ምኩራብ አባል ስለነበረ ነው።



እነዚህ አይሁድ ወደ ቅዱስ እስጢፋኖስ መጥተው ምን እንደጠየቁት ‹ይከራከሩት ነበር› የሐዋ.6፥8 ከማለት በቀር መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ነገር የለም። ቅዱስ የሐንስ አፈወርቅ ግን በድርሳኑ እንዲህ ይላል[136]

> «አንተ ጉበዝ እስኪ ንገረን ይህን የዋህ ሕዝብ የማይሆን ነገር እያስተማርህ የሚገርሙ ተአምር እያደረግህ ለምን ታሳስተዋለህ? አምላክ ነው ብለህ የምትሰብከውን እስኪ ንገረን? ከማርያም የተወለደ፣ የእንጨት ጠራቢ ልጅ ጌታም መፍጠር የሚችል ይመስልሃል?፣ የተወለደው በቤተልሔም፣ እየተማረ ያደገው በናዝሬት መሆኑ ጠፋህ እንዴ?፣ በተወለደ ጊዜ ከድህነቱ ብዛት የተነሣ የሚጠጋበት እንኳን አጥቶ በበረት ተጣጥሎ ከበረት የተወረወረ፣ ንጉሥ ሄሮድስን ፈርቶ የሸሸ፣ ጋጠኤትን ሊያወራ በዮርዳኖስ የተጠመቀ፣ የሚራብ የሚጠማ የሚደክመው የሚተኛ፣ ሲያዝ ማምለጥ፣ ለተከሰሰበትም ፍርድ መከላከል ያልቻለ፣ ሲሰቅሉት ሊመርጥ ያቃተው ነገር ግን የተፈረደበትን ሞት በመስቀል የሞተ እርሱን በመቃብር እንዲቀበርው ‹አምላኬ የምትናገር› ብለህ እንደምታለህ? እስቲ አሰበው እግዚአብሔር እንዲህ የሚሰቃይ ይመስልሃል?» ነበር ያሉት።

ቅዱስ እስጢፋኖስ ለጠየቁት ሁሉ የሚገባቸውን መልስ እየሰጠ ስላሳፈራቸው በክርክር ሊያሳምኑት አለመቻላቸውን ሲያውቁ በቁጣ ተንገሥተው ያለ አንዳች ፍርድ ከከተማዋ በስተሰሜን ወደ ቄድሮን በሚወስደው መንገድ አጠገብ በድንጋይ ወግረው ገደሉት።[137]

ያረፈው በተወለደበት ዕለት ጥር 1 ቀን በ35 ዓ.ም ሲሆን አይሁድ ከተበተኑ በኋላ የኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ሥጋውን ሌሊት በድብቅ በመረጉ ወስደው ከኢየሩሳሌም 20 ማይልስ ርቀት ላይ በምትገኘው ቃፋርጋማላ (የገማልኤል ከተማ ማለት ነው) በተባለች ቦታ ቀበሩት።[138]

136 Orato. in steph. s.l.vol.viii.p.18 inter supria
137 Ep. de invent. s. steph. ap. sur. ad. aug.ll
138 Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, p.69

## ቅዱስ ስምዖን የጌታ ወንድም

ቅዱስ ስምዖን የቅዱስ ዮሴፍ (የእመቤታችን ጠባቂ) ወንድም የቀለዮጳ ልጅ ሲሆን[139] እናቱ የእመቤታችን እኅት የሆነችውና በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ‹የቀለዮጳ ሚስት ማርያም› በመባል የተጠቀሰችው ናት።[140] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ እንደገለጠው ስምዖን የተወለደው ከጌታችን መወለድ 13 ዓመት አስቀድሞ ነው። ይህም ማለት ጌታችን ማስተማር በጀመረበት ዓመት የ43 ዓመት ጐልማሳ ነበር ማለት ነው።

የተማረው በረካባውያን[141] እግር ሥር ሲሆን ታናሹ ያዕቆብ በ62 ዓ.ም በአይሁድ እጅ በተሠዋ ጊዜ ሕዝቡን ሲመክርና ከዚህ በደል እንዲርቁ ያስተምር የነበረው ሰው ስምዖን መሆኑን አውሳብዮስና ኤጲፋንዮስ መስክረዋል።[142]

ቁጥሩ ከሰባ ሁለቱ አርድዕት ወገን ሲሆን በ62 ዓ.ም ታናሹ ያዕቆብ በሰማዕትነት ሲያርፍ ሐዋርያት ከየሀገረ ስብከታቸው በመሰባሰብ በመንበሩ ስምዖንን ሊቀጳጳስና ሾሙት።[143]

ስምዖን በኢየሩሳሌም መንበር በተቀመጠበት ዘመን በአካባቢው አስጊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነበረ። ውስጥ ውስጡን ይካሄድ የነበረው የአይሁድ ዓመፅ በሮማውያን ላይ የከረረበት ወቅት ነበር። በ64 ዓ.ም እንቅስቃሴው ለየለትና ኢየሩሳሌም መታመስ ጀመረች። የሮማ ጦርም ዙርያዋን ከበባት።[144]

139 Hegesib. ap. Eusebius Mist.Eccl.1.iii.C.11

140 ዝኒ ከማሁ፣ 32

141 ረካባውያን ማለት የረካብ ዘሮችና ተከታዮች ማለት ነው። ለአምላኩ እግዚአብሔር ቅንዓት ስለነበራቸው የረካብ ልጅ ኢዮናዳብ የበአልን አምልኮ ለማጥፋት ከንጉሥ ኢዩ ጋር ተባብሮ ነበር። 2ነገሥ 10፥15–31። ኢዮናዳብም ልጆቹ ከወይን ተከልክለው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ስላዘዛቸው ትእዛዙን ለሕገ እግዚአብሔር የተገዙ ነበሩ። ኤር.35፥1 ነሕ.3፥14።

142 Hegesib. ap Eusebius 1.ii.c.23: Haeres.1 xxviii c.7

143 Ap Eusebius 1.iii.c.11 vid.1.iv.c.22

144 የኢየሩሳሌም ከተማ ጌታችን በተናገረው ትንቢት የተነሣ በ70 ዓ.ም በሮማውያን ጦር እንዴት እንደ ጠፋች በፊልሞር መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁ.2 ላይ ተመልክቷል።



የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ስምዖንና በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃ.20፥21 ላይ የተናገረውን ቃል አስታውሰው አስቀድመው በመዘጋጀታቸው የልዑል እግዚአብሔር መልአክ እየመራቸው ወደ አንድ መሸሸጊያ ቦታ ወሰዳቸው።[145] ይህችም ቦታ ፔላ ትባላለች።

ፔላ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ የምትገኝ ከተማ ነች። ስሟን ያገኘችው በመቄዶንያ ከምትገኘው ተመሳሳይ ስም ካላት ከተማ ነው። ከመቄዶንያ የመጡ የእስክንድር ሠራዊት በዚህች ቦታ ሰፍረውባት ስለነበር ስሟን አትርፈውላታል።

ስምዖን በዚህች ቦታ እስከ ትራጃን ዘመነ መንግሥት ድረስ ከልጆቹ ጋር ከቆየ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም በመመለስ የፈረሰችን በመጠገን፣ የተበተኑትን በመሰብሰብ ክርስቲያናዊ ተግባሩን ቀጠለ።

በመጨረሻ ‹አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት› እያለ በማስተማሩ የአሕዛብን ልማድ የተቀበሉት የአይሁድ ሀብታሞች ተነሡበት። ተማለውም በወቅቱ የሶርያ ገዥ ለነበረው አቲቆስ ከሰሱት[146] ንጉሡም ትምህርቱ የእርሱንም ሕይወት የሚቃወም በመሆኑ ይህን ዓይነቱን ትምህርት እንዲተው አስጠንቅቆ ለቀቀው። ነገር ግን ይህን ትምህርት ገፋበት እንጂ አላቆመውም። በመሆኑም በቄሣር ትርያኑስ ዘመነ መንግሥት (98–117 ዓ.ም)

በንጉሥ ቲኪቆስ ዳግም ተይዞ ወደ እሥር ተጣለ። አይሁድ ‹ቀጣዩ የአይሁድ ንጉሥ እኔ ነኝ ይላል› ብለው ነገር ስላበዙበት ለብዙ ጊዜ በእሥር ሲሰቃይ ከኖረ በኋላ በ120 ዓመቱ በ106 ዓ.ም በሠይፍ ተሠይፎ ዐረፈ።[147]

## ወንጌላዊው ፊልጶስ

የተወለደው በቂሳርያ የወደብ ከተማ ነበር።[148] በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ እስጢፋኖስ ሞት ምክንያት

145 ኤጲፋንዮስ እንደተናገረው፣ (De pond. etmens.c.15)

146 Eusebius Mist. Eccl.1.iii.c.32.

147 Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, p. 175

148 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 771 ( Isidor, Epist. 1. ep.449)

የተነጣ ክርስቲያኖች በየሀገሩ እስኪበተኑ ድረስ ከሐዋርያት እግር ሥር ተምረዋል።

በ35 ዓ.ም እስጢፋኖስ በአይሁድ እጅ ሕይወቱ ስታልፍና ክርስቲያኖች በየቦታው ሲበተኑ ፊልጶስም ወደ ሰማርያይቱ ከተማ ወደ ጊቶን መጣ። ይህች ከተማ የታወቀው ጠንቋይ ሲሞን መሠርይ ተወልዶ ያደገባት ናት።[149]

ሰማርያውያን የእሥራኤልና የአረማውያን ድብልቆች ናቸው። በ7ኛው መ/ክ/ዘ አሥሩ የእሥራኤል ነገዶች ሲማረኩ በይሁዳ ምድር ከቀሩት እሥራኤላውያን ጋራ ባቢሎናውያን አምጥተው የቀላቀሉዋቸው አረማውያን ስለነበሩ ባሕላቸውም እምነታቸውም ተቀላቅሏል።

አይሁድ ከባቢሎን ምርኮ ሲመለሱና ቤተ መቅደሱን ሲሠሩ ከአረማውያን ጋር ተቀላቅላችኋል በማለት በሥራው እንዳይተባበሩ ከለከሉዋቸው። ከዚያም በኋላ በቤተ መቅደሱ እንዳይገለገሉ አገዱዋቸው። ከዚያ ቀን ጀምሮ አይሁድና ሰማርያውያን አይተባበሩም።

ሲሞን መሠርይ ከፊልጶስ ጋር የተዋወቀው በዚሁ ከተማ ነው። ሲሞን መሠርይ እጅግ አያሌ አስማታዊ ተአምራትን እያደረገ ለሕዝቡ ‹ለአይሁድ የተገለጽኩት አምላክ እኔ ነኝ› እያለ ያስተምር ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ‹መንፈስ ቅዱስ ነኝ› በማለት የክህደት ትምህርቱን ጀመረ።

በዚህ ዘመን ነበር ወንጌላዊ ፊልጶስ ሰማርያ የደረሰው። መንፈስ ቅዱስ በሰጠው ጸጋ እየተጠቀመ ሕዝቡን በወንጌል ትምህርት በማነፁና ሲሞን ሊያደርጋቸው የማይችሉትን ብዙ ተአምራት በማድረጉም የሰማርያ ሰዎች ሲሞንን እየተዉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመለሱ።

ሲሞን መሠርይ ብቻውን በመቅረቱና የፊልጶስም ትምህርትና ተአምራት ስላስገረመው አብሮ ከሕዝቡ ጋር አምኖ ተጠመቀ።[150]

---

149 Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, p.79.

150 ሲሞን መሠርይ ከዚህ በኋላ ወደ ሮማ ከሄደ ተመልሶ የግኖስቲኮች የሐሰት ትምህርት ቀንደኛ ተዋናይና ርእሰ መናፍቃን ሆኗል።



ከሰማርያ በኋላም በጋዛ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ አሳምኖ አጥምቋል። ቀጥሎም በአካባቢው በነበሩት ሀገሮች እየተዘዋወረ ሲያስተምር ቆይቶ ወደ ሀገሩ በመመለስ የሐዋ.21፥8፣9 በቂሳርያ ለብዙ ዓመታት ካስተማረ በኋላ በዚያው ዐርፏል።[151]

# ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ

## የመጀመሪያው ሐዋርያ – ለአፍሪካውያን

ይህ ጃንደረባ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት የሕንደኬ የገንዘብዋ ሁሉ ኃላፊ (በጅሮንድ) ነበር። ኢትዮጵያውያን ከጥንት ዘመን ጀምሮ ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ለበዓለ ፋሲካ በቤተ መቅደስ ይሰግዱ እንደነበረው ሁሉ ይህም ጃንደረባ ከ4000 ማይልስ በላይ ተጉዞ ኢየሩሳሌምን ተሳልሞ በመመለስ ላይ ነበረ።

ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ የነቢዩ ኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበረ። ነገር ግን የነቢዩ ቃል ስለማን እንደሚናገር ሊገባው አልቻለም። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በዚያ አካባቢ በመስበክ ላይ የነበረውን ወንጌላዊውን ፊልጶስ ላከለት። ወንጌላዊው ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ በመንገዱ ላይ አግኝቶት ወንጌልን ሰበከለት። ከዚያም አንድ ወንዝ ዳር ሲደርሱ በጃንደረባው ጠያቂነት ፊልጶስ አጠመቀው።[152]

ወንጌላዊው ፊልጶስ ጃንደረባውን ያጠመቀበት ወንዝ ቤት ሶርን በተባለችውና እስከ ዛሬ ድረስ ከኢየሩሳሌም 20 ማይልስ ርቀት በምትገኘው መንደርና በኬብሮን መካከል ባለው ኩሬብታ ሥር የሚመነጭ ነው።[153]

ቅዱስ ጀሮም የተባለው አባት ‹የኢትዮጵያውያን ሐዋርያ› በማለት ይጠራዋል። በሰፊው ለኢትዮጵያውያን ወንጌልን የሰበከ እርሱ ነውና![154]

---

151 Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, p.88-89.

152 ዛሬ በሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባይኖርም በአንዳንድ የጥንት ተራዎች ‹ከተጠመቀ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በላዩ ወረደ› ይላል። ገጽ ከግሡ ገጽ 87 V.39.Cod.Alexand. In Bible Reg. Angl - alique plures codd.Mss

153 Eusebius de. loc. Heb. invoc. BEÓÓOup.

154 Com.In Esai. l.lii. vol.lii,p.385

ይህ ጃንደረባ ወደ አክሱም ከመጣ በኋላ መጀመሪያ ያጠመቀው ንግሥት ሕንደኬን ሲሆን ከርስዋም በኋላ መኳንንቱና መሳፍንቱ አምነው ተጠመቁ። ከአክሱም ቀጥሎም ኑብያን አስተምሮአል። በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በጃንደረባው ይሰጥ በነበረው ትምህርተ ወንጌል ላይ የበለጠ ሐዋርያዊ ብርሃን አበራበት። በአካባቢው የነበረውንም ጣዖት አምልኮ በማስወገድ ከኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ጋር ብዙ ቦታዎችን አስተማረ።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከሀገሩ ቀጥሎ ወደ የመን በመሻገር ክርስትናን ከሰበከ በኋላ ወደ ፐርሺያ ከዚያም ወደ ሕንድ አመራ። በመጨረሻም ጥንት ታፕሮባና (Taprobana) ዛሬ ሲሎን በምትባለው ደሴት ወንጌልን በማስተማር ላይ እያለ በሰማዕትነት ዐለፈ።[155]

## ሌንጊኖስ ሰማዕት

ሌንጊኖስ ዘሩ ከዮናናውያን ወገን የሆነ የሮማ ወታደር ነበር። በጠባዩ ከነገር መቀላቀል አይወድም። በዚህም ምክንያት የሮማ ጭፍሮችና የአይሁድ አጋፋሪዎች በጌታችን ላይ ያን ሁሉ ስቃይ ሲያደርሱበት ገለልተኛ ለመሆን ፈልጎ ከአካባቢው ሸሽቶ ነበር።

በዕለተ ዓርብ ግን ሮማውያን በጌታችን መከራ ያልተባበረውን ሁሉ እንደ ንጉሥ ጠላት ስላዩት በመጨረሻዋ ሰዓት ‹ተፈፀመ› ካለ በኋላ ወደ ቀራንዮ ተራራ ወጣ። ሮማውያን የሁለቱን ሽፍቶች አጥንት ሲሰብሩ እርሱ ደግሞ ከሞተ መቼም አልጐዳም ብሎ የጌታን ጎኑን ወጋው።

ሌንጊኖስ አንድ ዓይኑ አያይም ነበረ። በዚያች ሰዓት ግን ከጌታ ግራ ጐን ውኃና ደም ሲወጣ በሽተኛ ዓይኑን ቢነካው ዓይኑ በራለት። በዚህ ጊዜ እጅግ በጣም ተገረመ። የሆነውንም ሁሉ ማስተዋል ጀመረ። በሞቱ ሰዓት የተደረጉትን ተአምራት መረመረ። ከዚህ በኋላ ‹በእውነት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው።› እያለ በኢየሩሳሌም ከተማ ማስተማር ጀመረ። ሮማውያንና አይሁድ በነገሩ ስለተበሳጩ አሳደዱት።

155 Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, p. 87-88; Ap Godign 1.i.c.18



ጌታችን ከተነሣ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስን ፈልጎ አገኘና ወንጌልን በሚገባ ተማረ። የሮማውያንና የአይሁድ ማሳደድ አላስቀምጠው ስላለ ኢየሩሳሌምን ለቆ ወደ ታናሿ እስያ ቀጳዶቅያ ከተማ በመምጣት ስብከቱን ቀጠለ። ብዙ ወገኖቹንም ወደ ክርስትና መልሷል። በመጨረሻ ግን የሮማ ወታደሮች ለንጉሥ ጢባርዮስ ቄሣር ስላመለከቱ በቀጳዶቅያ ከተማ ተይዞ ሐምሌ 23 ቀን አንገቱን ተሠይፎ ሰማዕትነትን ተቀብሏል።[156]

## አልዓዛርና እኅቶቹ

ማርያም እንተ እፍረት (ማርያም—ባለሽቱዋ):- በኢየሩሳሌም ከተማ በነበሩ ሮማውያን የተነሣ ብዙ መሸታ ቤቶች በድብቅና በግልጥ ተከፍተው ነበር። ማርያምም በዚህ ሙያ ከሚተዳደሩት የአይሁድ ሴቶች መካከል ነበረች። ነገር ግን ንስሐ ገብታ የቀደመ ኑሮዋን ትታ በጌታ እግር ሥር የ300 ዲናር ሽቶ ምን ማለት ነው?
(በማርከፍከፍ) ተመለሰች።
ሉቃ.7፥36–50። ጌታም መመለሷን ዓይቶ ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ወገን አደረጋት። ማርያም ከተመለሰች በኋላ ከጌታ አልለይም ብላ ልቡናዋን ለትምህርተ ወንጌል የሰጠች ነበረች። በዚህም ጌታ ‹የማይቀሟትን ዕድል መረጠች› ብሎ አመስግኗታል። ሉቃ.10፥42።

ማርታ:- የምትኖረው ከኢየሩሳሌም 3 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘው በቢታንያ መንደር ሲሆን። ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባና ሲወጣ በቤትዋ ያርፍ ነበር።

አልዓዛር:- ጌታ ይወደው የነበረ የቢታንያ ሰው ነው። የማርያምና የማርታ ወንድም ሲሆን ሞቶ ጌታ ከመቃብር አስነሥቶታል። ዮሐ.11፥1–53።

አልዓዛርና ሁለቱ እኅቶቹ ጌታችን ካረገ በኋላ በቀድሞው መኖርያቸው ክርስቲያኖችን በእንግድነት እየተቀበሉና ቤታቸውን የወንጌል መማርያ አድርገው ተቀምጠው ነበር። በኋላ ግን አይሁድ በክርስቲያኖች ላይ ስደት በማስነሣታቸው በ35 ዓ.ም አካባቢ

156 ስንክሳር ሐምሌ 23 ቀን፤ ( Seven Words on the Cross, by Pope Shenouda )

እልዓዛርንና ሁለቱን እኅቶቹን በቀዳዳ መርከብ ጭነው ወደ ባሕር ጣሉአቸው። እነርሱም በልዑል እግዚአብሔር ረዳትነት ከሞት ተርፈው ወደ ሲፕረስ በመምጣት ኑሮአቸውን በዚያ ከመሠረቱ በኋላ እልዓዛር የመጀመሪያው የኪትዮን (ፈረንሣይ ውስጥ የምትገኝ ከተማ) ጳጳስ በመሆን በዚያ ስፍራ ክርስትናን ማስፋፋታቸውን የምሥራቃውያን ትውፊት ይገልጣል።[157]

## ጲላጦስ ሰማዕት

ጲላጦስ ሮማዊ ሲሆን የይሁዳ ገዥ ተደርጐ በጢባርዮስ ቄሣር የተሾመው በ26 ዓ.ም ነው። ለ8 ዓመታት ካስተዳደረ በኋላ ነበር ጌታችን በፊቱ ለፍርድ የቀረበው። ጲላጦስ የጌታን ንጽሕና በመረዳቱ በመጀመሪያ ሊፈታው ወድዶ ነበር። ነገር ግን ‹ይህንን ብታደርግ የቄሣር ወዳጅ አይደለህም› ብለው አይሁድ ስላስፈራሩት አስገረፈው። አሁንም አይሁድ ‹ሞት ይገባዋል› ብለው ስለሙኙበት ‹ከደሙ ንጹሕ ነኝ› በማለት አሳልፎ ሰጣቸው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱን የአይሁድ አለቆች ሲሰሙ የመቃብሩን ጠባቂዎች ‹ደቀ መዛሙርቱ ሥጋውን ሰርቀው ወሰዱት› በማለት እንዲያስወሩ መከረዋቸው ነበር።

ይህን ወሬ ንጉሥ ጲላጦስ እንደሰማ ጠባቂዎቹን አስጠርቶ ከ4 ወገን ከፍሎ ለየብቻ ቢጠይቃቸው በጊዜና በወሰደው ሰው ማንነት እርስ በእርሳቸው ተለያዩ።[158] በዚህም ጊዜ ‹በእውነት ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቷል› በማለት መሠከረና አምላክነቱን አመነ። ይህንንም እምነቱን ላገኛቸው ሁሉ መናገር ጀመረ።

ለ2 ዓመታት ያህል የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱን በመመስከሩ በ36 ዓ.ም በጢባርዮስ ቄሣር ፍርድ ቤት ተከስሶ አንገቱን በመሠየፍ በሰማዕትነት ዐረፈ።[159]

እግዚአብሔር አምላካችን በእነዚህ ቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ ሁላችንንም በምግባር በሃይማኖት ያጽናን! አሜን።

---

157 Oxford Christian Dictionary, p. 793

159 Oxford Christian Dictionary, p. 1072

158 ግብረ ሕማማት ለፋሲካ ዋዜማ የሚነበበውን ተመልከት